አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

በደብረ ብርሃንና በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ለሚሠለጥኑ መምህራን የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርህ-ትምህርቱን አላማዎች የሚያሟላ ነው ?

ደመቀ ሙሉጌታ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ቋ.ዋ.ሥ.
ቤተ መጻሕፍት
ILS
LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ግንቦት 1989

በደብረ ብርሃንና በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ለሚሠለጥኑ መምራን የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማዎች የሚያሟላ ነው ?

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድህረ-ምረቃ ትምህርት
ቤት የቀረበ ጥናት

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን
በማስተማር /TEAM/ ለማስተርስ
ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ
ደመቀ ሙሉጌታ

ግንቦት 1989

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

በደብረ ብርሃንና በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች
ለሚሠለጥኑ መምህራን የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ
መማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-
ትምህርቱን አላማዎች የሚያሟላ ነው?

በ
ደመቀ ሙሉጌታ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ደ/ል/ማ፡ ንጋሠ
አማካሪ

ማሬቱ፡ ሐውዴ
ፈታኝ

YONAS ADMASSU
ፈታኝ

ምስጋና (Acknowledgement)

ከጥናቱ መነሻ ጀምሮ እስከፍጻሜው ድረስ ውድ ጊዜያቸውን በመሰዋት፣ ጽሑፉን ደጋግመው በማንበብ፣ በማስተካከልና ምክር በመለገስ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለአቶ ይልማ ከበደ የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ::

በትምህርት ፋኩልቲ መምህር የሆኑት ዶ/ር ማረው ዘውዴ የጥናቱን ቢጋርና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎቼን በመመልከት፣ ማስተካከያ በመስጠትና የጥናቱን አቅጣጫ በመጠቆም ላደረጉልኝ ትብብር ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው::

እንዲሁም ለጥናቱ መሳካት የሚረዳ ገንቢ አስተያየት በመስጠትና በማበረታታት ድጋፍ ያደረጉልኝን ዶ/ር አረጋ ሀይለሚካኤልን ላመሰግናቸው እወዳለሁ::

በትምህርት ላይ በቆየሁበት ጊዜ ቤተሰብ የማስተዳደርን ኃላፊነት በመሸከምና እኔንም በማበረታታት ለረዳችኝ ባለቤቴ ወ/ሮ አስቴር ዘሪሁን፣ የማቴሪያልና የሞራል ድጋፉ ላልተለየኝ አጐቴ አቶ አሊጋዝ ከበደ የተለዬ ምስጋና አቀርባለሁ::

በሁለት ዓመቱ የትምህርት ወቅት በልዩ ልዩ መልኩ ርዳታቸውን የለገሱኝ አቶ ዳኜ በላቸው፣ አቶ ክፍሌ አደራ፣ አቶ ክፍሌ ሀ/ማርያም፣ አቶ ስጠታው ይማም፣ አቶ ጥላሁን ገ/ክርስቶስ፣ አቶ ተስፋዬ ገ/መስቀል አቶ ሞላ አየለ፣ ወ/ት ወርቅነሽ አሊጋዝ፣ አቶ ውብሸት ዘሪሁንና ወ/ሮ በላይነሽ ዘሪሁን ከፍተኛ ባለውለታዬ ናቸው::

ለጥናቱ ወደ ውጤት መድረስ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች ሲሰበሰቡ ቀና ትብብር ያደረጉልኝ የደብረ ብርሃንና የደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ዲሬክተሮች፣ መምህራንና ሠልጣኞች እንዲሁም የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ባልደረቦችን አመሰግናቸዋለሁ::

በሥርዓተ ትምህርት ኢንስቲትዩት የመምህራን ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች መረጃ በመስጠትና ለጥናቱ ሊጠቅመኝ በሚችል ወርክሾፕ ላይ እንድሳተፍ በመፍቀዳቸው ትብብራቸውን አደንቃለሁ::

በመጨረሻም ጥናቱን በኮምፒውተር ለጻፈችልኝ ለወ/ት ደብሪቱ መገርሣ ምስጋናዬን እገልጻለሁ::

ማውጫ

ርእስት ገጽ

ምስጋና

አጠቃሎ

የሠንጠረዥ ዝርዝር

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አላማ 3

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ 5

1.4 የጥናቱ ወሰን 5

1.5 የቁልፍ ቃላት መግለጫ 6

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት 8

2.1 የመምህራን ሥልጠና 8

2.1.1 በሥልጠና ወቅት ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች . . . 9

2.1.2 ከሥልጣኙ የሚጠበቁ ግዴታዎች 11

2.2 የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ምንነት 12

2.2.1 መምህራንን ለማሠልጠን የሚያገለግል መርሀ-ትምህርት . . 14

2.2.2 የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ክፍሎች 16

2.2.2.1 የመርሀ-ትምህርት አላማ 17

2.2.2.1.1 አጠቃላይ አላማ 18

2.2.2.1.2 ዝርዝር አላማ 18

2.2.2.2 የመርሀ-ትምህርት ይዘት 19

2.2.2.3 የማስተማር-መማር ዘዴ 21

2.2.2.4 ግምገማ 24

2.3 የቋንቋ መማሪያ (ማስተማሪያ) መጻሕፍት 25
2.3.1 የተማሪው መጽሐፍ 25
2.3.2 የመምህሩ መምሪያ 27
2.4 የመርሀ-ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍ ግንኙነት 30
2.5 የመጻሕፍት ግምገማ 32

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች 35
3.1 የጥናቱ ዘዴ 35
3.1.1 የመረጃ ምንጮች 35
3.1.2 የናሙናዎች አመራረጥ 36
3.1.3 የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች 37
3.1.3.1 የመርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ 37
3.1.3.2 መጠይቅ 39
3.1.3.3 ቃለ መጠይቅ 40
3.1.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ 42
3.1.4.1 የመርሀ-ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍ
አተናተን 42
3.1.4.2 የመጠይቅ አተናተን 42
3.1.4.3 የቃለ መጠይቅ አተናተን 42

ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ትንተናና ማብራሪያ 43
4.1 የመረጃዎች ትንተና 43
4.1.1 የመርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ ትንተና 43
4.1.2 ከመጠይቅ የተገኙ ምላሾች ትንተና 55
4.1.2.1 ከሠልጣኞች የተገኙ መረጃዎች ትንተና 55
4.1.2.2 ከመምህራን-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች መግለጫ 65
4.1.2.2.1 የመምህራኑን የግል ሁኔታ በተመለከተ ለቀረቡ
ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች 65

4.1.2.2.2 መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን በሚመለከት
ለመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች 66

4.1.2.2.3 ለተጨማሪ አስተያየት ከመምህራን የተገኙ
መልሶች መግለጫ 73
4.1.3 ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና 74
4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ 75
4.2.1 የመማሪያ መጽሐፉና የመርሀ-ትምህርቱ ግንኙነት . . . 75
4.2.2. ከመጠይቅ የተገኙ ውጤቶች 77
4.2.3 ከቃለመጠይቅ የተገኙ ውጤቶች 80

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳቦች 82
5.1 ማጠቃለያ 82
5.2 የመፍትሔ ሀሳቦች 85
ዋቢዎች 87
አባሪዎች
አባሪ 1 የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት አላማዎች 92
" 2 ከመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የሚወጡ
መምህራን የባህርይ ገጽታ (ፕሮፋይል) 95
" 3 የግንኙነት ቀመርና አተረጓጎም 96
" 4 የግንኙነት ቀመር አሠራር 97
" 5 ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ 98
" 6 ለሠልጣኞች የቀረበ መጠይቅ 107
" 7 ለትምህርት ባለሙያው የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ . . 112
" 8 ለመምህሩ የቀረበ ቃለ መጠይቅ 113
" 9 የትምህርት ባለሙያው ቃለ መጠይቅ መልስ . . . 114
" 10 የመምህሩ ቃለ-መጠይቅ መልስ 119

አጠቃሎ (Abstract)

ይህ ጥናት አላማ አድርጐ የተነሳው በ1987 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ የዋለው የደሴና የደብረብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማዎች ማሟላት መቻሉን መገምገም ነው፡፡

በጥናቱ ሂደት የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ይጣጣማል ? መጽሐፉ ለመምህርነት ሥልጠና ተስማሚ ነው ? የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ በአግባቡ የተዘጋጀ ነው ? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተሞክሯል፡፡

በክልል ደረጃ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ከማዕከል ከተሠራጨው መርሀ-ትምህርት ልዩ ልዩ ክፍሎች ጋር ያለው ግንኙነት የጠነከረ አለመሆኑን የተዛምዶ ቀመሩ ውጤት አረጋግጧል፡፡

መምህራንን ለማሠልጠን ያለውን ብቃት ለመረዳት ለመምህራንና ዕጩ መምህራን መጠይቆች ተበትነው ከተገኘው ምላሽ መማሪያ መጽሐፉ ሊጠቅም የሚችለው በዝቅኛ ደረጃ መሆኑ ታውቋል፡፡

የሥልጠናውን አላማ ለማሳካት እንዲቻል በመጽሐፉ የዝግጅት ሂደት ምን ያህል ጥረት እንደተደረገ ለማወቅ ለአንድ የትምህርት ባለሙያና ለመጽሐፉ አዘጋጅ መምህር ቃለመጠይቅ ቀርቧል፡፡ ከተጠያቂዎቹ በተገኘው ምላሽ መሠረት መጽሐፉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዘጋጅቶ ወዲያውኑ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት የሚያመለክተው አሁን ያለው የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞቹ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ሙሉ በሙሉ ለማሳካት የማይችል መሆኑን ነው፡፡

- የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉት መልመጃዎች በአግባቡ አለመዘጋጀታቸው፣
- የመጽሐፉ ይዘቶች የተለያዩ የማስተማር-መማር ዘዴዎችን ለማስተዋወቅ አመቺ አለመሆናቸው፣
- የትምህርት ዕቅድ ዝግጅትና የትም/መርጃ መሣሪያዎችን አጠቃቀም የሚመለከቱት ይዘቶች የተሟሉ አለመሆኑ፣

መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ በአጥጋቢ ሁኔታ ግብ ለማስመታት እንደማይችል ያመለክታሉ።

በዚህ መሠረት ከአሁኑ የተሻለ ብቃት ያለው የ1ኛ ደረጃ መምህራንን ለማሠልጠን የሚረዳ የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ለማዘጋጀት እንዲቻል ከችግሮቹ በመነሳት በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ የመፍትሔ ሐሳቦች ቀርበዋል።

የሠንጠረዦች ዝርዝር

ገጽ

ሠንጠረዥ 1. በናሙናነት የተመረጡ ሠልጣኞች ዝርዝር 37

" 2. የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዝርዝር አላማዎች 44

" 3. የመርሀ-ትምህርቱ ይዘቶች 45

" 4. የመርሀ-ትምህርቱ የማስተማር-መማር ዘዴዎች 46

" 5. የመርሀ-ትምህርቱ ግምገማዎች 47

" 6. የደሴና የደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች 48

" 7. የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ሥርጭት . . 49

" 8. የመርሀ-ትምህርቱ ዝርዝር አላማዎችና የመጽሐፉ መልመጃዎች ግንኙነት 51

" 9. የመርሀ-ትምህርቱ ይዘቶችና የመልመጃዎቹ ግንኙነት . . . 52

" 10. የመርሀ-ትምህርቱ ማስተማር-መማር ዘዴዎችና የመልመጃዎች ግንኙነት 53

" 11. የመርሀ-ትምህርቱ ግምገማዎችና የመልመጃዎቹ ግንኙነት 54

" 12. መጠይቅ የሞሉ ሠልጣኞች አጠቃላይ መግለጫ 55

" 13. የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፉን የይዘት ብቃት የሚመለከቱ ጥያቄዎች ምላሾች 56

" 14. የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን የቋንቋ አጠቃቀም የሚመለከቱ ጥያቄዎች ምላሾች 57

" 15. የመጽሐፉን መልመጃዎች አዘገጃጀት የሚመለከቱ ጥያቄዎች ምላሾች 58

" 16. የማስተማር-መማር ዘዴን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ ምላሾች መግለጫ 60

" 17. በራስ መተማመንን በሚመለከት ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ 63

ገጽ

ሠንጠረዥ18. መጠይቅ የሞሉ መምህራን አጠቃላይ መግለጫ 65
" 19. የመማሪያ መጽሐፉን ይዘት ብቃት የሚመለከቱ
ጥያቄዎች ምላሾች 66
" 20. የመማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች አዘገጃጀት የሚመ
ለከቱ ጥያቄዎች ምላሾች 67
" 21. የመጽሐፉን የማስተማር ዘዴ የሚመለከቱ ጥያቄዎች
ምላሾች 69
" 22. የመርሀ-ትምህርቱንና መማሪያ መጽሐፉን ግንኙነት
የሚመለከቱ ጥያቄዎች ምላሾች 71
" 23. አጠቃላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለቀረቡ ጥያቄዎች
የተሰጡ ምላሾች 72
" 24. ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ባለሙያዎች አጠቃላይ
መግለጫ 74

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ (INTRODUCTION)

1.1 የጥናቱ ዳራ (BACKGROUND OF THE STUDY)

የመምህራን ትምህርት በአውሮፖ የተጀመረው በ17ኛው ክፍለ ዘመን ቢሆንም (አብርሃም፣ 1986 : 3) በአገራችን ግን ሥራ ላይ የዋለው ዘግይቶ ነው። የመጀመሪያው የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም በ1937 ዓ.ም በዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ ተጀመረ። (ተሾመ፣ 1979 : 167፤ ሀይሎም፣ 1993 :2) ከዚያም የማሠልጠኛ ተቋሞቹ ቁጥር ቀስ በቀስ እየጨመረ ሄዶ እስከ 1949 ዓ.ም. ድረስ የሀረር፣ የጅማ፣ የናዝሬትና የደብረብርሃን ማሠልጠኛዎች ተከፈቱ። (ተሾመ፣ 1979፣ 394) የተቋሞቹ መሠረታዊ አላማም የ1ኛ ደረጃ መምህራንን ለማሠልጠን እንደነበረ ተገልጿል።

በዚያን ጊዜ የነበረው ሥልጠና የተለያዩ ኘሮግራሞችን የያዘ ስለሆነ፣ ሠልጣኞቹ በትምህርት ላይ የሚቆዩት ከ1-4 ዓመት ሲሆን የሚመለመሉትም ከ8ኛ-11ኛ ክፍል ደረጃ ያላቸው ነበሩ። (ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1977 ዓ.ም ገጽ 35) በዚህ ዓይነት የሚካሄደው ሥልጠና እስከ 1956 ዓ.ም ከቀጠለ በኋላ ከ1956 ዓ.ም ጀምሮ በአንድ ወጥነት ሁሉም የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች 10ኛ ክፍልን የጨረሱ ተማሪዎች በመቀበል ማሠልጠን ጀመሩ። (ተሾመ፣ 1979፡ 508)። ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ ግን ተቋሞቹ 12ኛ ክፍልን የፈጸሙ ተማሪዎች በመቀበል የአንድ ዓመት የቅድመ ሥራ ሥልጠና ያካሂዱ ጀመር። (ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1979 ዓ.ም ገጽ 18)

የአንደኛ ደረጃ መምህራንን ለማፍራት የሚያስችሉትን የማሠልጠኛ ተቋሞች ቀስ በቀስ በየአካባቢው ለማስፋፋት የተቻለ ቢሆንም (ሀይሎም፣ 1993 : 3) የመምህራንን አሠለጣጠን በተመለከተ ቋሚ የሆነ አንድ ወጥ ፖሊሲ ስላልነበረ ሥርዓተ ትምህርቱ በቅርጽም ሆነ በይዘት በየጊዜው ሲለዋወጥ ቆይቷል። እያንዳንዱ የመምህራን ማሠልጠኛ

በዚህ ክፍል ውስጥ ዓ.ም የሚል ያልተከተላቸው ሁሉ የኢውሮፓውያንን የዘመን አቆጣጠር የሚመለከቱ ናቸው።

ተቋም በመምህራን አማካይነት በሚዘጋጅ የተለያዩ የማስተማሪያ ጽሑፍ ከመጠቀም በቀር በመሥያው በሠለጠኑ ሰዎች በማዕከል የተዘጋጀ የማስተማሪያ መጽሐፍ ያልነበረው መሆኑ ተገልጿል። (ትምህርት ሚኒስቴር 1972 ዓ.ም. ገጽ 1)

በትምህርት ሚኒስቴር ሰነድ ውስጥ (1972 ዓ.ም ገጽ 1) እንደተጠቀሰው ለአንደኛ ደረጃ መምህራን አሠለጣጠን የሚያገለግል ብሔራዊ ሥርዓተ-ትምህርት ለመጀመሪያ ጊዜ የተነደፈው በ1958 ዓ.ም. ነው። ዝግጅቱም የተከናወነው በትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት ከየማሠልጠኛ ተቋሞች በተመረጡ መምህራንና በሌሎች ባለሙያዎች አማካይነት ነበር። ሆኖም ሥርዓተ ትምህርቱ ቢዘጋጅም በዚያን ወቅት የማስተማሪያ መጽሐፍ አልነበረም። ይህም ችግር እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ሳይወገድ መቆየቱን የተጠቀሰው ሰነድ ያስረዳል።

ከጥቅምት 1972 ዓ.ም ጀምሮ የትምህርት ሚኒስቴር ባለሙያዎች፣ የማሠልጠኛ ተቋሞች መምህራንና የውጭ ኤክስፐርቶች በተሳተፉበት ወርክሾፕ የሥርዓተ ትምህርትና የማስተማሪያ ጽሑፍ ረቂቅ ተዘጋጅቶ በጊዜ እጥረት ምክንያት ረቂቆቹን ለማሻሻል ባለመቻሉ እንዳሉ እንዲሠራባቸው መደረጉን የሥርዓተ ትምህርቱ ንድፍ መግቢያ (ትምህርት ሚኒስቴር 1972 ዓ.ም) ያስረዳል። የማስተማሪያ መጽሐፉ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሻሽሎ የታተመው በ1982 ዓ.ም ሲሆን (ሥርዓተ ትምህርት እንስቲትዩት 1982 ዓ.ም) የሥርዓተ ትምህርቱ ንድፍና የመማሪያ መጽሐፉ እስከ 1986 ዓ.ም ድረስ ሲሠራባቸው ቆይቷል።

ዱቢንና ኦልሽቴይን (1986 ፡ 32) መርሀ-ትምህርት ለትምህርት ዓላማ ግብ መምታት የሚያገለግል ተግባራዊ መመሪያ መሆኑን ይገልጻሉ። ይሁን እንጅ እስከ 1986 ዓ.ም ድረስ ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀ መርሀ-ትምህርትና በርሱም ላይ የተመሠረተና የመርሀ-ትምህርቱን አላማ የሚያራምድ መማሪያ መጽሐፍ እንዳልነበረ ከላይ ከተጠቀሱት መረጃዎች እንረዳለን።

በ1986 ዓ.ም አዲስ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ስለተነደፈ (የሽግግር መንግሥት፣ 1986 ዓ.ም) የፖሊሲውን ለውጥ መነሻ በማድረግ የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የማስተማሪያ መሣሪያዎች ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ተተክተዋል። አዲሱ መርሀ-ትምህርት በአገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀ ሲሆን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው (1986 ዓ.ም ገጽ 7) ለክልሎች በሰጠው ሥልጣን መሠረት የ1ኛ ደረጃ ትምህርት በአፍ

መፍቻ ቁንቁ እንዲሰጥ በመወሰኑ የመማሪያ መጽሐፉ በየአካባቢው እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

ይህ ጥናትም በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ደረጃ በተዘጋጀው የአማርኛ ቁንቁ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ላይ ያተኮረ ነው።
ለጥናቱም አነሳሽ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል፡-

- በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቁንቁ ማስተማሪያ መጻሕፍት ላይ የተለያዩ የቅድመና ድህረ ምረቃ ጥናታዊ ጽሑፎች የተዘጋጁ ሲሆን (አያሌው፣ 1985 ዓ.ም፤ ጌታቸው 1986 ዓ.ም፤ አሥራቴ 1988 ዓ.ም) በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የማስተማሪያ መጻሕፍት ላይ ግን ጥናቶች ባለመካሄዳቸው፤
- ከላይ ከተጠቀሱት መረጃዎች ለመረዳት እንደሚቻለው ከዚህ በፊት የታየው የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የማስተማሪያ-መሣሪያዎች ዝግጅት ተለዋዋጭና በችኮላ የተከናወነ በመሆኑ የአሁኑም ቢሆን ከዚህ ችግር የተላቀቀ መሆኑን ለመረዳት በመፈለግ፤
- የአገር አቀፉ መርሀ-ትምህርትና በክልል ደረጃ የተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ምን ያህል ተጣጥመው ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሰመረ ውጤት እንደሚያመጡ መታወቁ ጠቃሚ በመሆኑ፤
- የመማሪያ መጽሐፉ አዲስ እንደመሆኑ ጥናት ሊደረግበትና በተግባር ላይ ከዋለ በኋላ የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዲወገዱ የማሻሻያ ሀሳብ ሊሰጥበት ይገባል፣ የሚሉት ይገኙበታል።

ከዚህ አንፃር በማየት በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ለሚገኙት ለደብረብርሃንና ለደሴ የ1ኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች በተዘጋጀው የአማርኛ ቁንቁ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ጥናቱን ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

1.2 የጥናቱ ዓላማ (OBJECTIVES OF THE STUDY)

ይህ ጥናት አላማ አድርጐ የተነሳው ለደብረ ብርሃንና ለደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀው የአማርኛ ቁንቁ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን ዓላማ ለማሳካት መቻሉን መገምገም ነው።

የመማሪያ መጻሕፍት ድርሻ መርሀ-ትምህርትን በተግባር መተርጐም በመሆኑ (ብራውንና ሌሎች፣ 1982) አዲሱ መጽሐፍ የታለመለትን ውጤት ለማስገኘት መቻሉና አለመቻሉ በጥናቱ ይረጋገጣል።

በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው የ1ኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት መግቢያ ላይ ተከታዩ ሀሳብ ሰፍሯል።

> ዝግጅቱ መሠረት ያደረገው የዕጩ መምህራንን የቋንቋ ክህሎት ማዳበርና የማስተማር-መማር ዘዴዎችን ማስጨበጥ ሲሆን ለዚህም አላማ ተግባራዊነት የተለያዩ ይዘቶች ተቀርጸዋል (ሥርዓተ ትምህርት፣ 1987 ዓ.ም መግቢያ)

ይህንንም መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ስምንት አጠቃላይ አላማዎች ተነድፈዋል።

1- የቋንቋን መሠረታዊ ሐሳብ ይረዳሉ፤
2- የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮችን ይገነዘባሉ፤
3- የሥርዓተ-ነጥቦችን አጠቃቀም ያውቃሉ፤
4- የሥነ-ጽሑፍ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤
5- ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
6- ከአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያው ሳይክል (1ኛ-4ኛ) የትምህርት መሣሪያዎች ጋር ይተዋወቃሉ፤
7- የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎችን አዘገጃጀትና አጠቃቀም ይረዳሉ፤
8- የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀምን ይገነዘባሉ፤

(ሥርዓተ ትምህርት ኢንስቲትዩት፣ 1987 ዓ.ም)

እነዚህ አላማዎች በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ አማካይነት ግብ መምታታቸውን ይህ ጥናት በዋናነት ከመረመረ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ታስቧል።

1- መጽሐፉ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ይጣጣማል ?
2- መጽሐፉ ለቋንቋ መምህርነት የሚያበቃ ሙያ ሊያስጨብጥ ይችላል ?
3- የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ በአግባቡ የተዘጋጀ ነው ?

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ (SIGNIFICANCE OF THE STUDY)

ይህ ጥናት ለደብረ ብርሃንና ለደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች፣ ለ1ኛ ደረጃ መምህርነት ሥልጠና የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ ትምህርቱን ዓላማ ከማሟላት አንፃር ያለውን ብቃት ስለሚገመግምና ጥንካሬና ጉድለቱን ስለሚጠቁም ለመጽሐፉ ተጠቃሚዎች የበኩሉን አስተዋጽዖ ያበረክታል።

1- የክልሉ ትምህርት ቢሮ የሥርዓተ-ትምህርት መምሪያ ባለሙያዎች ወደፊት ለሚያካሂዱት መጽሐፉን የማሻሻል ተግባር በጠቋሚነት ይረዳቸዋል፤

2- በሁለቱ የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ውስጥ ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአጋዥነት ያገለግላል፤

3- ለወደፊቱ በዚህ መስክ ጥናት ለሚያካሄዱ ተመራማሪዎች በመነሻነት ያገለግላል።

1.4 የጥናቱ ወሰን (SCOPE OF THE STUDY)

ይህ ጥናት በዋናነት የሚያተኩረው በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት ቢሮ ሥር ለሚገኙት ለደብረብርሃንና ለደሴ መምህራን ማሠልኛ ተቋሞች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ላይ ነው። መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ከማሳካት አንፃር የሚገመገም በመሆኑ መርሀ-ትምህርቱ በማነፃፀሪያነት ብቻ አገልግሏል። የሁለቱን ሰነዶች ግንኙነት ከማየት ውጭ መርሀ-ትምህርቱን በተናጠል ወስዶ መመርመር አላስፈለገም።

ከተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት በተገኘው ሀሳብ መሠረት ለመምህርነት ሥልጠና የሚዘጋጅ መርሀ-ትምህርት የሚከተሉትን መሠረታዊ ጉዳዮች ማሟላት ይጠበቅበታል።

- ለማስተማር ዘዴ የበለጠ ድርሻ መስጠት አለበት (ክሮስ፣ 1987፤ ቢርደንና ሌሎች፣ 1992፤ ፀሁርያክ፣ 1996፤ ሥርዓተ ትምህርት ኢንስቲትዩት፣ 1997)።
- አቢይ አላማዎች አጠቃላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሲያተኩሩ ዝርዝር ዓላማዎች ደግሞ ተማሪዎች እንዲያሳዩ የሚፈለገውን የባህሪይ ለውጥ ማመልከት አለባቸው። (ታባ፣ 1962 ፤ ብራውንና ሌሎች፣ 1982)

- የመርሀ ትምህርቱ ይዘት የቋንቋ እውቀትና ክሂልን ማካተት ይገባዋል። (ዌስት፣ 1960፤ ሂል እና ደቢን፣ 1979፣ ካኒንግወርዝ፣ 1984)
- ዝግጅቱ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎችና በመምህራን ተሳትፎ ቢከናወን ውጤታማ ይሆናል። (ፋሪልና ሄንማን፣ 1989፤ ሀርመር፣ 1991)

በአጥኚው እምነት ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞቹ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት እነዚህን ሁኔታዎች አሟልቶ ተገኝቷል። በዚህም የተነሳ የመርሀ-ትምህርቱን የአዘገጃጀት ሂደት ድክመትና ጥንካሬ በዝርዝር ማየት አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። በመርሀ-ትምህርቱ አላማዎች አቀራረጽ ረገድም የጐላ ድክመት ስላልታየው አጥኚው እንዳለ በመቀበል ለጥናቱ መሠረት አድርጓቸዋል። ስለዚህ ጥናቱ በዋናነት የሚያተኩርበት የመርሀ-ትምህርቱ አላማዎች በመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፉ አማካይነት ግብ ሊመቱ መቻላቸውን በመገምገሙ ላይ ነው።

1.5 የቁልፍ ቃላት መግለጫ (DEFINITION OF IMPORTANT TERMS)

በጥናቱ ውስጥ የተጠቀሱት ቁልፍ ቃላት አግባብ እንደሚከተለው ተብራርቷል።

መልመጃ (Exercise)፡- በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት የትም/ይዘቶች ላይ ተመስርተው የቋንቋ ክህሎትን ያዳብራሉ ተብለው የቀረቡ ጥያቄዎችን ይመለከታል።

መርሀ-ትምህርት (Syllabus)፡- ለተወሰነ ደረጃ በተዘጋጀ የቋንቋ ትምህርት ውስጥ አላማ፣ ይዘት፣ የመማር-ማስተማር ክንውንና የግምገማ ስልቶች ጠቅለል ባለመልክ ተቀናጅተው የሚገኙበት ሰነድ ነው።

የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ (Textbook)፡- በመርሀ-ትምህርቱ መሠረት ተዘጋጅቶ መምህራንና ሠልጣኞች በጋራ የሚጠቀሙበት ለደሴና ለደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የሚያገለግል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ነው።

ሥልጠና (Training)፡- 12ኛ ክፍልን አጠናቀው የተመለመሉ ተማሪዎች ለአንድ ዓመት የቋንቋ ክህሎትና የማስተማር ዘዴ ትምህርት እየተሰጣቸው ለአንደኛ ደረጃ መምህርነት የሚዘጋጁበት ፕሮግራም።

ሥርዓተ ትምህርት (Curriculum)፡- በትምህርት ፍልስፍና ላይ ተመስርቶ የሚካሄድ ማንኛውም ዓይነት በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚሰጡ ፕሮግራሞችን የያዘ አጠቃላይ የትምህርት ግብ።

ተዛምዶ (Correlation)፡- የሁለት ነገሮችን የመገናኘት ወይም የመለያየት ደረጃ የሚያመለክት ነው።

ዓላማ (Objective)፡- በአንድ የትምህርት ሂደት ውስጥ ተማሪዎች፣ እንዲያሳዩ የሚፈለግባቸውን የባህሪይ ለውጥ ዓይነት የሚያመለክትና አቅጣጫ የሚጠቁም የመርሀ-ትምህርት ክፍል።

ክሂሎች (Skills)፡- አራቱን የቋንቋ ችሎታዎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) የሚገልጽ ጽንሰሃሳብ ነው።

የማስተማር ዘዴ (Teaching Methodology)፡- የተወሰነ ዓላማን ለማስፈጸም የተዘጋጀ የትምህርት ፕሮግራም ለተማሪዎች የሚቀርብበትን መንገድና ስልት የሚያመለክት።

ይዘት (Content)፡- በመርሀ ትምህርት ላይ የሰፈረውን አላማ ለማሳካት ከልዩ ልዩ ምንጮች የተመረጡ ጽንሠ ሀሳቦች፣ ጭብጦች፣ አመለካከቶች ወዘተ. . ለትግበራ ተዘጋጅተው የሚቀርቡበት ክፍል።

ግምገማ (Evaluation)፡- ለተወሰነ ደረጃ ይመጥናል ተብሎ የተዘጋጀ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ መሳካትና አለመሳካቱን የማረጋገጥ ተግባር ነው።

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት (REVIEW OF RELATED LITERATURE)

2.1 የመምህራን ሥልጠና (Teacher Training)

የመምህራን ትምህርት በአውሮፓ በተስፋፋበት ከ1920-1930 ባለው ጊዜ ውስጥ በተማሪዎች ቁጥር መጨመር የተነሳ መምህራንን የሚያሠለጥኑ ተቋሞች በርካታ እንደነበሩ ተገልጿል። (አብርሃም፣ 1986 ዓ.ም) በዚህም የተነሳ የመምህራን ሥልጠና (Teacher Training) እየተስፋፋ መጣ። እንደ ዊደውሰን (1990፡62) አገላለጽ ይህ የትምህርት ፕሮግራም ለተወሰነና ተለይቶ ለታወቀ የትምህርት ፍላጐት ሠልጣኞችን ለማዘጋጀት የሚያስችል የአጭር ጊዜ ዕቅድ ነው። ሥልጠና የአጭር ጊዜ ግብ መምቻና አስቀድሞ ለሚታወቅ ችግር መፍትሔ የሚሆን ፈጣን ዘዴ መሆኑን ምሁራን ይስማሙበታል። ፊኒቺያሮ (1984፡50) ስለዚህ ሲያብራሩ ሥልጠና የረጅም ጊዜ ግብን የሚያመለክት ፕሮግራም ሳይሆን የቅርብ ጊዜ ፍላጐትን በፍጥነት ለማሟላት የሚያገለግል የአንድ አገር የትምህርት ዕቅድ መሆኑን ገልፀዋል። ሌላው ምሁር (ፍሪማን፣ 1986) በመምህርነት ሥራ ለሚሠማራ ሁሉ ሥልጠና አስፈላጊ መሆኑንና ለአንድ አገር የትምህርት ዕድገት ጠቃሚ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ሂል እና ደቢን (1975፡1) እንደሚያብራሩት አንዳንድ ሰዎች ለመምህርነት ተግባር ላቅ ያለ ዝንባሌ አላቸው። ዕውቀታቸውን ለሌላው የማስተላለፍ ችሎታቸው ከፍተኛ ነው። ይሁን እንጅ ችሎታ እያላቸው ተማሪዎቻቸው ትምህርቱን በቀላሉ ሊረዱላቸው የሚችሉበትን ስልት ላይገልጹላቸው ይችላሉ። በሌላ በኩል መጠነኛ ዕውቀት ኖሯቸው የሚያውቁትን ያህል በማራኪ አቀራረብ ለተማሪዎቻቸው የማስተላለፍ ብልሃት ያላቸው ሰዎችም አሉ።

በምሁራኑ አመለካከት ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱም ክፍሎች የሥልጠና እገዛ ያስፈልጋቸዋል። ሥልጠናው ለመጀመሪያው ቡድን የማስተማር ዘዴና ቴክኒክ አጠቃቀምን ሲያሳወቅ ለሁለተኛው ደግሞ የተሟላ ዕውቀት በማስጨበጥና ትምህርቱን ከተማሪዎች ፍላጐት ጋር እንዴት እንደሚያጣጥሙት መንገድን በማሳየት ይጠቅማቸዋል።

2.1.1 በሥልጠና ወቅት ትኩረት የሚደረግባቸው ጉዳዮች

ሂልና ደቢን (1975) " የመምህራን ማሠልጠኛ ኮርስ " በሚለው መጽሐፋቸው ለመምህርነት ሙያ የሚዘጋጁ ሠልጣኞች ሊያተኩሩባቸው የሚገቡ ሶስት መሠረታዊ ነጥቦችን እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

- የተሻለ የማስተማር ዘዴን ከነባር መምህራን ልምድ መቅሰም፣
- በትወራ የሚነገራቸውን በሚገባ መረዳት፣
- የተመለከቱትንና የተነገራቸውን በተግባር ላይ ማዋል፣

ሁለቱ ምሁራን አጽንዖት የሰጡት ጉዳይ ሠልጣኙ በሙያው የመርካት ስሜት እንዲያድርበት ለዚህ የሚያበቃ ተስማሚ ኮርስ ሊዘጋጅለት የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ኮርሱ ሲዘጋጅ ለሥልጠናው ሂደት ተስማሚ ይሆን ዘንድ በምን ላይ ትኩረት መደረግ እንዳለበት ኬኔዲ (1979 ፡ 42) እንደሚከተለው አመልክተዋል፡፡

1- የሠልጣኙ ደረጃ፣ ልምድና ፍላጐት እንዲሁም የሥልጠናው ሁኔታ አስቀድሞ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡
2- የሥልጠናው ሂደት መምህሩ የተለያዩ ተግባራትን በበላይነት እንዲያከናውን የሚመራ ሳይሆን የአማካሪነት ሚና እንዲጫወት ማስቻል ይኖርበታል፡፡
3- ሠልጣኙ የቋንቋና የተወሰነ የትምህርት ዘርፍ መምህርነት ችሎታን አጣምሮ እንዲይዝ ማስቻል ተገቢ ነው፡፡
4- ሠልጣኙ ለትምህርት ዘርፉ የተዘጋጀውን መጽሐፍ ሲገለገል በራስ የመተማመን ችሎታውን መጠቀም እንዲገባው ማስቻል አስፈላጊ ይሆናል፡፡
5- የቋንቋውን ልዩ ልዩ ዘርፎች (ሰዋስው፣ ቃላት፣ ክሂሎች ወዘተ.) ሲያስተምር ከቋንቋ ተግባቦታዊ ባህሪይ አንፃርና በሳይንሳዊ መንገድ እንዲመለከት ይጠበቅበታል፡፡
6- በመጻሕፍት ዝግጅት መረጣና ማሻሻል ተግባር ላይ ሠልጣኙ በግልም ሆነ በቡድን ተሳትፎ ማድረግ ያስፈልገዋል፡፡
7- አግባብነት ያለው የማስተማር ዘዴን ለምሳሌ የቡድን ሥራ፣ የግልሥራ፣ ወዘተ. መለማመድ ይኖርበታል፡፡

ሻው (1987 ፡ 12) በተጨማሪ አንድ ሠልጣኝ ሊቀዳጃቸው የሚገባ ሥነ-ትምህርታዊ ክሂሎች (Pedagogical skills) ትምህርትን ስለማቀድ፣ መልመጃዎችን ስለማዘጋጀት፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ስለማዘጋጀትና ፈተናዎችን በአግባቡ ስለማውጣት ወዘተ. መሆን እንዳለባቸው ያሳስባሉ። እንደምሁሩ አገላለጽ ለሠልጣኙ የሚቀርብለት የኮርስ ዓይነት ከሥልጠና በኋላ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር መጣጣም ይኖርበታል። ማሪያኒ (1987 ፡ 75-76) የተባሉትም በበኩላቸው በመምህርነት ሥልጠና ወቅት የሚሰጥ ትምህርት መምህሩ ከሚያስተምረው ትምህርት በተጨማሪ ሠልጣኙ ሊኖረው የሚገባውን የባህሪይ ገጽታ (Profile) ግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለበት ያስገነዝባሉ። ሠልጣኙ በትምህርት ላይ እያለ ሊማራቸው ስለሚገቡ የትምህርት መስኮች ፍሪማን (1989 ፡ 28-33) የሚከተሉትን ነጥቦች አስፍረዋል።

- ዕውቀት (Knowledge)
- ክሂል (Skill)
- ዝንባሌ (Attitude)
- ግንዛቤ (Awareness)

ስትሬቨንስ የተባሉት ምሁርም (1977 ፡ 74-75) መምህራንን ለማፍራት የሚካሄደው የሥልጠና ኮርስ ሶስት የተለያዩ ይዘቶችን ማካተት እንዳለበት አመልክተዋል።

ይዘቶቹም፡- ሀ. የክሂል ክፍሎች (Skill components)
ለ. የመረጃ ክፍሎች (Information components)
ሐ. የትወራ ክፍሎች (Theory Components) ናቸው።

በእርሳቸው አገላለጽ የክሂል ክፍሎች የሚሏቸው የመምህራን የቋንቋ ችሎታ፣ የማስተማር ጥበብ፣ የክፍል አያያዝና የመማር ማስተማር ሂደት ክትትልን ሁሉ ይመለከታሉ። የመረጃ ክፍሎች በሚሏቸው ሥር ደግሞ መርሀ-ትምህርትና ሌሎች የትምህርት መሣሪያዎች እና የቋንቋ ባህሪያትን የሚመለከቱ መረጃዎችን የሚያጠቃልሉ ሲሆን የቋንቋ መምህሩ እነዚህን መረጃዎች የግድ ማወቅ እንዳለበት ያስገነዝባሉ። በትወራ ክፍሎች ሥር የሚጠቀሱት በትምህርት ፍልስፍና፣ በሳይኮሎጅና በተግባራዊ

ሥነልሣን ወዘተ. . መስክ የተካሄዱ ግኝቶች ሲሆኑ ሠልጣኙ ተገንዝቦ ሊጠቀምባቸው እንደሚገባ ያስታውሳሉ፡፡

ሠልጣኞቹ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ከተረዱ የሙያው ባለቤት ለመሆን ብቃት ይኖራቸዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ ስትሬቨንስ (1977) ከመምህራን የሚጠበቁ ችሎታዎችን እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡-

ሀ- የተሟላ የቋንቋ ችሎታ፣

ለ- የማስተማር ቴክኒክና የክፍል አያያዝ ብቃት፣

ሐ- የትምህርቱን ሂደት በአግባቡ የመምራት ችሎታ፣

መ- ስለሚጠቀመበት የትምህርት መሣሪያ በሚገባ ማወቅ፣

ሠ- ቋንቋን ማስተማር ከልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች ጋር ያለውን ግንኙነት መረዳት፡፡

ሮጀርስ (1979 ፡ 84) በሥልጠና ሂደት፡ የሚያልፉ ተሳታፊዎች ትኩረት የሚያደርጉበትን ጉዳይ ሲገልጹ፡-

ሀ- ከመነሻው ጀምሮ ለመምህርነት ሙያ ራስን ማዘጋጀት፣

ለ- ሥልጠናውን ከክፍል ውስጥ ትግበራ ጋር ማጣጣም፣

ሐ- የትምህርቱን ይዘት በአግባቡ አደራጅቶ ለተቀባዩ ማቅረብ መቻል፣

መ- የሙያ ፍቅርን በማዳበር እስከመጨረሻው መዝለቅ ወዘተ. . ናቸው፡፡

ብለዋል፡፡

2.1.2 ከሠልጣኙ የሚጠበቁ ግዴታዎች

የመምህሩ ኃላፊነት በአጠቃላይ ሲታይ የትምህርቱን ሥራ ማስተባበር፣ ራሱንም ተሳታፊ ማድረግና በዕውቀት ምንጭነት ማገልገል መሆኑን ሀርመር (1983 ፡ 200-204) ያስረዳሉ፡፡ በሙያው የሰለጠነ መምህር የሚከተሉት ችሎታዎች እንዲኖሩት የሚጠበቅ መሆኑን ብራውንና ሌሎች (1982 ፡ 8) አመልክተዋል፡፡

- የሚያስተምረውን ትምህርት አጣርቶ ማወቅ፣
- የህፃናት አስተዳደግ መሠረታዊ መርሆዎችን መረዳት፣
- ስለ አጠቃላይ ዕውቀት የተሻለ ግንዛቤ መጨበጥ፣
- ስለ ማስተማር ዘዴዎችና ስልቶች በሚገባ ማወቅ፣

- ለመሥያው አዎንታዊ አመለካከት መኖር፣
- የአካባቢውን ፍላጐት በማጤንና የተገኘውን ቁሳቁስ በመጠቀም ትምህርቱን አስማምቶ ለማቅረብ በጐ ፍላጐት ማሳደር፣
- በት/ቤቱ የተሻለ የሥራ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ
- የሚያስችል የመንፈስ ቆራጥነት ስሜት ማሳደር።

የመምህሩ የማስተማር ጥረት በተማሪው ላይ የባህሪይ ለውጥ ለማስገኘት ነው። ተማሪው በዕውቀት እንዲዳብርና በችሎታ እንዲበለጽግ መምህሩ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅበት አብዱረህማን እንዲህ በማለት ያስገነዝባሉ፡-

> መምህራን ሥርዓተ ትምህርቱን በመከተል ሊያስተምሩ የፈለጉትን ትምህርት ያቅዳሉ፣ ያቀዱትንም ለተማሪዎቻቸው ያስተምራሉ። በሚያስተምሩበትም ጊዜ ለትምህርቱ ለተማሪዎቻቸውና ለራሳቸው የሚስማማቸውን የማስተማር ዘዴና የትምህርት መርጃ መሣሪያ መርጠው ይጠቀማሉ። መምህራን በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪዎቻቸውም የየራሳቸውን የመማር ድርሻ እንደየችሎታቸውና እንደየዝንባሌያቸው ያከናውናሉ። . . . . በዚህም የማስተማር-መማር ውህደት ይፈጠራል። (አብዱሮህማን፣ 1985 ዓ.ም ገጽ 1)

ለማስተማር-መማሩ ሂደት መገልገያ የሚሆኑት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጁት ልዩ ልዩ የትምህርት መሣሪያዎች ናቸው። ከነርሱም መካከል ለክፍል ውስጡ የትምህርት ሂደት ትግበራ በመነሻነት የሚያገለግለው ዋናው ሰነድ መርሀ-ትምህርት ነው።

ይህ ጥናት የሚመለከተው የመምህራን ማሠልጠኛ መርሀ ትምህርትን ቢሆንም መምህራንን ለማሠልጠን የሚዘጋጅ መርሀ-ትምህርት አጠቃላዩን የቋንቋ ትምህርት መርህና አሠራር መከተሉ የማይቀር ነው። ስለዚህ ከአጠቃላዩ ወደ ልዩው በማምራት በቅድሚያ ለማናቸውም የቋንቋ ትምህርት የሚያገለግል መርሀ-ትምህርት ምንነት ይገለፃል። በመቀጠል ስለ መምህራን ማሠልጠኛ መርሀ-ትምህርት ዝርዝር ሁኔታ የተለያዩ ምሁራን የሰጡት አስተያየት ይቀርባል።

2.2 <u>የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ምንነት</u>

መርሀ-ትምህርትን ከሥርዓተ-ትምህርት ጋር አንድ እያደረጉ የሚጠቀሙ አገሮች እንዳሉ ስተርን (1984 ፡ 118) ይጠቁማሉ። ይሁን እንጅ ብዙዎቹ ምሁራን በሁለቱ ፅንሰ ሀሳቦች መካከል የትርጉም ልዩነት እንዳለ ይስማማሉ። ኑናን (1988 ፡ 5)

ቫንኤከን በመጥቀስ የሥርዓተ-ትምህርትና የመርሀ-ትምህርትን ልዩነት እንደሚከተለው ገልፀዋል፡፡

<u>ሥርዓተ-ትምህርት</u>፡- ዕቅድን፣ ትግበራን፣ ምዘናንና የትምህርት ፕሮግራም ማስተባበርን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

<u>መርሀ-ትምህርት</u>፡- ከሥርዓተ-ትምህርት ጠበብ ብሎ ይበልጥ የሚያተኩረው በይዘት አመራረጥና አደራጃጀት ላይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ሻው (1987 ፡ 564) ሮበርትሰን የሰጡትን ትርጉም ጠቅሰው እንደሚከተለው አስፍረውታል፡፡

<u>ሥርዓተ-ትምህርት</u>፡- ተግባርን፣ አላማን፣ ይዘትን፣ ሂደትን፣ ግምገማንና ማንኛውንም ዓይነት በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚሰጡትን ፕሮግራሞች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡

<u>መርሀ-ትምህርት</u>፡- ግን የሥርዓተ ትምህርት ዕቅድ ማስፈጸሚያ ሲሆን በይዘት አደረጃጀት ላይ ያተኩራል በማለት ገልፀውታል፡፡

የምሁራኑ ሀሳብ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ ሥርዓተ-ትምህርት ስለ አጠቃላይ የትምህርት ግብ ሰፋ ያለ ትንታኔ የሚያካትትና በርካታ ጉዳዮችን በውስጡ የያዘ ፅንሰ ሀሳብ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ (አለን፣ 1984፣ ዱቢንና አልሸቴይን፣ 1986፣ ኑናን፣ 1988፣ ሻው፣ 1987)

የመርሀ-ትምህርትን ክልል የሚወስኑት ምሁራን (ስተርን፣ 1984፣ ኑናን፣ 1988፣ ያልደን፣ 1987) ከሥርዓተ-ትምህርት የሚወጣ፣ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል፣ የመማር-ማስተማር ክንውን በመሆኑ ይስማማሉ፡፡

ምሁራን የመርሀ-ትምህርትን ትርጉም በየበኩላቸው እንደሚከተለው ያብራራሉ፡፡ ያልደን (1987፡72) "መርሀ-ትምህርት ማለት ለአንድ የተወሰነ የትምህርት ፕሮግራም ይዘት መወሰን (መምረጥ) ነው" ሲሉ በሌላ በኩል ኑናን (1988 ፡ 6) መርሀ-ትምህርትን በትምህርት ይዘት ብቻ ሳይወሰን በሌሎች የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴዎች ሊገለጽ የሚችል ነው በማለት ትርጉሙን ሰፋ አድርገው ይመለከቱታል፡፡ ዱቢንና አልሸቴይን (1986 ፡ 28) ስለዚሁ ጉዳይ የበኩላቸውን ትንታኔ ሲሰጡ መርሀ-ትምህርት የኮርስ ቢጋር ወዘተ. . እየተባለ ቢጠራም በመርሀ ደረጃ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

1- ተማሪው ኮርሱን ከጨረሰ በኋላ ምን እንዲያውቅ ይፈለጋል ?

2- በኮርሱ ወቅት በትምህርትነት የሚቀርበው ነገር ምንድን ነው ?

3- የሚሰጠው ትምህርት ምን ዕድገት ያሳያል ምን ያህል ጊዜስ ይወስዳል ?

4- ትምህርቱ እንዴትና በምን ዓይነት ስልት ይገመገማል ?

እስካሁን የተገለፁትን ማብራሪያዎች በማገናዘብ የመርሀ-ትምህርትን ትርጉም በተመለከተ ቀጥሎ የተገለፀው የዱቢንና ኦልሸቴይን ብያኔ አብዛኛውን ሀሳብ የሚያካትት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

> መርሀ-ትምህርት በሥርዓተ-ትምህርት ላይ ተመስርቶ የሚነደፍ፣ የትምህርት ፍልስፍና በተግባር የሚገለጽበት፣ የመማር-ማስተማር መሠረታዊ ጉዳዮች በዝርዝር የሚቀርቡበትና ለትምህርት አላማዎች ግብ መምቻነት የሚያገለግል ተግባራዊ መመሪያ ነው (1986 : 37)

ኑናን (1991 : 6) መርሀ-ትምህርት የትምህርቱን አካሄድ የሚያመለክት፣ አወቃቀሩም ከቀላል ወደ ውስብስብ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከሚታወቀው ወደማይታወቀው የሚሄድና የመምህሩንና የተማሪውን ሚና የሚያሳይ መሆኑን ይነግሩናል፡፡

ከዚህ በመቀጠል ለመምህራን ሥልጠና የሚያገለግል መርሀ-ትምህርት ምን ዓይነት ቢሆን እንደሚመረጥ በጉዳዩ ላይ የጻፉ ምሁራን አስተያየት ይቀርባል፡፡

2.2.1 <u>መምህራንን ለማሠልጠን የሚያገለግል መርሀ-ትምህርት</u>

ሙርዶክ (1996 : 49) ዎተርስን በመጥቀስ እንዳሰፈሩት ለመምህራን ማሠልጠኛ የሚያገለግል የቋንቋ መርሀ-ትምህርት የሠልጣኞችን ፍላጐት ማሟላት ይችል ዘንድ እንደ አመቺነቱ ሥራ ላይ የሚውል (Flexible) ሆኖ መቀረጽ አለበት፡፡ እንደ ሙርዶክ አገላለጽ ለመምህራን ማሠልጠኛዎች የሚዘጋጀው መርሀ-ትምህርት ከሌላው የሚለየው በዝግጅቱ ወቅት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ለሥነ ዘዴው (Methodology) መሆኑ ነው፡፡

ይህም ሥነ ዘዴ በምን ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> ተፈላጊው የመርሀ-ትምህርት ዓይነት በሠልጣኞች የሚከናወን፣ በርካታ ተግባራትን የያዘና ሠልጣኝ-መራሽ ሥነ ዘዴን የሚከተል መሆን አለበት። በዚህ መንገድ የተማረ ሠልጣኝ በትምህርቱ ሂደት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ባህሪያዊ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ይታመናል።(መርዶክ፣ 1996፡49)

ለመምህራን ሥልጠና የሚዘጋጅ መርሀ-ትምህርት ከሌላው ከሚለይባቸው ባህሪያት አንዱ ለማስተማር ዘዴ የላቀ ድርሻ የሚሰጥ መሆኑን በሥርዓተ ትምህርት ኢንስቲትዩት የተዘጋጀ ጽሑፍ ያስረዳል። "የመምህራን ትምህርትና የሥልጠና ሥርዓተ-ትምህርት" በሚል ርዕስ ለወርክሾፕ የተዘጋጀው ይኸው ያልታተመ ጽሑፍ (1997 ፡ 25) በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች የማሠልጠኛ መጻሕፍት ይዘት ውስጥ የማስተማር ዘዴ ድርሻ ከ60% ማነስ እንደሌለበት ያስገነዝባል።

ዳቢድ ክሮስ (1987 ፡ 73-75) የተባሉት ምሁርም ለመምህራን ማሠልጠኛ የሚዘጋጅን መርሀ-ትምህርት ባህሪያት እንደሚከተለው በቅደም ተከተል አስቀምጠዋል።

1- መርሀ-ትምህርቱ መዘጋጀት ያለበት የሠልጣኞችና የመምህራን ፍላጐት ከታወቀ በኋላ እንጅ ሊስማማ ይችላል በሚል ግምት መሆን የለበትም። በፍላጐታቸው መሠረት ከተዘጋጀ ሥነ ትምህርታዊ (Pedagogical) ጠቀሜታው የጐላ፣ ለህብረተሰቡ ተስማሚ የሆነና ተፈላጊውን ውጤት የሚያስገኝ ይሆናል።

2- የአቀራረብ ስልቱንም በተመለከተ ተማሪዎቹ እንዳይቸገሩ የገለባው ይዘት ከውይይት ጋር ተቀናጅቶና በአብዛኛው በተግባራዊ ክንውን ተደግፎ በተብራራ ሁኔታ መተላለፍ አለበት።

3- በመርሀ-ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ መካከል ውስጣዊ ቁርኝት እንዲኖር ያስፈልጋል።

4- ሠልጣኞቹ ከመርሀ-ትምህርቱ ዕንሰ ሐሳብ ፍጹም ዝንፍ ማለት የለባቸውም ሳይባሉ ለፍላጐታቸው ተስማሚ የሆኑና የአካባቢ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች በመጨመር በመሠረታዊ ክሂሎች ላይ ያተኮረ ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል።

5- በመርሀ-ትምህርቱ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ለሥነ ትምህርት (Pedagogy) ሲሆን የቋንቋ ክህሎት መዳበር በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ መሆን አለበት።

ቶኒ ቢርደንና ሌሎች (1992 ፡ 28) ስለ መምህራን ሥልጠና ሲያብራሩ መርሀ-ትምህርቱ ለሠልጣኞች መሠያዊ ብቃት (Professional Competence) ለመቀዳጀት ሊረዳቸው እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ መምህራንን ለማፍራት የሚበጅ የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ይዘት ከሚያካትታቸው ጉዳዮች መካከል ክሮስ (1987 ፡ 76) የሚከተሉትን ዘርዝረዋል፡፡

- ሰዋስው (መዋቅር)፣
- ቃላት፣
- የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ)፣
- የማስተማር ክሂሎች፣
- የትምህርት ዕቅድ፣
- ግምገማ ወዘተ. .

በአጠቃላይ ለመምህርነት ሥልጠና የሚዘጋጅ መርሀ-ትምህርት ለመሠያዊ ክሂሎች (Professional Skills) እና ለትምህርት ዘርፉ (Subject Area) ዕውቀት መጐልበት የሚረዳ፣ ለተግባራዊ ክንውን ትኩረት የሚሰጥ መሆን እንዳለበት ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ይስማሙበታል፡፡

2.2.2 የቋንቋ መርሀ-ትምህርት አካሎች

ቋንቋ ውስብስብ ይዘት ያለው በመሆኑ በትምህርትነት ሲሰጥ በልዩ ልዩ ንኡሳን ክፍሎች ተሸንሽኖ መቅረብ ይኖርበታል (ኑናን፣ 1991)፡፡ ይህንን ለማድረግ የሚቻለውም በመጀመሪያ የትምህርት ዓላማ፣ ይዘት፣ የማስተማር ዘዴና የጊዜ አመዳደብ ወዘተ. . የሚይዘውን መርሀ-ትምህርት በመንደፍና በዚያ ላይ ተመርኩዞ የመማሪያ መጻሕፍትን በማዘጋጀት ነው፡፡ ዱቢንና አልሸቴይን (1991 ፡ 28) እንደሚያስረዱት የቋንቋ መርሀ- ትምህርት ቀጥሎ በተጠቀሱት ነጥቦች ሊገለጽ ይችላል፡፡

- ከትምህርቱ በኋላ ከተማሪው የሚጠበቀው ምንድን ነው ?
  (የአላማን አስፈላጊነት ያሳያል)
- ምን እናስተምራለን ?
  (አላማውን ለማስፈጸም የሚያስችል ይዘት መኖር እንዳለበት ያመለክታል)

- ለምን ያህል ጊዜ እናስተምራለን ?
  (እንደ ቋንቋው ትምህርት አላማ ስፋትና ጥልቀት ምን ያህል ጊዜ እንደሚያስፈልግ ለማወቅ ያስችላል)
- እንዴት እንገመግማለን ?
  (የተፈለገው ውጤት መገኘት አለመገኘቱን ለማረጋገጥ የሚቻልበትን የምዘና አስፈላጊነት ያመለክታል።)

ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት መሠረታዊ ነጥቦች መገንዘብ የሚቻለው በማንኛውም የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ አላማ፣ ይዘት፣ የመማር-ማስተማር ክንውንና ግምገማ የማይቀሩ አካሎች መሆናቸውን ነው። ይሁን እንጅ የዚህ ጥናት አድማስ የተወሰነ በመሆኑ እያንዳንዱን ክፍል በጥልቀት ለማየት አይሞክርም።

2.2.2.1 የመርሀ-ትምህርት አላማ(Objective of a Syllabus)

በማንኛውም አይነት የትምህርት ሂደት በመጀመሪያ ሊታሰብ የሚገባውና ተፈላጊው ጉዳይ አላማ ነው። የሚጠበቀውንም ውጤት የሚወስነው አላማው ነው። ስለትምህርት ዓላማዎች ጠቀሜታ በርካታ ነጥቦች ይጠቀሳሉ። የትምህርት ይዘትን ለመምረጥ፣ የመማሪያ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀትና ለማሻሻል፣ ለተፈላጊው የትምህርት ዘርፍ ተገቢውን ትኩረት ለመስጠት፣ የትምህርት ቅደም ተከተልን ለማስያዝና የትምህርት ሂደትን በአግባቡ ለመገምገም አላማ አስፈላጊ እንደሆነ ታባን በመጥቀስ አበበ በቀለ (1974 ፡ 23) አስፍረዋል። የትምህርት አላማን ጠቀሜታ (ሀችንሰንና ዎተርስ፣ 1987፣ ዱቢንና ኦልሽቴይን፣ 1990) አስገንዝበው በአዘገጃጀቱ ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ ገልፀዋል።

የትምህርት አላማዎች አጠቃላይና ዝርዝር ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ተማሪው ስለ ትምህርቱ በአጠቃላይ ማወቅ የሚገባውን ጉዳይ የሚያሳዩት አጠቃላይ አላማዎች ሲሆኑ ዝርዝር አላማዎች ደግሞ ተማሪው በአንድ የትምህርት ርዕስ ላይ በዝርዝር እስከመጨረሻው የሚጨብጣቸውን ነጥቦች፣ በእነርሱም አማካይነት የሚያሳያቸውን ለውጦች ይጠቁማሉ። (ዱቢንና ኦልሽቴይን፣ 1986 ፡ 24)

2.2.2.1.1 አጠቃላይ አላማ (General objective)

አጠቃላይ አላማ በየክፍል ደረጃው ከሚገኝ ተማሪ ምን እንደሚጠበቅና ተማሪውም ቀጥሎ ወደየትኛው ደረጃ እንደሚሸጋገር ያመለክታል። በዚህም መሠረት አጠቃላይ አላማዎች እንዴት እንደሚቀረጹ ታባ (1962 ፡ 197) ያብራራሉ።

1- አጠቃላይ አላማዎች ተማሪው ምን እንዲያደርግ ይጠበቅበታል ? ምን መሥራት አለበት ? የሚሉትን እንጂ የመምህሩን ተግባር ማመልከት የለባቸውም። መምህሩ የድርጊቱ መሪ ወይም ቀያሽ እንጂ ድርጊት ፈጻሚ አይደለም።

2- አጠቃላይ አላማዎች የሥራ መጨረሻን (ውጤትን) ማመልከት እንጂ የትምህርት ርዕሶች በመዘርዘር የሚያበቁ መሆን የለባቸውም፤ ድርጊትን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል።

3- አንድ አጠቃላይ አላማ ነጠላ ውጤትን ብቻ እንዲያስገኝ ሆኖ መጻፍ አለበት። በአንድ አላማ በርካታ ውጤቶች ከተጠቆሙ ተግባራዊነታቸው አስቸጋሪ ይሆናል።

4- አጠቃላይ አላማዎች ግልጽ ሆነው መጻፍ አለባቸው። ግልጽነት የሌለው አላማ የማይጨበጥ ስለሚሆን ለተግባራዊነት አመቺ አይሆንም።

5- አጠቃላይ አላማዎች ዝርዝር ጉዳዮችን ከመግለጽ ይልቅ አጠቃላይ ጉዳዮችን እንዲያሳዩ ሆነው መጻፍ አለባቸው።

6- አጠቃላይ አላማዎች ከትምህርት ሂደት ይልቅ ውጤትን ማሳየት ይኖርባቸዋል በማለት ዘርዝረዋል።

2.2.2.1.2 ዝርዝር አላማ (Specific objective)

አጠቃላይ አላማዎች ከተነደፉ በኋላ በመቀጠል ዝርዝር አላማዎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ዝርዝር አላማዎች ተማሪው በተጨባጭ የሚያውቃቸውን ዝርዝር ጉዳዮች የመጠቆም ድርሻ ይጠበቅባቸዋል። በዚህም ሂደት በአጠቃላይ አላማው መሠረት ትኩረት የሚያሻው የይዘት ክፍል በዝርዝር አላማው ላይ በግልጽ መታየት አለበት። ታባ (1962) በዝርዝር አላማ ውስጥ ትኩረት የሚደረግባቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡-

1- በትምህርቱ መጨረሻ በተማሪው ላይ የሚታውን የባህሪይ ለውጥ ዓይነት ማመልከት፣
2- የትምህርቱ ሂደት የሚከናወንበትን ሁኔታ ማሳየት፣
3- የትምህርቱ ሂደት በምን መንገድ እንደሚገመገም በግልጽ መጠቆም።

ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ዋና ዋና አገልግሎቶች አሏቸው፡-

1- ትምህርቱ ምን ምን መያዝ እንዳለበት ይመራሉ።
2- በምን ላይ ትኩረት መደረግ እንደሚገባ ይጠቁማሉ።
3- ምን አይነት የትምህርት ይዘት መመረጥ እንዳለበት ያሳውቃሉ።
4- በየትኞቹ የማስተማር ልምዶች ላይ ትኩረት መደረግ እንዳለበት ያመለክታሉ።

ለዚህም ነው ዝርዝር አላማዎች ሲዘጋጁ በጣም ግልጽ እንዲሆኑ የሚጠበቀው። ለማንኛውም የትምህርት ፕሮግራም አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎች ከተነደፉ በኋላ ቀጣዩ ተግባር በአላማው የተገለፁትን የትምህርት ግቦች ከዳር ሊያደርሱ የሚችሉ ይዘቶችን ማዘጋጀት ይሆናል።

2.2.2.2. የመርሀ-ትምህርት ይዘት (Content of a Syllabus)

ለማንኛውም የቋንቋ መርሀ-ትምህርት የሚመረጡ ይዘቶች ሁሉ የጋራ ባህሪይ በመርሀ-ትምህርቱ ላይ የሰፈረውን አላማ ተግባራዊ ለማድረግ መቻላቸው ነው። ከተለያዩ ምንጮች የተመረጡ ፅንሰሀሳቦች፣ መመሪያዎች፣ ህጎች፣ ጭብጦችና አመለካከቶች ወዘተ. . የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያግዝ መልክ ተዘጋጅተው ሲቀርቡ ይዘቶች ይሰኛሉ። ኑናን (1988) ይዘት ተማሪው እንዲማረው የሚፈለገው የቋንቋ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት መሆኑን ያስገነዝባሉ።

ለቋንቋ ትምህርት የሚመረጡ ይዘቶችን ክሂል ሰጭ (Skill-oriented) እና እውቀት ሰጭ (Knowledge-oriented) በማለት በሁለት ክፍል መመልከት እንደሚቻል ዱቢንና ኦልሽቴይን (1986 :50) አመልክተዋል። ክሂል ሰጭ ይዘት ሲባል በቋንቋው ለመጠቀም የሚያስችሉ ክሂሎችን ማለትም ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍን ያካተተ ነው። የተወሰኑ ምሁራን ለቋንቋ ትምህርት የሚዘጋጅ ይዘት አራቱንም

ክሂሎች በተመጣጠነ ሁኔታ መያዝ አለበት ይላሉ። (ዊድወሰን፣ 1978 ፡ 57፤ ሁዋይት 1988 ፡ 68-69)። ቀደም ባለው ጊዜ በቋንቋ ትምህርት ይዘት አራቱም የቋንቋ ክሂሎች ተመጣጥነው መገኘት አለባቸው ቢባልም በተግባር ሲታይ ግን በቋንቋ ትምህርት በብዛት የሚቀርበው የማንበብና የመጻፍ ልምምድ ሲሆን በቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ደግሞ ሰፊ ቦታ ይዞ የሚገኘው የመናገር ክሂል ልምምድ እንደሆነ ይገልጻሉ።
ብራይትና ማክግሪጐር በቋንቋ ትምህርት ይዘት ውስጥ የክሂሎችን አስፈላጊነት አስገንዝበዋል።

> ሰው ቋንቋን የሚማረው በቀሪ የህይወት ዘመኑ በሙሉ ሊጠቀምበት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ ማስተማር ያለብን ዕውቀትን ሳይሆን ክሂልን ነው። እነዚህ የቋንቋ ዘርፎች እኛ ለተማሪዎች የምናስተምራቸው ወይም የምናከናውን ሳቸው ጉዳዮች አይደሉም። ክሂሎችን ማዳበር የሚቻለው በልምምድ ነው። ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስ ተምሩት በመለማመድ ነው። በእንደዚህ ያለው ሂደት መምህሩ በብዛት ከመናገር ይልቅ በማዳመጥና በማንበብ ላይ ጊዜውን ማጥፋት አለበት። ተማሪዎች ከርሱ በላይ እንዲናገሩ እንዲጽፉና እንዲያነቡ የሚረዳ ሊሆን ይገባዋል።
> (ብራይትና ማክግሪጐር፣ 1978 ፡3)

በነዚህ ምሁራን አመለካከት በይዘት ዝግጅት ረገድ የቋንቋ ክሂል ከቋንቋ ዕውቀት የበለጠ ትኩረት ይሰጠው ቢባልም የቋንቋ ዕውቀት ጭራሽ አያስፈልግም ማለት አይደለም። የዕውቀት ሰጭ ይዘት መግባት ለመምህራኑ ጠቃሚ መሆኑን የሚያብራሩ አሉ። (ብራይትና ሌሎች፣ 1982 ፡42)። ለዚህም ከሚሰጡት ምክንያቶች መካከል ዕውቀት ክሂሎችን ለማስተማር እንደ መነሻ በመሆን ያገለግላል የሚል ነው።

እንደ ዌስት (1960) እና ካኒንግወርዝ (1984) አስተሳሰብ ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ማለት የዕውቀትና የክሂሎች ቅንጅት ነው። በአጠቃለይ ሲታይ እንደ ትምህርቱ አላማና እንደሚፈለገው ውጤት የትምህርት አቅጣጫዎች ይለያዩ እንጂ ሁለቱም ይዘቶች በቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍት ውስጥ መገኘታቸው ጠቃሚነት እንዳለው ይታመንበታል። ሊተኮርበት የሚገባው ሌላው ተግባር በመጻሕፍቱ ውስጥ የሰፈሩትን ይዘቶች ለተማሪዎቹ የማስተላለፉ ጉዳይ ነው። ይህም ትምህርቱ ለተቀባዮቹ የሚቀርብበትን መንገድና ስልት ይመለከታል።

2.2.2.3 የማስተማር-መማር ዘዴ (Teaching-Learning Methodology)

በመርሀ-ትምህርት ዝግጅት ውስጥ አላማ ከተነደፈና አላማውን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችል የትምህርት ይዘት ከተዘጋጀ በኋላ ቀሪው ተግባር ክንውን ነው። ስተርን (1984) ክንውን በአጠቃላይ ትምህርት እንዴት ? የሚለው ጥያቄ የሚመለስበት መሆኑን ያስገነዝባሉ። ይህም የእንዴትነት ጥያቄ የሚመለሰው የማስተማሪያ ዘዴን፣ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና የትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀምን፣ ለትምህርት የተሰጠውን ጊዜና የመማሪያ ክፍሉን ሁኔታ ወዘተ. . በማጥናት መሆኑን ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ ሲታይ ክንውን አንድን መርሀ-ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ የትምህርት ይዘት፣ የታቀደውን አላማ ለማስገኘት እንዲችል ለተማሪዎች የሚቀርብበት መንገድ ነው። በዚህ ውስጥ ሊጠቀስ የሚችለው ዋናው ጉዳይ ምን ዓይነት የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ እንጠቀማለን ? የሚለው ጥያቄ ነው። ለማስተማሪያነት የምንጠቀምበት ዘዴ ተማሪው ቋንቋውን ለምን ተግባር ይማረዋል ? የሚለውን ጥያቄ መሠረት የሚያደርግ ነው። የሚገኘው መልስ የማስተማሪያ ዘዴውንም ለመምረጥ ያገለግላልና።

በቋንቋ ትምህርት ሂደት የማስተማሪያ ዘዴ የውጤታማነት ወይም የውድቀት አቢይ ምክንያት እንደሆነ፣ ትምህርቱም እንዴት እንደሚሰጥ የሚወስነው ዘዴው መሆኑን ማኪ (1965 : 135) ያስረዳሉ። ከዚህም ጋር በማያያዝ የማስተማሪያ ዘዴውም ሆነ ስልቱ ሊመዘኑ የሚችሉት ሊያሳኩት ከሚገባው አላማ አንፃር እንደሆነና የዘዴው ዓይነትም ለመርሀ-ትምህርቱ ግብ መምቻነት ተስማሚነቱ መገምገም እንዳለበት ያስገነዝባሉ።

የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ደግሞ ትምህርቱ ለተማሪዎች የሚቀርብበትን ሁኔታ ማጤን አስፈላጊ ነው። አንዱ መንገድ የትምህርት ዕቅድን በሚገባ ማዘጋጀትና በሥራ መተርጐም ነው። ኤጅ (1993 : 63) በመምህሩ የሚተገበረው የትምህርት ዕቅድ ሲዘጋጅ፡-

1- የትምህርቱን ዓላማ ማስፈር፣
2- አላማው እንዴት እንደሚተረጐም ማመልከት፣
3- አላማው ለመሳካቱ መገምገሚያውን ማመልከት ይኖርበታል ብለዋል።

በዕቅዱ ውስጥ መምህሩ ምን ሊሠራ እንዳሰበ፣ ተማሪው ምን እንደሚሠራና እያንዳንዱ ክፍል ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ በግልጽ ከተቀመጠ ውጤታማ መሆኑን በቀላሉ ማረጋገጥ እንደሚቻል የተጠቀሱት ምሁር ያብራራሉ። እንደ ሀርመር (1991 : 258) አገላለጽ ጥሩ የትምህርት ዕቅድ ተደጋጋሚ አቀራረብን የሚያስወግድ (Variety)፣ እንደ አመቺነቱ (Flexibility) ሥራ ላይ የሚውል እና ስልቶችንና ተግባራትን አቀናጅቶ የያዘ መሆን አለበት። በኤጅ (1993) አባባል የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት ከፍተኛው ድክመት ከትምህርት ጊዜ ጋር ለመጣጣም አለመቻል ነው።

በአጠቃላይ መምህሩ፣ ማን ይማራል ? ምን ይማራል ? እንዴት ይማራል ? የሚሉትን ለራሱ ጠይቆና በትክክል አስቦ ዕቅዱን ካዘጋጀው ውጤቱ የተቃና እንደሚሆን ምሁራኑ ይገልጻሉ። (የዕቅድ ዝግጅት ናሙናን ከብራውንና ሌሎች፣ 1982 : 139፣ ከዶድ፣ 1970 : 39 ጋር ያገናዝቡ)።

የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማነት ሲነሳ ሊታወስ የሚገባው ሌላው ጉዳይ የትምህርት መርጃ መሣሪያ (Teaching Aid) ሁኔታ ነው። በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተደገፈ ትምህርት እንደዚሁ ከሚሰጠው ይልቅ ይበልጥ ግልጽና የማይረሳ ይሆናል። ይህንኑ አንድ የቋንቋ ምሁር ሲያብራሩ እንደሚከተለው ገልፀውታል።

> አንድ ሰው ከሚሰማው ይልቅ የሚያየውንና የሚያደርገውን ለረጅም ጊዜ ያስታውሳል። በአይን ማየት በቋንቋም ሆነ በማንኛውም ዘርፍ የሚሰጥ ትምህርትን ተጨባጭና ግልጽ ያደርገዋል (ናስር፣ 1972 : 54)።

በመሆኑም የማስተማሪያ ዘዴ ተገቢነት የሚለካው ትምህርቱ የሚቀርብባቸው ልዩ ልዩ መንገዶች ሁሉ ተቀናጅተው አላማውን ግብ ማስመታት ሲችሉ ነው። የተለያዩ የትምህርት አላማዎችን ለማሳካት ደግሞ ተስማሚ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መርጠ መጠቀሙ የተለመደ እንደሆነ ይገለፃል። በዚህም የተነሳ በመማር-ማስተማሩ ሂደት የተፈጠሩ በርካታ የማስተማሪያ ዘዴዎች በልዩ ልዩ ሰነዶች ላይ ይታያሉ። እነዚህ የተለያዩ ዘዴዎችም በጥቅሉ ጥናታዊና ዘመናዊ፣ ወይም መምህሩን ማዕከል ያደረገና ተማሪውን ማዕከል ያደረገ፣ ተማሪን በብዛት የሚያሳትፍና የማያሳትፍ ተብለው ይከፈላሉ። በሪቻርድስና ኑናን (1990 : 132)፣ አብዱሮህማን (1985 ዓ.ም ገጽ 1)፣ ብራውንና ሌሎች (1982 : 39) ከተገለጹት የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎች መካከል የሚከተሉት ለአብነት ያህል ሊጠቀሱ ይችላሉ።

- የገለፃ ዘዴ (Lecture Method)
- የቡድን ውይይት ዘዴ (Group Discussion Method)
- የግል ሥራ ዘዴ (Individualized Teaching Method)
- የድርጊት ዘዴ (Activity Method)
- የጥያቄና መልስ ዘዴ (Question and Answer Method)

በሌላ በኩል ሱሳን (1984 ፡ 34) ሥርዓተ ትምህርትን ሥራ ላይ ለማዋል አመቺ የሚሆኑ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የመጠቀምን ተገቢነት በመግለጽ ዘርዝረዋል፡፡

- የቡድን ሥራ (Group work)
- ነፃ ፕሮጀክት (Free project)
- የክፍል ውይይት (Class discussion)
- የተማሪዎች ሪፖርት (Student Report)
- ሚናን መጫወት (Role play)
- ሠርቶ ማሳየት (Demonstration)
- ቃላዊ ክንውን (Oral Activity) ወዘተ. .

በቋንቋ ምሁራን አመለካከት (ፍሪማን፣ 1986፤ ማርቶን፣ 1982፤ ኑናን፣ 1991) ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጥ ዘዴ ተማሪን ማዕከል ያደረገና ተግባቦታዊ ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፡፡ በላርሰን ፍሪማን (1986 ፡ 128) አገላለጽ መሠረት በተግባቦታዊ ዘዴ ቋንቋን የማስተማር ስልት ውስጥ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- የማስተማሩ ግብ የተማሪውን ተግባቦታዊ ችሎታ ማዳበር በመሆኑ የሥነ ልሣንና የአጠቃቀም ዕውቀት እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡
- የመምህሩ ሚና የክፍሉ አስተባባሪ በመሆን የትምህርቱን ሂደት ማፋጠን እንጅ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆን የለበትም፡፡
- ማንኛውም ነገር የሚከናወነው በተግባቦታዊ ፍላጐት በመሆኑ ተማሪዎች ዋነኞቹ የቋንቋው ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡
- ከቋንቋው ቅርጽ ይልቅ ለአጠቃቀም ትኩረት ይሰጣል፤ ተማሪዎች ለአራቱም የቋንቋ ክህሎት ትኩረት ይሰጣሉ፡፡
- የትምህርቱ ሂደት የተማሪዎችን ችግር ሊያቃልል በሚችልበት መንገድ ይቀየሳል ወዘተ. .

እንደ ብራውንና ሌሎች፣ (1982 ፡3) ኑናን፣ (1991 ፡ 2) መምህሩ አንድን የማስተማሪያ ዘዴ በሚመርጥበት ወቅት ትምህርቱን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀሙ የግድ ነው።

ምሁራኑ ሐሳባቸውን ሲያጠቃልሉም ማንኛውንም የትምህርት አላማ ለማሳካት የሚያስችል ብቸኛ የማስተማሪያ ዘዴ የሌለ መሆኑን ጠቅሰው የትምህርት ሥራን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎችን አቀናጅቶ ከመጠቀም የተሻለ አማራጭ እንደሌለ አስገንዝበዋል። የትምህርቱ ሂደት ከተከናወነ በኋላ ደግሞ አላማው መሳካትና አለመሳካቱ በግምገማ መረጋገጥ ይኖርበታል።

2.2.2.4 ግምገማ (Evaluation)

በመርሀ-ትምህርት ውስጥ ከሚጠቃለሉት አስፈላጊ ክፍሎች መካከል የመጨረሻው ግምገማ ነው። ግምገማ የተፈለገው አላማ ከግብ መድረስ አለመድረሱን መፈተሻ ስልት ነው። በትምህርቱ መጨረሻ በተማሪው ላይ ይታያሉ ተብለው የተዘረዘሩት የባህሪይ ለውጠች መገኘት አለመገኘታቸው በግምገማ ይረጋገጣል። እንዲሁም አንድ የትምህርት ፕሮግራምን ወይም የኮርስ ይዘትን ለማሻሻል ግምገማ አስፈላጊ መሆኑን ሁዋይት (1988 ፡ 48) ክሮንባክን በመጥቀስ አስፍረዋል። በዚህም የግምገማ ሂደት መርሀ-ትምህርቱን ያዘጋጀው ክፍል የነደፈው አላማ በትክክል ተግባራዊ መሆን አለመሆኑን ይረዳል።

ግምገማ በሁለት መንገድ ሊከናወን ይችላል። አንደኛው ተማሪው በትምህርቱ ሂደት ውስጥ እያለ የሚያሳየው የችሎታ ዕድገት በተከታታይ የሚመዘንበት (Formative Evaluation) ነው። ሌላው ደግሞ በትምህርቱ ፕሮግራም መጨረሻ ተማሪው በአላማው የተነደፈውን የችሎታ ደረጃ አግኝቶ ወይም አላገኘ እንደሆነ የሚረጋገጥበት የማጠቃለያ ግምገማ (Summative Evaluation) መሆኑን ሁዋይት (1988 ፡ 145) እና ቄር እና ሮበርትስ (1994 ፡ 14) ገልጸዋል።

ለሁለቱ መገምገሚያ መንገዶች ማጠናከሪያም የምልከታ ግምገማ ማካሄድ አስፈላጊ የሚሆንበት ወቅት ሊያጋጥም ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ እንደቃለ መሕይቅ፣ መጠይቅ፣ወዘተ. .የመሳሰሉት የግምገማ ሥራ ሊከናወንባቸው ይችላል።(አለን፣ 1984 ፡ 71) አመለካከት፣ ፍላጐት፣ አድናቆትና ጥላቻ ወዘተ. . የመሳሰሉትን ለማወቅ ሁለቱንም የግምገማ አይነቶች በማቀናጀት መጠቀሙ አስፈላጊ ይሆናል። የመማር-

ማስተማር አላማ የተዘጋጀውን መጽሐፍ መጨረስ ሳይሆን ተማሪዎች የተወሰነ እውቀት እንዲኖራቸው ክሂሎችን እንዲያዳብሩና አመለካከታቸውን እንዲለውጡ ለማድረግ ነው። በተለይ በአንድ የማሠልጠኛ ተቋም ውስጥ የሚካሄድ ግምገማ፡-

- በኮርሱ አላማ መሳካት፣
- ሠልጣኞች በሚቀስሙት ዕውቀት፣
- በማስተማሩ ዘዴ፣
- በመምህራን ሚና እና
- በፕሮግራሙ ይዘት ወዘተ. . ላይ ማተኮር እንዳለበት ዊር እና ሮበርትስ (1994 ፡ 113-115) አብራርተዋል።

በነዚህና በመሳሰሉት መሣሪያዎች አማካይነት ተማሪው ስለ ትምህርቱ አሰጣጥ ጠቃሚነት ምን እንደሚል በማወቅ ወደፊት ለሚደረጉት ለውጦችና መሻሻሎች ተፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ ይቻላል። (ሁዋይት፣ 1988 ፡ 151)

በመሆኑም ከግምገማ በሚገኘው የመረጃ ምገባ (feedback) ላይ በመመሥረት ድክመትና ጥንካሬን መገምገምና የተሻለ የአሠራር ስልትን መቀየስ በመርሀ-ትምህርት አፈጻጸም የጐላ ድርሻ አለው። የትምህርት አላማን ለማሳካት መርሀ-ትምህርቱን መሠረት በማድረግ የሚዘጋጁ የተለያዩ መማሪያ-ማስተማሪያ መጻሕፍት ይኖራሉ። የመማር-ማስተማር ክንውኑ የሚካሄደውም በእነርሱ መሣሪያነት ነው።

2.3 የቋንቋ መማሪያ (ማስተማሪያ) መጻሕፍት

2.3.1 የተማሪው መጽሐፍ (Student Text)

የቋንቋ መርሀ-ትምህርት ከተዘጋጀ በኋላ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ የሚሆነው በመማሪያ መጽሐፍ አማካይነት መሆኑ ይታወቃል። መጻሕፍት በመርሀ-ትምህርቱ የተመለከተውን ይዘት መሠረት በማድረግ ተዘጋጅተው ተማሪው የሚጠበቅበትን የአስተሳሰብና የአሠራር ለውጥ እንዲያገኝ የሚያግዙ አስፈላጊ መሣሪያዎች ናቸው። የሚከተለው ገለጻም ይህንኑ ያመለክታል።

> የመማሪያ መጻሕፍት፣ ተማሪው ቋንቋን በራሱ ጥረት ለተፈለገው አላማ እንዲጠቀምበት ወደሚያስችል ደረጃ የሚያደርሱ አይነተኛ መሣሪያዎች ናቸው። (ከኒንግወርዝ፣ 1984፡58)

ብራውንና ሌሎች (1982 ፡ 9-10)፣ ቢሎውስ (1961 ፡ 58) መማሪያ መጻሕፍት አንድን የተወሰነ የትምህርት ዓይነት ለማጥናት የክፍሉ ተማሪዎች በሙሉ የሚገለገሉባቸው ጠቃሚና ተፈላጊ መሣሪያዎች መሆናቸውን አስገንዝበዋል።

ምሁራን የመማሪያ-መጻሕፍትን ተፈላጊነት ቢያስገነዝቡም በሌላ በኩል ሁሉም የትምህርት ክንውኖች በመጻሕፍቱ ውስጥ ባሉ ይዘቶች ላይ ብቻ ይወሰናሉ ማለት እንዳልሆነ አሳስበው መጻሕፍት መቆጠር ያለባቸው ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ ከምንጠቀምባቸው አስፈላጊ የትምህርት መሣሪያዎች መካከል እንደ አንዱ መሆኑን አብራርተዋል። (ብራውንና ሌሎች፣ 1982)

ለዚህም ነው መምህራን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሰፈሩትን ዕንሰሀሳቦች ለማስተላለፍ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ትምህርቱን ይበልጥ ተጨባጭና ማራኪ ለማድረግ ብርቱ ጥረት እንደሚጠበቅባቸው ምሁራን የሚመክሩት። ይህንንም ለማሳካት ከተጠቀሱት የተማሪውና የመምህሩ መጻሕፍት በተጨማሪ ሌሎች አዳባሪ መሣሪያዎችን መጨመሩ ጠቀሜታው የጐላ መሆኑን ያስገነዝባሉ።(ዊስት፣ 1960፤ ናስር፣ 1972፤ ማኪ፣ 1978፤ ክኒንግወርዝ፣ 1984) ለመማር-ማስተማሩ ሂደት በመሣሪያነት እንዲያገለግሉ የሚዘጋጁ መጻሕፍት የሚጫወቱት ሚና በተለያዩ ምሁራን የተገለፀ ሲሆን ቢሎውስ (1961) እና ብራውንና ሌሎች (1982) እንዲሁም ሌሎች የቋንቋ ምሁራን ከጠቀሱዋቸው ነጥቦች መካከል ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

- መርሀ-ትምህርቱን በተግባር ለመተርጐም ያስችላሉ፤
- መምህሩ ምን ማስተማር እንዳለበት ይገልጻሉ፤
- ለተማሪው ጥናት በመነሻነት ያገለግላሉ፤
- አስፈላጊና መሠረታዊ ዕውቀትን ያስጨብጣሉ፤
- ለተማሪው የንባብ ልምድ መሠረት ይሆናሉ፤
- ለሚሰጠው ትምህርት በቋሚ መዘክርነት ያገለግላሉ፤
- ተፈላጊውን የአመለካከትና የባህሪይ ለውጥ ያስገኛሉ ወዘተ. .

በምሁራኑ አባባል መሠረት መጻሕፍት ከዕይታ የትምህርት መሣሪያዎች ሁሉ የላቁና በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። በመጻሕፍቱ ውስጥ የተጠቀሱት ይዘቶች ለመማር-ማስተማሩ ሂደት መሠረት እንደመሆናቸው መምህሩ የራሱን ልምድና ዕውቀት ለማገናዘብ የሰፈሩትን ቁምነገሮች ወደ ተማሪው የሚያስተላልፍበትን ስልት ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል።

2.3.2 የመምህሩ መምሪያ (Teacher's Guide)

ስለ መጻሕፍት ሲነሳ አይነተኛ መሣሪያ የሆነው የመምህሩ መምሪያ የሚዘነጋ አይደለም፡፡ መምሪያው የመምህሩን ዝርዝር የአሠራር ሂደት በመጠቆም ረገድ የበኩሉ ድርሻ አለው፡፡ የመምህር መምሪያ መምህሩ ምን ማስተማርና እንዴት ማስተማር እንዳለበት በግልጽ የሚጠቁም መሆን እንዳለበት ይጠቀሳል፡፡

ዌስት የተባሉት ምሁር ስለዚህ ጉዳይ የሚከተለውን አስተያየት ሠንዝረዋል፡፡

> መምህሩ የሚያስተላልፈው መጽሐፉን በትክክል ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲችል ስለትምህርቱ አካሄድ ዘርዘር ያለ ትንታኔ የሚሰጠውና አቅጣጫ የሚጠቁመው የመምህሩ መምሪያ እንደሚያስፈልገው የታወቀ ነው፡፡ (ዌስት፣ 1960 ፡ 23)

የተማሪው መጽሐፍም ሆነ የመምህሩ መምሪያ የተፈለገውን አገልግሎት ለመስጠት ይችሉ ዘንድ በሚዘጋጁበት ጊዜ የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ ሀችንሰንና ዎተርስ (1987) ሪቻርድስ (1987) ይዘረዝራሉ፡፡

- በመርሀ-ትምህርቱ ላይ መመሥረት አለባቸው፣
- የክብደት ደረጃቸው በየምዕራፉም ሆነ በአጠቃላይ መጠበቅ አለበት፣
- የትምህርቱን ቅደም ተከተል ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፣
- ይዘታቸው የሚስብና በተግባር የሚተረጐም ሊሆን ይገባል፣
- ትክክለኛና ተገቢ የቋንቋ አጠቃቀም እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፣
- በቋንቋ ዘርፎች መካከል ያለው ቅንጅት አጥጋቢ መሆን አለበት፣

በመማሪያ መጽሐፍ ይዘት ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎች ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የክሂሎች መዳበር የሚመጣው ደግሞ እያንዳንዱን ክሂል በተናጠል ሳይሆን በቅንጅት (Inegrated) መልክ በማለማመድ ነው፡፡ ካሮልሪድ (1984 ፡ 70) የሚከተለውን ሐሳብ ሠንዝረዋል፡፡

> የተቀናጀ ክሂል በአብዛኛው ሥራ ላይ የሚውለው በመካከለኛና ከዚያ በላይ ለማስተማር በተዘጋጀ ሠልጣኝ ነው፡፡ ይህ ትክክል ቢሆንም አስፈላጊነቱ ግን ለዚህ ደረጃ ብቻ አይደለም፡፡ ለመጀመሪያ ደረጃ ሠልጣኝም ያንኑ ያህል አስፈላጊ ነው፡፡

በደራሲዋ አመለካከት ከሥልጠናው መነሻ ጀምሮ ለአራቱ ክሂሎች በተመጣጠነ መልክ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው። ሂል እና ዶቢን (1979 ፡ 4) ለመምህርነት ለሚዘጋጁ ሠልጣኞች ከማስተማር ዘዴው ጐን ለጐን አራቱን ክሂሎች የሚያዳብር ትምህርት መሰጠት እንዳለበት ያሳስባሉ። እንደ ካሮልሪድ (1984 ፡ 73) የክሂሎች ቅንጅት አስፈላጊነት፡-

1- የማስተማር-መማር ሂደት ተከታታይነት እንዲኖረው ይረዳል።
2- አራቱንም ክሂሎች የሚያካትት ተግባር በተለያየ መልክ ሲቀርብ ተማሪዎችን ለማነቃቃት ይረዳል።
3- የተቀናጀ የክሂሎች አጠቃቀም ስልት ለውጤት የሚያበቃ ግብአት ለመኖሩ ማረጋገጫ ነው።
4- የተቀናጀ የክሂሎች ስልት በእውነተኛ የተግባቦት ተግባር ላይ ተመስርቶ የቋንቋ ችሎታን ለማዳበር ይረዳል።
5- የተቀናጀ የክሂሎች ስልት ተማሪዎች የቀሰሙትን የቋንቋ ትምህርት ለመከለስና በተለያየ መንገድ የተሰጠውን የማስተማር ዘዴ ለማጤን ይረዳል።
6- የክሂሎች ቅንጅት ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖርና በተለያዩ ይዘቶችና ሞዴሎች አማካይነት በሚገባ ለመጠቀም የሚያስችል ዕድል ለተማሪዎች ይሰጣል።
7- የተቀናጀ የክሂሎች አሰጣጥ ስልት በተወሰነ ክሂል ደከም ለሚሉ ተማሪዎች ሊረዳ ይችላል።
8- አራቱም የቋንቋ ክሂሎች ጐን ለጐን የሚዳብሩ ከሆነ የተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታ መሻሻልን ያሳያል።

ማክዶና እና ሻው (1993 ፡ 206) ኑናንን በመጥቀስ እንዳመላከቱት ለውጤታማ የቋንቋ ትምህርት በመልመጃዎች አማካይነት ልምምድ በማድረግ የተቀናጀ ክሂልን ማዳበር መፍትሄ መሆኑን ጠቁመዋል።

ቋንቋ በባህሪው ውስብስብ በመሆኑ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት ለማዘጋጀት ሲታሰብ ይህንን ባህሪውን በመረዳት አላማን መወሰንና የሚሰጠውን ትምህርት መመጠን እንደሚገባ ኑናን (1991 ፡ 6) ያስረዳሉ። መማሪያ መጻሕፍት የተፈለገውን አላማ ግብ መምቻ ይሆኑ ዘንድ በሚዘጋጁበት ወቅት የሚከተሉትን ባህሪያት ማሟላት እንደሚገባቸው ስትሬቨንስ (1977 ፡ 27) ገልፀዋል።

1- እውነተኛ (Realistic)፡- በመምህራንና ተማሪዎች በትክክል ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ፣ ትምህርት ሰጭና በቀላሉ የሚገኙ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡

2- ተገቢ (Relevant)፡- ለተማሪዎች እድሜ፣ አላማና ደረጃ ተስማሚ መሆን አለባቸው፡፡

3- አስደሳች (Interesting)፡- የተለያየ አቀራረብ ኖሯቸው ተማሪዎችን የሚስቡና የሚማርኩ ሊሆኑ ይገባል፡፡

4- አበረታች (Encouraging)፡- ተማሪውን ለትምህርቱ የሚያነቃቁ ዕውቀቱን የሚያጐለብቱ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡

5- ተደጋጋፊ (Compatible)፡- ከማስተማር ስልቱና ከተማሪው አመለካከት ጋር የሚጣጣሙና በሚገባ የተቀነባበሩ መሆን አለባቸው፡፡

መምህራን ስለ መጻሕፍት ያላቸው አመለካከት ተመሳሳይ አለመሆኑን ግራንት (1989 : 6-9) አብራርተዋል፡፡ እንደ ምሁሩ አቀራረብ መምህራንን በአመለካከታቸው መሠረት በሶስት ምድብ ከፍለዋቸዋል፡፡

- የመጀመሪያዎቹ የመማሪያ መጽሐፉን የማይሠሩበትና የራሳቸውን መጽሐፍ አዘጋጅተው ቢጠቀሙ ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆኑ የሚያምኑ ናቸው፡፡
- በሁለተኛ ረድፍ የተመደቡት ደግሞ የተዘጋጀ የማስተማሪያ መጽሐፍን አስፈላጊነት አጠንክረው የሚያምኑና ከዚያ ውጭ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡
- በሶስተኛ ደረጃ የሚታዩት ደግሞ ከሁለተኛው ምድብ ጋር በመጠኑ የሚቀራረቡ ሆነው በተዘጋጀው መጽሐፍ የሚጠቀሙ ግን ደግሞ ለዚያ ተገዥ ያልሆኑ ወይም በዚያ የማይወሰኑ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

ሀርመር ደግሞ በመማሪያ መጻሕፍት ላይ የሚያጋጥሙ ድክመቶችን ሲጠቁሙ የሚከተሉትን ነጥቦች አስታውሰዋል፡፡

- የተለያዩ የማስተማር ስልትን ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ አለመሆን፣
- ለያንዳንዱ ተማሪ ዳራና ገጠመኝ የሚስማሙ ሆነው አለመገኘት፣
- የክሂልና የተግባር ይዘትን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አለመጠበቅ

ጥቂቶቹ መሆናቸውን ገልፀው ጥሩ የሚባሉት መጻሕፍት በመምህራንና እውቀቱና ችሎታው ባላቸው ባለሙያዎች የተዘጋጁ መሆናቸውን አመልክተዋል። (ሀርመር፣ 1991 ፡ 257-258) ፋረልና ሄንማንም በበኩላቸው ለዝግጅቱ ቀዳሚውን ሚና የሚይዙት ልምድ ያላቸው መምህራን እንደሆኑ ገልፀው የሌሎች ባለሙያዎች ተሳትፎም አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል። በሁለቱ ምሁራን አመለካከት የመማሪያ-ማስተማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ችሎታና የዝግጅት ልምድ ያላቸው እንዲሁም ቋንቋውን በጥልቀት የሚያውቁ መሆን ይገባቸዋል። (ፋራልና ሄንማን፣ 1989 ፡ 45)

በአጠቃላይ ሲታይ ግን ፍጹም የሆነ የማስተማሪያ (መማሪያ) መጽሐፍ ማግኘት ቢያስቸግርም (ግራንት፣ 1989 ፡8) ለመነሻ የሚሆን የተዘጋጀ መጽሐፍ የመጠቀሙ አስፈላጊነት የሚታመንበት ነው።

2.4 የመርሀ-ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍ ግንኙነት

መርሀ-ትምህርት ተግባራዊ ሊሆን የሚችል የመማር-ማስተማር ክንውን ማሳያ የሥርዓተ-ትምህርት አካል መሆኑ ተገልጿል። ተግባራዊነቱ የሚተረጐመው ደግሞ በመማሪያ (ማስተማሪያ) መጻሕፍት አማካይነት መሆኑ ይታወቃል። ስለሆነም በመርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጻሕፍት መካከል የሚኖረው ግንኙነት ሁኔታ ለትምህርቱ ውጤት መሳካት የራሱ የሆነ ገንቢ ወይም አፍራሽ ሚና ይኖረዋል።

በመርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጻሕፍት መካከል ሊኖር ስለሚገባው ተዛምዶ የተለያዩ ምሁራን የየበኩላቸውን ሐሳብ ሰጥተዋል። እንደ ምሁራኑ አገላለጽ ለመማሪያ መጽሐፍ መሠረት የሚሆነው መርሀ-ትምህርቱ ነው። መማሪያ መጻሕፍት በመርሀ-ትምህርቱ ላይ የሰፈሩትን አላማዎች ለመተርጐም በሚያስችል ሁኔታ ተዘጋጅተው ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል። ሪቻርድስ (1987 ፡ 21) የመርሀ-ትምህርትና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ግንኙነት በሚከተለው ሁኔታ ገልፀውታል።

> ለመማር-ማስተማሩ ሂደት ቀዳሚው ተግባር የመርሀ-ትምህርት ዝግጅት ነው። ከዚያ በኋላ በመርሀ-ትምህርቱ አላማ መሠረት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ተዘጋጅተው በመምህራንና ተማሪዎች አማካይነት ሥራ ላይ ይውላሉ። የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ መምህሩ ምን እንደሚያስተምርና ተማሪዎቹም እንዴት እንደሚማሩ መሣሪያዎችም እንዴት ሥራ ላይ እንደሚውሉ ያመለክታሉ።

የመማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር የቅርብ ተዛምዶ ሊኖረው እንደሚገባና ተዛምዶ ከሌለው ግን ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል ካኒንግወርዝ (1984)፣ ግራንት (1989) በየበኩላቸው ገልፀዋል። ስለሆነም የመርሀ-ትምህርቱ አላማ የመማሪያ መጽሐፉን ይዘት እንደሚወስነው ከምሁራኑ ማብራሪያ መረዳት ይቻላል።

የመማሪያ መጽሐፍ ሲዘጋጅ የሚመሠረተው በመርሀ-ትምህርቱ አላማ ላይ በመሆኑ አላማውን ተግባራዊ ሊያደርግ ካልቻለ በሁለቱ ሰነዶች መካከል ያለው ግንኙነት የላላ መሆኑን ያመለክታል። የዚህም ውጤት በትምህርቱ ስኬታማነት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ለመረዳት ይቻላል። ዱቢንና አልሽቴይን (1990 : 29) የመርሀ-ትምህርትና የመማሪያ መጽሐፍን ግንኙነት አስመልክተው ሲያብራሩ ሁለቱ መሣሪያዎች ሊጣጣሙ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። እንደ ሁለቱ ምሁራን ሐሳብ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የሰፈሩት ይዘቶችና የማስተማር ዘዴዎች በመማሪያ መጽሐፉም ውስጥ መንፀባረቅ ይኖርባቸዋል። ይህም ሁኔታ የሁለቱን መሣሪያዎች መመሳሰል ያመለክታል። ምሁራኑ ሁለቱ የቋንቋ ማስተማሪያና መማሪያ መሣሪያዎች የማይነጣጠሉ መሆናቸውን አስረድተዋል።

> የማስተማሪያ መሣሪያዎችን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች
> የመማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር መጣጣም
> ወይም መስማማት እንደሚገባው ማረጋገጥን እንደ
> ዋነኛ ሥራቸው አድርገው መውሰድ አለባቸው።
> (ዱቢንና አልሽቴይን፣ 1986 : 168)

መርሀ-ትምህርት ምን ማስተማርና እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ስለሚጠቁም መማሪያ መጽሐፉ በዚያ ላይ ካልተመሠረተ የመማር-ማስተማሩን ሂደት በሥርዓት መምራት አስቸጋሪ መሆኑን ምሁራኑ ያስገነዝባሉ። የመርሀ-ትምህርቱ ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በትክክል ካልሰፈረ አንድ የተወሰነ አላማን ማሟላት አለመቻሉን ያመለክታል።

የመስኩ ባለሙያዎች እንደሚሉት በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ ለተማሪዎች የሚመጥኑና ተገቢነት ያላቸው አላማዎች ተመርጠው በግልጽ ከሰፈሩ በኋላ ግብ ማስመቻ የሚሆኑ ተስማሚ ይዘቶች ይመረጥላቸዋል። ይህ ተግባራዊ የሚሆነው ደግሞ በመማሪያ መጽሐፍ አማካይነት ነው።

በሌላም በኩል መርሀ-ትምህርት ተፈላጊው አላማ ተፈጻሚ መሆኑን ልናረጋግጥበት የምንችልበት አንዱ መንገድ ሲሆን ይህም በመማሪያ መጽሐፉ አማካይነት እንደሚገለጽ ሪቻርድስ (1987 : 25) ያብራራሉ።

ከላይ በዝርዝር ከቀረበው የተለያዩ ምሁራን አስተያየት መረዳት የሚቻለው የመማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን ገጽታ ቁልጭ አድርጎ ሊያሳይ በሚችል ሁኔታ ተዘጋጅቶ መቅረብ እንዳለበት ነው። ከዚህ በመነሳት፡ መማሪያ መጻሕፍትን መገምገም የሚቻለው በመርሀ-ትምህርቱ መስተዋትነት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። የተሟላ የቋንቋ ትምህርት ለማካሔድም የሁለት ሰነዶች ተጣጥሞ መዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል።

2.5 የመጻሕፍት ግምገማ

የግምገማ አስፈላጊነት አንድ ነገር ለተወሰነ አላማ ምን ያህል ተስማሚ ነው ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ነው። ፍጹም ጥሩ ወይም መጥፎ የሚባል ነገር ባለመኖሩ በግምገማ ጊዜ ሊታይ የሚገባው የተስማሚነቱ ደረጃ መሆኑን ሀችንሰንና ዎተርስ (1987 ፡ 96) ያስረዳሉ።

እንደ ዱቢንና ኦልሽቴይን (1986 ፡ 167) አገላለጽ የቋንቋ ትምህርት በመምህራን አማካይነት ግልጽና ተጨባጭ ሆኖ ለተማሪዎች የሚተላለፈው በመጻሕፍት አማካይነት ነው። ስለሆነም በሥራ ላይ ያሉ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ በየወቅቱ ግምገማ ሊካሄድባቸው ይገባል። በመጻሕፍት ግምገማ ወቅት ሊተኮርባቸው ስለሚገቡ ነጥቦች የተለያዩ ምሁራን በርካታ መመዘኛዎችን ያሰፍራሉ፡ (ዶድ፣ 1970፡ ሉዊ፣ 1977፡ ዊሊያምስ፣ 1983፡ ሀችንሰንና፣ ዎተርስ፣ 1987፡ ግራንት፣ 1989)

ምሁራኑ ከዘረዘሯቸው ነጥቦች መካከል ለአብነት ያህል የሚከተሉት ተጠቅሰዋል።

- መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ የሚያሟላ መሆኑ፣
- የመርሀ-ትምህርቱ ይዘቶች በሙሉ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መጠቃለላቸው፣
- የመጽሐፉ ይዘት ወቅታዊነት፣
- የይዘቶች አደረጃጀት ተገቢነት፣
- በይዘቱ ውስጥ የተለያዩ የቋንቋ ክፍሎች መካተታቸው፣
- የክሂሎችና ንዑስ ክሂሎች ተመጥኖ መቅረብ፣
- ለተማሪዎች ፍላጐትና ዝንባሌ ተስማሚ መሆን፣
- ለመምህሩ የማስተማር ዘዴ ያለው ተገቢነት፣
- ወቅታዊ ሥነዘዴን ለመጠቀም አመቺ መሆኑ ወዘተ. . .

ዱቢንና አልሸቴይን (1986 : 28-30) የጠቆሚቸው የሚከተሉት ስድስት ጥያቄዎች በአብዛኛው የተዘረዘሩት መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ናቸው፡፡

- የመማሪያ መጽሐፉ በማን ተዘጋጀ ?

  ትምህርቱን፣ አካባቢውን፣ የተማሪዎቹን ገጠመኝ፣ ብሎም የማህበረሰቡን ባህልና ፍላጐት የሚያውቁ ባለሙያዎች ካላዘጋጁት ችግር ይኖርበታል፡፡

- የመማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትመህርቱ ጋር ይጣጣማል ?

  በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱት ጉዳዮች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ካልተንፀባረቁ ድክመት አለበት ማለት ነው፡፡

- የመማሪያ መጽሐፉ ለተማሪዎችና ለመምህራን የተለያዩ አማራጮችን ይሰጣል ?

  አማራጮቹ የማስተማር ስልት፣ ቅደም ተከተልን የመማር-ማስተማር ክንውንና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ካልተሟላ ጉድለት ይኖርበታል፡፡

- በመጽሐፉ ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸው ክሂሎች የትኞች ናቸው ?

  የክሂሎቹ አቀራረብ ተናጠላዊ ነው ወይንስ ቅንጅታዊና ተደጋጋፊ? የክሂሎች ቅንጅት መኖሩ ይመረጣል፡፡

- በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ቋንቋውን ለማስተማር ምን ያህል ብቁ ናቸው ?

  በይዘት መምረጫና መገምገሚያ ሲመዘኑ ብቁ ካልሆኑ ውጤቱ የሚጠበቀውን ያህል አይሆንም፡፡

- መምህራንና ተማሪዎች ስለመጽሐፉ ምን አስተያየት አላቸው ?

  አስተያየቱ ተሰብስቦ መተንተን ይኖርበታል፡፡ ይህም ለወደፊቱ የማሻሻል ሂደት ይጠቅማል፡፡

እንደምሁራኑ አባባል በነዚህ ጥያቄዎች መልስ አማካይነት የትምህርቱ አላማ ግቡን አለመምታቱ ከታወቀ ችግሩን ለማስወገድ፡-

- መርሀ-ትምህርቱን፡
- መማሪያ መጽሐፉን፡
- የማስተማር ዘዴውን፡
- የመመዘኛ ስልቱን ወዘተ. .

መፈተሽ ተገቢ ነው፡፡ (ሀችንስንና ዎተርስ፣ 1987 - 152)

ለየትኛውም ደረጃ የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሣሪያዎች በተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። በተግባር ላይ ከዋሉም በኋላ ስለብቃታቸው መገምገምና ጠንካራ ጐናቸው የበለጠ እንዲጐለብት ደካማ ጐናቸው እንዲሻሻል በየወቅቱ ጥናት ሊደረግባቸው ይገባል።

ይህ ጥናትም በዚህ አላማ መሠረት ለደሴና ለደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከመርሀ-ትምህርቱ አላማ አንጻር ይገመግማል።

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴና የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች (METHODOLOGY)

3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በ1987 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ የዋለው የደብረ ብርሃንና የደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ፣ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሟላት ያለውን ብቃት ለመመርመር የተካሄደ ነው።

የአጠናን ስልቱም ገላጭ (Deseriptive) የምርምር ዘዴን የተከተለ ነው። በጥናቱ አላማ መሠረት የተፈለገውን ውጤት ለማስገኘት ስራ ላይ የዋሉት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች የመፃሕፍት ትንተና፣ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ናቸው።

በዚህ ምዕራፍ ሥራ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች፣ የናሙናዎች አመራረጥ፣ የመረጃ አሠባሰብና አተናተን ስልቶች በዝርዝር የቀርባሉ።

3.1.1 የመረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. የአገር አቀፉ የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች መርሀ-ትምህርትና ለደብረ ብርሃንና ለደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች በክልል ደረጃ የተዘጋጀው የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ፣

ለ. በደብረ ብርሃንና በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ውስጥ የሚያስተምሩ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣

ሐ. በሁለቱ የማሠልጠኛ ተቋሞች ውስጥ በ1989 ዓ.ም በትምህርት ላይ የሚገኙ 220 ዕጩ መመህራን፣

መ. በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት ቢሮ፣ በሥርዓተ ትምህርት መምሪያ ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች::

መምህራኑና ሠልጣኞቹ የሚገለገሉባቸውን የትምህርት መሣሪያዎች በቅርበት ስለሚያውቋቸው አስተያየታቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል:: የትምህርት ባለሙያዎቹ ደግሞ የመጽሐፉን ዝግጅት በማስተባበርና በመገምገም ተግባር ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆናቸው በመረጃ ምንጭነት ተፈላጊ ናቸው::

3.1.2 <u>የናሙናዎች አመራረጥ</u>

የጥናቱ ትኩረት የሆነው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ሥራ ላይ የዋለው በደሴና በደብረ ብርሃን የ1ኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ብቻ በመሆኑና በተቋሞቹ ውስጥ ያሉት መምህራን ቁጥር አነስተኛ ስለሆነ ናሙና መውሰድ ሳያስፈልግ ያሉት አራቱም መምህራን በጥናቱ ውስጥ እንዲታቀፉ ተደርጓል::

በክልሉ ትምህርት ቢሮ ውስጥ ካሉት የሥርዓተ ትምህርት ባለሙያዎች (ኤክስፐርቶች) መካከል አንዱ ብቻ በቦታው ላይ የቆዩ ሲሆን ሌሎቹ ግን ለሥራው አዲስ በመሆናቸው የተሟላ መረጃ አይሰጡም በሚል ግምት የአመቺነት ናሙና (Purposeful sampling) በመጠቀም ለነባሩ አንድ ባለሙያ ብቻ ቃለ መጠይቅ ተደርጓል:: ከተለያዩ ሰዎች የሚገኘው ሀሣብ ጠቀሜታ እንዳለው ስለሚገመት ከትምህርት ባለሙያው በተጨማሪ መረጃ የሚሠጥ ሰው ተፈልጐ ነበር:: በዚህም መሠረት መጽሐፉን ካዘጋጁት መምህራን መካከል አንደኛው በአካባቢው ስለተገኙ ቃለ መጠይቁ ቀርቦላቸው ተገቢውን ምላሽ ሠጥተዋል::

በሁለቱም የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ውስጥ ካሉት 1097 ሠልጣኞች መካከል የአጥኚውን አቅምና የጊዜ መጣበብ ሁኔታ በማገናዘብ 1/5ኛውን (20%) በቁጥር 220 የሚሆኑት በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል:: (ሠንጠረዥ 12ን ይመልከቱ)

ከየማሠልጠኛ ተቋሞቹ በተገኘው የዕጩ መምህራን የሥም ዝርዝር መረጃ መሠረት የደብረ ብርሃን ሠልጣኞች አጠቃላይ ቁጥር 557 ሲሆን የዚህም 20% 112 ይሆናል:: ሠልጣኞቹ በ14ክፍሎች ውስጥ የተደለደሉ ሲሆን በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ ሠልጣኞች አማካይ ቁጥር 40 ነው:: የዚህ 20% ደግሞ 8 ይሆናል:: ስለዚህ ከ14ቱም

ክፍሎች ስምንት፣ ስምንት ተማሪዎች ሲወሰዱ ተፈላጊው ቁጥር (14 x 8 = 112) ይገኛል ማለት ነው። ከየክፍሉ ስምንቱን ተማሪዎች ለይቶ ለማውጣት ደግሞ የሥርዓታዊ ናሙና (Systematic Sampling) ዘዴ በመጠቀም ተፈላጊው ቁጥር እስኪገኝ ድረስ ከተራ ቁጥር አንድ በመጀመርና አምስት፣ አምስት ተማሪዎችን በመዝለል ነው። በዚህም መሠረት 40 ሠልጣኞች ባሉበት ክፍል በጥናቱ የሚታቀፉት ተማሪዎች ቁጥር 1 - 6 - 11 - 16 - 21 - 26 - 31 -36 ይሆናል ማለት ነው።

በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም የሚገኙት ሠልጣኞች ቁጥር ደግሞ 540 ሲሆን የዚህ 20% 108 ይሆናል። ሠልጣኞቹ በ12 ክፍሎች ውስጥ የተደለደሉ ሲሆን በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ ሠልጣኞች አማካይ ቁጥር 45 ነው። የዚህ 20% ደግሞ 9 ይሆናል። በየክፍሉ ዘጠኝ፣ ዘጠኝ ተማሪዎች ሲወሰዱ ተፈላጊው ቁጥር (12x9= 108) ይገኛል። ከየክፍሉ ዘጠኙን ተማሪዎች ለማግኘት አሁንም ለዚያኛው ማሠልጠኛ ተቋም የተጠቀምንበትን ሥርዓታዊ የናሙና ዘዴ በመከተል እንደላይኛው ተፈላጊው ቁጥር እስኪገኝ ድረስ አምስት፣ አምስት ቁጥር በመዝለል ይሆናል። (ሠንጠረዥ 1ን ይመልከቱ)

ሠንጠረዥ - 1:- ከየተቋሞቹ በናሙናነት የተመረጡ ሠልጣኞች ዝርዝር

የተቋሙ ስም	የሴክሽን ብዛት	የሠልጣኞች ብዛት			የአንድ ክፍል አማካይ ቁጥር	በናሙናነት የተመረጡ ብዛት		
		ወ	ሴ	ድ		ወ	ሴ	ድ
ደብረ ብርሃን	14	350	207	557	40	70	40	112
ደሴ	12	333	207	540	45	85	23	108
	26	683	414	1097	-	155	64	220

3.1.3 የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች

3.1.3.1 የመርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ

በዚህ ርዕስ ስር ለደሴና ለደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ይዘቶችና የመርሀ-ትምህርቱ አላማዎች ምን ያህል እንደሚጣጣሙ፣ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሳካት ያለውን ብቃት ለመመርመር ጥረት ተደርጓል። የሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች ግንኙነት አምንታዊ

ወይም አሉታዊ ገጽታ ያለው መሆኑን ለመረዳት ተሞክሯል። ለዚህ ያመች ዘንድ በቅድሚያ የመርሀ-ትምህርቱ ዝርዝር አላማዎች፣ ይዘቶች፣ የማስተማር ዘዴዎችና ግምገማዎች ከራሱ ከመርሀ-ትምህርቱ አቢይ የትምህርት አላማዎች ጋር በንፅፅር ታይተዋል።

አቢይ የትምህርት አላማዎች የተባሉት በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው የመምህራን ማሠልጠኛ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ላይ የሠፈሩት ናቸው። (አባሪ 1ን ይመልከቱ)

በሁለተኛ ደረጃ የመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ከመርሀ-ትምህርቱ አቢይ የትምህርት አላማዎች ጋር እየተነፃፀሩ ለያንዳንዱ አላማ ማስፈፀሚያ ተገቢና በቂ መልመጃዎች መዘጋጀታቸውና አለመዘጋጀታቸው ታይቷል። የመልመጃዎቹ ዝርዝር (ሠንጠረዥ 7ን ይመልከቱ) እንደየቅደም ተከተላቸው ቀርበዋል። መልመጃዎቹ የቋንቋ ክሂሎቹንም ሆነ የማስተማር ችሎታን ምን ያህል ለማዳበር እንደሚችሉ በትንተናው ክፍል ውስጥ ተብራርቷል።

የመፃሕፍት ትንተና በሚለው ስር በዋናነት የተተኮረበት ነጥብ የመርሀ-ትምህርቱና የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ግንኙነትን መመርመር በመሆኑ ለዚህ እንዲረዱ በተለያየ መልክ የቀረቡ 10 ሠንጠረገሮች አሉ። የመርሀ-ትምህርቱ አራት ክፍሎች (ዝርዝር አላማ፣ ይዘት፣ የማስተማር ዘዴና ግምገማ) ከመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት አንድ ባንድ ታይቶና በተዛምዶ ቀመር (Correlation Formula) አማካይነት ተሰልቶ ተቀምጧል። የአሠራር ሂደቱን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ክፍል የሳይኮሎጅ ሁለተኛ አመት ተማሪና በቋንቋ ትምህርት ዘርፍ የድህረ ምረቃ ተማሪ የሆኑ ሁለት ባለሙያዎች ገምግመውታል።

በቀመሩ መሠረት የተገኙት ውጤቶች በአባሪ 3 በተገለፀው መሠረት ተርጉመ ዋል። በመጨረሻም በአጠቃላይ የተገኙት ውጤቶች በዝርዝር የተብራሩ ሲሆን ለውጤቱ መገኘት በምክንያትነት የተጠቀሱት ጉዳዮችም ተዘርዝረዋል።

3.1.3.2 መጠይቅ (Questionnaire)

ሀ) ለመምህራን የቀረበ መጠይቅ

በደብረ ብርሃንና በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ውስጥ በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሞላ የተዘጋጀው መጠይቅ 27 ጥያቄዎችን የያዙ አራት ክፍሎች አሉት።

ጥያቄዎቹ ከአሳሽ ጥናት (Pilot Study) የተመረጡ ሲሆን አስተማማኝነታቸውን፣ ግልጽነታቸውንና የቅደም ተከተል አጠባበቃቸውን ለማረጋገጥ ሲባል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ፋኩልቲ (Education Faculty) እና በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል (Ethiopian Language and Literature Department) የሚገኙ ሁለት መምህራን እንዲሁም በድህረ ምረቃ ትምህርት ክፍል የሚከታተል የቋንቋ ተማሪ በድምሩ 3 ባለሙያዎች እንዲገመግሟቸው ተደርጓል።

በመጠይቁ ውስጥ ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል አብዛኛዎቹ በሊከርት የደረጃ ስኬል (Likert rating Scale) መሠረት የተዘጋጁ ሲሆኑ ተጠያቂዎቹ መልስ በሚሠጡበት ጊዜ ገለልተኝነትን ወደሚያመለክተው ወደ መካከለኛው አማራጭ እንዳያዘነብሉ ለመከላከል ሲባል ምርጫዎቹ ከአምስት ወደ አራት ዝቅ ብለዋል።

ክፍል አንድ የመምህራንን የግል ሁኔታ የተመለከቱ ጥያቄዎችን ይዟል። ክፍል ሁለት ደግሞ ስለ ቋንቋው ትምህርትና የማስተማሪያ መሣሪያዎቹ ሥርጭት ወዘተ. . ከመምህራን የሚፈለጉ አጠቃላይ መረጃዎችን ለማወቅ የሚያስችል ነው። ክፍል ሶስት ስለመማሪያ መጽሐፉ ይዘት ሁኔታ የሚጠይቅ ነው። የመጨረሻው ክፍል ደግሞ በሁለቱ ሠነዶች (መርሀ ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ) መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ያተኩራል።

በመጠይቁ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎች በአብዛኛው አማራጭ መልሶችን የያዙና ጥቂቶቹ ደግሞ በጽሑፍ የሚመለሱ ናቸው። ጥያቄዎቹ ከተዛማጅ ጽሑፎች በተገኙ ሀሣቦች ላይ የተመሠረቱ ሲሆን ለሠልጣኞቹ ከቀረቡት ጋር እንዲገናዘቡ ተገቢው ጥረት

ተደርጓል። መጠይቆቹ የታደሏቸው አራቱም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተገቢው ሁኔታ ሞልተው መልሰዋል። (መጠይቁን በአባሪ 5 ይመልከቱ)

ለ/ <u>ለሠልጣኞች የተሠራጨ መጠይቅ</u>

ለሠልጣኞች የተዘጋጀው መጠይቅ ዋና አላማ ስለ አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፋቸው ተስማሚነትና ብቃት የሚኖራቸውን አጠቃላይ አመለካከት ለማወቅ ነበር። ጥያቄዎቹን የመምህራንን መጠይቅ የተመለከቱት ባለሙያዎች አብረው ከገመገሟቸው በኋላ ተሻሽለው ሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

በመጠይቁ ውስጥ ከተካተቱት ጥያቄዎች መካከል ትንተና የተካሄደባቸው 17 ሲሆኑ በሶስት ክፍሎች ውስጥ ተመድበዋል። በክፍል አንድ ፆታን፣ ዕድሜን፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ክፍል ሁለትና ሶስት ደግሞ ሠልጣኞቹ ለአማርኛ ቋንቋ መጽሐፋቸው ያላቸውን አመለካከት በተለያየ መንገድ እንዲገልፁ ታስቦ የተዘጋጁ ናቸው። ይህ ክፍል ስለመጽሐፉ ተስማሚነት፣ የይዘት ብቃት፣ የቋንቋ ደረጃ፣ የመልመጃዎች አዘገጃጀት ወዘተ.. በአጠቃላይ ለወደፊቱ የመምህርነት ሥራቸው ምን ያህል ሊረዷቸው እንደሚችሉ ሀሳባቸውን የሚገልፁበት ነው። ጥያቄዎቹ አማራጭ መልሶችን የያዙ ሲሆን በመጨረሻ ላይ ግን ተጨማሪ አስተያየታቸውን ሠፋ አድርገው የሚያሠፍሩበት ክፍት ቦታ ተዘጋጅቶላቸዋል። ከሠልጣኞች የቀረበው መጠይቅ የያዛቸው ጥያቄዎች እንደ መምህራኑ ሁሉ በተዛማጅ ጽሑፎች ውስጥ በተነሱ ነጥቦች ላይ እንዲመሠረቱ ተገቢው ጥረት ተደርጓል። ቀደም ብሎ በተጠቆመው ዘዴ መጠይቁን ለመሙላት የተመረጡት ሠልጣኞች ለብቻቸው ከተለዩ በኋላ ስለአላማውና አሞላሉ በአጥኚው በቂ ገለፃ ተደርጐላቸው መጠይቁ ታድሏቸዋል። ሠልጣኞቹ ከሞሉ በኋላም በመጨረሻ መጠይቆቹ ተሰብስበው ሲቆጠሩ ከታደሉት 220 ወረቀቶች ውስጥ 216ቱ እንደተመለሱ ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህም በተማሪዎቹ በኩል የሚፈለግባቸውን መረጃ ለማግኘት ያስችላል። (መጠይቁን በአባሪ 6 ይመልከቱ)

3.1.3.3 <u>ቃለ መጠይቅ (Interview)</u>

በዚህ ጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብ በተግባር ላይ ከዋሉት መሣሪያዎች አንዱ ቃለመጠይቅ ነበር። በዚህም ተሣታፊ እንዲሆኑ የታሠበው በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት ቢሮ በሥርዓተ ትምህርት መምሪያ ውስጥ ያሉ የትምህርት

ባለሙያዎች በሙሉ ነበሩ። ሆኖም ዝርዝር ሁኔታውን የሚያውቁት ነባር ባለሙያ አንድ ብቻ ሆነው ተገኝተዋል። በዚህም የተነሳ ጉዳዮን ከመነሻው ጀምሮ ከሚያውቁት ከእኚሁ ባለሙያ ጋር ብቻ የቃለ መጠይቁ ምልልስ ተካሂዷል። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሲባልም መጽሐፉን ካዘጋጁት መካከል ለአንዱ መምህርም የተለየ ቃለ መጠይቅ ቀርቧል።

ቃለመጠይቁ ያስፈለገበት ምክንያት ጥናቱ በዋናነት የሚያተኩረው በክልል ደረጃ በተዘጋጀው የአንደኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ በመሆኑ ይህንን ተግባር በማስተባበር የሚሠሩ ባለሙያዎችና የመጽሐፉ አዘጋጆች አስተያየት ጠቀሜታ ስላለው ነው።

ለመረጃ ሰጭዎቹ የቀረቡት ጥያቄዎች ሌሎቹን መጠይቆች ለገመገሙት ሶስት ባለሙያዎች ተሠጥተው የሐሳብ ልውውጥ ከተደረገባቸውና ማሻሻያ ከታከለባቸው በኋላ ሥራ ላይ የዋሉ ናቸው።

ቃለ መጠይቆቹ እንደ ቅደም ተከተላቸው 8 እና 7 ጥያቄዎችን የያዙ ሲሆን የጥያቄዎቹ ትኩረትም በመማሪያ መጽሐፉ ይዘቶች ብቃት፣ ስለ ሁለቱ ሠነዶች መጣጣም፣ (መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ) በመጻሕፍቱ ላይ ስለሚሠነዘሩ የትምህርት ባለሙያዎች አስተያየት፣ ለመምህርነት ሥልጠና መጽሐፉ ስላለው ብቃት ወዘተ. . ነበር።

የአሠራር ሂደቱን በተመለከተ ጥያቄዎቹ በአጥኚው እየተነበቡ ተጠያቂዎቹ ሀሳባቸውን ሲገልጹ በጽሑፍ እንዲመዘገቡ በማድረግ ነበር። የቃለ መጠይቁን ሂደት በቴኘ ለመቅዳት ሁኔታው አመች ባለመሆኑ ሳይሳካ ቀርቷል። ምዝግብ ቃለ መጠይቁ (Interview transcript) አባሪ 9 እና 10 ላይ ቀርቧል።

3.1.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

3.1.4.1 የመርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ አተናተን

የመርሀ-ትምህርቱ ዝርዝር አላማዎች፣ ይዘቶች፣ የማስተማር ዘዴዎችና ግምገማዎች ከመጽሐፉ መልመጃዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በተዛምዶ ቀመር ተሠልቶ ውጤቱ ተቀምጧል። ውጤቱን ለመተርጐምና የግንኙነቱን ደረጃ ለመለየት እንዲያስችልም የቀመሩ አካሄድ በአባሪ 3 ላይ ተመልክቷል።

3.1.4.2 የመጠይቅ አተናተን

ለመምህራንና ሠልጣኞች የቀረቡትን መጠይቆች ትንተና በተመለከተ የቀረቡት መልሶች በየፊደል ተራቸው ተደርድረውና በቁጥር ተወክለው ወደ መቶኛ ተለውጠዋል። እንደየጥያቄው አቀራረብ ውጤቱን በማየት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልስ መሰጠቱን ከሠንጠረዡ መገንዘብ በሚቻልበት ሁኔታ ሠፍረዋል። በጽሑፍ የቀረቡት መልሶችም ግምት ውስጥ ገብተው አጠቃላይ ትንታኔ ተሠጥቶባቸዋል።

3.1.4.3 የቃለመጠይቅ አተናተን

ለትምህርት ባለሙያውና ለመምህሩ ከቀረበው ቃለመጠይቅ የተገኘው ምላሽ በጽሑፍ ሠፍሮ በአባሪው ላይ ተመልክቷል። ከዚህ የተገኘው ሀሣብም በትንታኔው ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል። ከሁሉም የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች የተገኙት መልሶች ከተተነተኑ በኋላ ወደ አንድ ማጠቃለያ ሐሳብ ያደርሳሉ ተብሎ ይታመናል።

ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ትንተናና ማብራሪያ (ANALYSIS AND DISCUSSION OF DATA)

4.1 የመረጃዎች ትንተና

ይህ ምዕራፍ በተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት የተገኙት መረጃዎች የሚተነተኑበትና የሚብራሩበት ክፍል ነው። የጥናቱ መሠረታዊ አላማ ለደብረ ብርሃንና ለደሴ የ1ኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሟላት ብቃት እንዳለው ለመመርመር መሆኑ ቀደም ብሎ ተጠቅሷል። በዚህ ክፍል የሚቀርበው ትንተናም በጥናቱ መነሻ ላይ የቀረቡትን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል።

1- የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ይጣጣማል ?

2- መጽሐፉ ሠልጣኞችን ለመምህርነት ሙያ በሚገባ ያዘጋጃል ?

3- የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ በአግባቡ የተዘጋጀ ነው? የሚሉት ናቸው፡ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በመርሀ-ትምህርቱ መግቢያ ላይ "ዝግጅቱ መሠረት ያደረገው የዕጩ መምህራንን የቋንቋ ክህሎት ማዳበርና፣ የማስተማር-መማር ዘዴዎችን ማስጨበጥ ነው።" የሚለው አቢይ ሀሳብ በሥራ መተርጉመን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የዚህን አላማ ተፈጻሚነት ለመፈተሽ በመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያነት ጥቅም ላይ የዋሉትን፡-

1- የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ትንተና፣

2- በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና፣

3- በቃለ-መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች ትንተና አድርጉ ወደተገቢው መደምደሚያ ይደረሳል ተብሎ ተገምቷል።

4.1.1 የመርሀ-ትምህርትና የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ትንተና

በዚህ ክፍል የሚቀርበው ትንተና የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ምን ያህል ይጣጣማል ? ግንኙነታቸው የጠነከረ ነው ወይንስ የላላ ? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ነው።

መርሀ-ትምህርቱና የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ የሚጣጣሙ ወይም የማይጣጣሙ መሆናቸውን ለማወቅ የሚቻለው በተወሰኑ መመዘኛዎች አማካይነት በማነፃፀርና የመማሪያዎቹን ግንኙነት በተመለከተ የተገኙ መረጃዎችን ተንትኖ በማሳየት ነው። የግንኙነቱ ደረጃ የሚታወቀውም በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ያሉትን አራት ክፍሎች (ዝርዝር አላማዎች፣ ይዘቶች፣ የማስተማር-መማር ዘዴዎችና ግምገማዎች) ከመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ጋር በተናጠል በማወዳደር ነው። ይህ የአሠራር ሂደት የተዛምዶ ቀመርን በመጠቀም በመጨረሻ ላይ ይቀርባል።

ለትንተናው አመቺ ይሆን ዘንድ አጥኚው የተከተለው የአሠራር ሂደት በቅድሚያ የመርሀ-ትምህርቱን ልዩ ልዩ ክፍሎችና የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች ለየብቻቸው በሠንጠረዥ ማሳየት ነው። ከዚያ በኋላ ሁለቱን በማቀናጀት ተመሳሳይነታቸውንና ልዩነታቸውን በቀላሉ ማስገንዘብ ይቻላል። በዚህም መሠረት በመርሀ-ትምህርቱ የተጠቀሱትን አቢይ አላማዎች መሠረት ያደረጉ የተለያዩ ሠንጠረገሮች እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ሰፍረዋል።

ሠንጠረዥ - 2፡- የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዝርዝር አላማዎች መግለጫ

ተራ ቁጥር	አቢይ የትምህርት ዓላማዎች	የዝርዝር አላማ ዎች ብዛት	%
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	4	16
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	4	16
3	የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም	2	8
4	የሥነ ጽሑፍ ችሎታ መዳበር	4	16
5	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	5	20
6	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ/1ኛ-4ኛ ክፍል/	1	4
7	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም	3	12
8	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም	2	8
	ድምር፡-	25	100

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው በዝርዝር አላማዎች ውስጥ ይበልጥ ትኩረት የተሰጠው በተናጠል ሲታይ ለማስተማር-መማር ዘዴዎች ነው። የዚህ ርዕስ ድርሻ ከሌላው ጋር ሲነፃፀር 20% ነው። ዝቅተኛ ትኩረት የተሰጠው ደግሞ ለትምህርት

መማሪያዎች ትውውቅ ነው። ከተራ ቁጥር 1-4 ያሉት አላማዎች በቋንቋ እውቀትና ክሂል ላይ ያተኮሩ ሲሆን በድምሩ 56% ድርሻ ይዘዋል። ከተራ ቁጥር 5-8 ያሉት በማስተማር-መማር ዘዴዎች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ሲሆኑ ድርሻቸውም 44% ነው። ይህም የሚያመለክተው በማስተማር-መማር ዘዴ ውስጥ የሚመደቡት ነጥቦች ተጠቃለው ሲታዩ ከቋንቋ ክሂልና ዕውቀት ያነሱ ሆነው መገኘታቸው ነው።

የዚህ ጥናት ትኩረት በመርሀ-ትምህርቱ ላይ ባለመሆኑ ከመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ጋር ለሚደረገው ንፅፅር ያመች ዘንድ ከአቢይ አላማዎች አንፃር የዝርዝር አላማዎችን ድርሻ ከማሳየት ውጭ በአላማዎቹ አቀራረጽና ብቃት ላይ ትንታኔ አይሰጥም።

ሠንጠረዥ - 3፡- የመርሀ- ትምህርቱ ይዘቶች መግለጫ

ተራ ቁጥር	አቢይ የትምህርት ዓላማዎች	የይዘቶች ብዛት	%
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	13	19.1
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	10	14.7
3	የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም	6	8.8
4	የሥነ ጽሑፍ ችሎታ መዳበር	4	5.9
5	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	24	35.3
6	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ/1ኛ-4ኛ ክፍል/	4	5.9
7	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም	5	7.4
8	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም	2	2.9
	ድምር፡-	68	100

መግለጫው እንደሚያመለክተው ከቀረቡት ይዘቶች መካከል ከፍተኛ ድርሻ የተሰጠው ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴ የሚለው ነው። በሁለተኛ ደረጃ የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች የሚለው ትኩረት ተሰጥቶታል። በሶስተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች የሚለው ይከተላል።

ከዚህ ሠንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው ከተራ ቁጥር 1-4 የተገለፁት የቋንቋ ዕውቀትና ክሂልን የሚመለከቱት አላማዎች በድምሩ 33 ይዘቶች (48.5%) ሲይዙ በማስተማር-መማር ዘዴዎች ሥር የሚጠቃለሉት ከተራ ቁጥር 5-8 ያሉት ደግሞ በድምሩ 35 ይዘቶች አሏቸው። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 51.5% ይሆናል። ይህ

የሚያስረዳው በአቢይ የትምህርት አላማነት ከተዘረዘሩት ስምንት ነጥቦች መካከል የይዘቱ አብዛኛው ክፍል በማስተማር-መማር ዘዴ ላይ ያተኮረ መሆኑን ነው። ይዘቶቹ በዝርዝር አላማዎቹ ላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በቅደም ተከተል የሚያብራሩ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው።

ሠንጠረዥ - 4፡- የመርሀ-ትምህርቱ የማስተማር-መማር ዘዴዎች መግለጫ*

ተራ ቁጥር	አቢይ የትምህርት ዓላማዎች	የማስተማር-መማር ዘዴዎች ብዛት	%
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	6	11.3
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	2	3.8
3	የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም	4	7.4
4	የሥነ ጽሑፍ ችሎታ መዳበር	6	11.3
5	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	26	49.1
6	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ/1ኛ-4ኛ ክፍል/	3	5.7
7	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም	3	5.7
8	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም	3	5.7
	ድምር፡-	53	100

በሠንጠረዡ መሠረት ከፍተኛውን ቁጥር (49.1%) የያዙት ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች በሚለው አቢይ አላማ ሥር የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ክንውኖች ናቸው። በማስተማር ሥነ ዘዴ ውስጥ የሚጠቃለሉት ከተራ ቁጥር 5 - 8 የተዘረዘሩት ሲደመሩ 66.2% የሚሆነውን ድርሻ ይዘዋል። ቀሪው 33.8% የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከት ነው። በዚህ ክፍፍል መሠረት ለማስተማር ሥነ-ዘዴ የተሰጠው ድርሻ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች ለሚለው የተሰጠው ድርሻ ደግሞ ዝቅተኛ መሆኑ በሠንጠረዡ ላይ ይታያል።

*በሌሎች የቋንቋ መርሀ-ትምህርቶች ውስጥ "ክንውን" የሚባለው ክፍል ይህ ጥናት በሚካሄድበት መርሀ-ትምህርት ላይ "የማስተማር-መማር ዘዴ" በሚል ተተክቷል።

ሠንጠረዥ - 5፡- የመርሀ-ትምህርቱ ግምገማዎች መግለጫ

ተራ ቁጥር	አቢይ የትምህርት ዓላማዎች	የግምገማዎች ብዛት	%
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	2	12.5
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	1	6.25
3	የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም	1	6.25
4	የሥነ ጽሑፍ ችሎታ መዳበር	2	12.5
5	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	7	43.75
6	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ/1ኛ-4ኛ ክፍል/	1	6.25
7	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም	1	6.25
8	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም	1	6.25
	ድምር፡-	16	100

በዚህ ሠንጠረዥ መሠረት ከተራ ቁጥር 1-4 ለተጠቀሱት የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ግምገማዎች የተሰጠው ድርሻ 37.5% ሲሆን ከተራ ቁጥር 5-8 ለተዘረዘሩት የማስተማር-መማር ዘዴዎች የተሰጠው ግን 62.5% መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ሥርጭቱም ሲታይ የማስተማር-መማር ዘዴዎች የላቀ ድርሻ መያዛቸውን ያመለክታል፡፡

ከዝርዝሩ መረዳት እንደሚቻለው ከሌሎቹ የቋንቋ ክፍሎች ጋር ሲወዳደር ለሥነ ጽሑፍ የተሰጠው ድርሻ የበለጠ ነው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች ከሚለውም የላቀ ድርሻ ስለያዘ በግምገማው ላይ ሥነ ጽሑፍን ለሚመለከቱ ነጥቦች ትኩረት እንደተሰጠ ማወቅ ይቻላል፡፡

የመርሀ-ትምህርቱን ክፍሎች የሚመለከቱትን ሶስቱን ሠንጠረዦች ስናጤናቸው (ከሠንጠረዥ 2 በስተቀር) የማስተማር-መማር ዘዴዎች በሚለው አቢይ አላማ ሥር ለተጠቀሱት ነጥቦች ትኩረት ሰጥተዋል፡፡

በመርሀ-ትምህርቱ የክፍለ ጊዜ ድልድል መሠረት (አባሪ 1ን ይመልከቱ) 60% የሚሆነው የዝግጅቱ ክፍል በማስተማር-መማር ዘዴ ላይ ማተኮሩን ስለሚያመለክት በሠንጠረዡ ላይ የታየው ሥርጭት ከዚያ ጋር የሚገናዘብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይሁን እንጂ በየሠንጠረዦቹ የሚታየው የማስተማር-መማር ዘዴዎች ድርሻ ሲታይ በሠንጠረዥ ሁለት

44%፣ በሠንጠረዥ ሶስት 51%፣ በሠንጠረዥ አራት 66.2% እና በሠንጠረዥ አምስት 62.5% በመሆኑ ተመሳሳይ ሥርጭት አይታይበትም።

መርሀ-ትምህርቱንና መማሪያ መጽሐፉን ለማነፃፀር ያመች ዘንድ ከዚህ ቀጥሎ በቅድሚያ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች ከመርሀ-ትምህርቱ አቢይ አላማዎች አንፃር የሚያሳየው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ - 6፡- ለደሴና ለደብረ ብርሀን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች መግለጫ

ተራ ቁጥር	አቢይ የትምህርት ዓላማዎች	የመልመጃዎች ብዛት	%
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	9	22.5
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	5	12.5
3	የሥነ ጽሑፍ ችሎታን ማዳበር	3	7.5
4	ቋንቋን መፈተን	0	0
5	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	20	50
6	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ/1ኛ-4ኛ ክፍል/	0	0
7	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም	1	2.5
8	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም	2	5
	ድምር፡-	40	100

ከዚህ በላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ እንደሚታየው ከአቢይ አላማዎች አንፃር በመጽሐፉ መልመጃዎች ውስጥ ትኩረት የተሰጠው የማስተማር-መማር ዘዴዎችን ለሚመለከቱ ተግባራት ነው። ይህም ከመርሀ-ትምህርቱ የትኩረት ነጥብ ጋር የሚስማማ ነው። የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ ለሚለው ግን በመልመጃዎቹ ውስጥ የሰፈረ ነገር የለም። በሌላ በኩል በመርሀ-ትምህርቱ አላማዎች ውስጥ ያልተጠቀሰ "ቋንቋን መፈተን" የሚል ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ገብቷል። በመልመጃዎቹ ውስጥ ግን ሠልጣኞቹ የሚለማመዱባቸው ጥያቄዎች አልሰፈሩላቸውም። ከዚህ ሌላ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በአላማነት የተጠቀሰው "የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም" የሚለው በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ውስጥ ቦታ አልተሰጠውም።

የተዘረዘሩት ነጥቦች በሁለቱ የትምህርት መማሪያዎች (መርሀ-ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ) መካከል የተወሰነ ልዩነት መኖሩን በግልጽ ያመለክታሉ።
(ስለመልመጃዎቹ ዝርዝር ሁኔታ በሠንጠረዥ 7 ላይ ይመልከቱ)

ሠንጠረዥ - 7:- የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ሥርጭት

ተ ቁ	አቢይ ትምህርት ዓላማዎች	የመልመጃዎቹ አጠያየቅ ስልቶች								
		አንብብ	አስረዳ	አብራራ	ግለጽ	ጻፍ	ተወያዩ	በተግባር አሳይ	ሌሎች	ድምር
1	የቋንቋ መሠረት ሀሳቦች		3	2					4	9
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታ ጠባዮች			2	1	2				5
3	የሥነ ጽሑፍ ችሎታ መዳበር		2	1						3
4	ቋንቋን መፈተን									0
5	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	3						8	9	20
6	የትምህርት መማሪያዎች ትውውቅ /1ኛ-4ኛ									0
7	የቋንቋ መረጃ መሪያዎች አዘገጃጀት		1							1
8	የቋንቃ ትም/ዕቅድ አዘገጃጀ ትና አጠቃቀም						1		1	2
	ጠቅላላ ድምር	3	6	5	1	2	1	8	14	40

የመማሪያ መጻሕፍት የቋንቋ ክሂሎችን የሚያዳብሩት በመልመጃዎቻቸው አማካይነት መሆኑ ይታወቃል። ለትምህርት በተዘጋጁ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎችን ለመገምገም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ እንደሚገባ የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ።

- በመጻሕፍቱ ውስጥ ለየምንባቦቹ በቂ መልመጃዎች ቀርበዋል ?
- የቀረቡት የመልመጃ ጥያቄዎች የቋንቋውን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው ?
- በመጻሕፍቱ ውስጥ የሰፈሩት መልመጃዎች የተለያዩ የጥያቄ ዓይነቶችን የያዙ ናቸው ? (ናታል፣ 1982 ፡ 134)

ከነዚህ ጥያቄዎች አንፃር በሠንጠረዥ 7 ላይ የሰፈሩት የመልመጃ ዓይነቶች ሲገመገሙ ከቀረቡት 40 ጥያቄዎች ውስጥ በቁጥር 11 የሚሆኑት አስረዳና አብራራ

የሚሉ ናቸው። የመልመጃዎቹ አቀራረብም ተመሳሳይነት የሚታይባቸው ከመሆኑም በላይ በቁጥርም አናሳ ናቸው። በ25 ዝርዝር አላማዎች ሥር ለተጠቀሱት 68 ይዘቶች (ሠንጠረዥ 2 እና 3ን ይመልከቱ) ግብ ማስመቻ የተመረጡት 40 የመልመጃ ጥያቄዎች በቂ አይደሉም። ከዚህም በተጨማሪ የአጠያየቅ ስልታቸው አሻሚነት (ambiguity) የሚታይበት ነው።

ለምሳሌ፡- "አብራራ" ለሚለው ትዕዛዝ በቃል አብራርቶ መናገር ሲቻል በጽሑፍም አብራርቶ መመለስ ሌላው መንገድ ነው። የትኛውን ለማለት እንደተፈለገ መለየት አይቻልም።

ከመርሀ-ትምህርቱ አጠቃላይ አላማዎች መካከል አንዱ የሠልጣኞችን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበር ሲሆን ይህ የሚሟላው ደግሞ በሚቀርቡት መልመጃዎች አማካይነት ነው። መልመጃዎቹም አእምሮታዊ (Cognitive) ክሂላዊ (Skill) እና አመለካከታዊ (Attitude) ባህሪያትን በተመጣጠነ ሁኔታ ሊያዳብሩ በሚችሉበት መንገድ ሊዘጋጁ ይገባል።(ብራውንና ሌሎች፣ 1982 ፡ 129)

ከሠንጠረዡ ላይ እንደሚነበበው ግን የቀረቡት መልመጃዎች ከተጠቀሱት ሶስት ባህሪያት መካከል ወደ አእምሮታዊ የሚያደሉ ናቸው። የአጠያየቅ ስልታቸውም መጽሐፉን ብቸኛ ምንጭ በማድረግ አንብቦ በመረዳት ላይ ያተኮሩና የጠያቂና መላሽ ባህሪያትን የሚያዳብሩ እንጂ ሌሎች የማጣቀሻ ጽሑፎችን በመመርመር ሠልጣኞች ግንዛቤያቸውን ይበልጥ እንዲያሰፉ የሚጋብዙ አይደሉም። በዚህም ምክንያት የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች በተናጠል እንኳን ሲታዩ የመርሀ-ትምህርቱን አላማዎች ለማሟላት ብቃት እንደሚጐድላቸው መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ በመቀጠል በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎችና በመርሀ-ትምህርቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች መካከል ያለው ተዛምዶ ይገመገማል። በሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች መካከል ያለውን የግንኙነት ሁኔታ ለማወቅ በያንዳንዱ የመርሀ-ትምህርት አቢይ አላማ አቅጣጫ ላይ ብዛትንና መቶኛን ማስቀመጡ ብቻ አስተማማኝ ስለማይሆን የተዛምዶ ቀመር (Correlation formula) መጠቀም አስፈላጊ ሆኗል። ይህ ቀመር በሁለት ነገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ተስማሚነት ወይም ተጻራሪነት መቀራረብ ወይም መለያየት የሚያሳይ በመሆኑ ለዚህ ንፅፅርም ጠቀሜታ ይኖረዋል በሚል የጥናቱ አዘጋጅ ሥራ ላይ አውሎታል።

በመጀመሪያ ከአቢይ አላማዎች አንፃር የመርሀ-ትምህርቱን ዝርዝር አላማዎችና የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች ግንኙነት ቀጥለን እንመለከታለን::

ሠንጠረዥ - 8:- የመርሀ-ትምህርቱ ዝርዝር አላማዎችና የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ግንኙነት መግለጫ

ተ ቁ.	አቢይ የትምህርት አላማዎች	መርሀ-ትምህርት X	መማሪያ መጽሐፍ Y	X^2	Y^2	XY
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	4	9	16	81	36
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	4	5	16	25	20
3	የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም	2	0	4	0	0
4	ቋንቋን መፈተን	0	0	0	0	0
5	የሥነጽሑፍ ችሎታ መዳበር	4	3	16	9	12
6	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	5	20	25	400	100
7	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ	1	0	1	0	0
8	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት	3	1	9	1	3
9	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት	2	2	4	4	4
	ድምር:-	25	40	91	520	175

በሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር በተዛምዶ ቀመር እንደሚፈተሽ በተገለፀው መሠረት ሥራ ላይ የዋለው የፒርሰን ተዛምዶ ቀመር (Pearson Correlation Formula) ነው:: በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው ለትንተና ያመች ዘንድ መርሀ ትምህርቱ 'X' በሚል ምልክት የተወከለ ሲሆን መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን የሚያመለክተው ደግሞ 'Y' የሚለው ምልክት ነው:: በቀመሩ መሠረት የሁለቱ ግንኙነት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.75 ነው:: (አባሪ 4ን ይመልከቱ)

እንደ ቀመሩ ትርጓሜ ይህ ውጤት ከፍተኛ ግንኙነትን የሚያመለክት ነው:: (የቀመሩን ውጤት አተረጓጎም ከአባሪ 3 ጋር ያገናዝቡ) ይህም በመርሀ-ትምህርቱ ዝርዝር አላማዎችና በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለው ግንኙነት የጠበቀ

መሆኑን ያመለክታል። ሁለቱ መሣሪያዎች ሙሉ በሙሉ ግንኙነት አላቸው ወይም ይጣጣማሉ ለማለት ግን ሌሎቹን ማወዳደሪያዎች ማየት አስፈላጊ ይሆናል።

ሠንጠረዥ - 9፡- በመርሀ-ትምህርቱ ይዘቶችና በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ መግለጫ

ተ ቁ.	አቢይ የትምህርት አላማዎች	መርሀ-ትምህርት X	መማሪያ መጽሐፍ Y	X^2	Y^2	XY
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	13	9	169	81	117
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	10	5	100	25	50
3	የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም	6	0	36	0	0
4	ቋንቋን መፈተን	0	0	0	0	0
5	የሥነ-ጽሑፍ ችሎታ መዳበር	4	3	16	9	12
6	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	24	20	576	400	480
7	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ	4	0	16	0	0
8	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት	5	1	25	1	5
9	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት	2	2	4	4	4
	ድምር፡-	68	40	942	520	668

በመርሀ-ትምህርቱ ይዘቶችና በመጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለው ግንኙነት ከመነሻው ጀምሮ በተከተልነው አሠራር መሠረት በተዛምዶ ቀመሩ ሲሰላ ውጤቱ 0.62 ነው። ዝርዝር አሠራሩ በአባሪ 4 ላይ የተመለከተውን የሚከተል ነው። በአባሪ 3 ላይ በቀረበው አተረጓጎም ይህ ውጤት በሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች መካከል ግንኙነት እንዳለ ያመለክታል። ይሁን እንጅ ግንኙነቱ የጠበቀ ሳይሆን የላላ ወይም የደከመ መሆኑንም መረዳት ይቻላል። ይህም የሚያመለክተው በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ለቀረቡት ይዘቶች ሁሉ በቂ መልመጃዎች አለመዘጋጀታቸውንና በሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች መካከል ልዩነት መኖሩን ነው። በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለው ግንኙነት በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ (Moderate Relation) መሆኑን የቀመሩ ትርጉም በግልጽ ያሳያል።

ሠንጠረዥ - 10፡- በመርሀ-ትምህርቱ የማስተማር-መማር ዘዴና በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለው ግንኙት መግለጫ

ተ ቁ.	አቢይ የትምህርት ዓላማዎች	መርሀ-ትምህርት X	መማሪያ መጽሐፍ Y	X^2	Y^2	XY
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	6	9	36	81	54
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	2	5	4	25	10
3	የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም	4	0	16	0	0
4	ቋንቋን መፈተን	0	0	0	0	0
5	የሥነጽሑፍ ችሎታን መዳበር	6	3	36	9	18
6	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	26	20	676	400	520
7	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ	3	0	9	0	0
8	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት	3	1	9	1	3
9	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት	3	2	9	4	6
	ድምር፡-	53	40	795	520	611

ሠንጠረዡ እንደሚያመለክተው ቀደም ብሎ በተጠቀሰው አሠራር መሠረት በሁለቱ የማስተማሪያ መሣሪያዎች መካከል ያለው ግንኙነት ውጤት 0.65 ነው። በተዛምዶ ቀመሩ ስሌት ትርጉም መሠረት ይህ ውጤት የመካከለኛ ደረጃ ግንኙነትን የሚያመለክት ነጥብ ነው። በዚህ የማወዳደሪያ መስፈርት አኳያ በመርሀ-ትምህርቱ የማስተማር-መማር ዘዴዎችና በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለው ግንኙነት ያልጠበቀ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ - 11፡- በመርሀ-ትምህርቱ ግምገማዎችና በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ መግለጫ

ተ ቁ.	ዐቢይ የትምህርት ዓላማዎች	መርሀ-ትምህርት X	መማሪያ መጽሐፍ Y	X^2	Y^2	XY
1	የቋንቋ መሠረታዊ ሀሳቦች	2	9	4	81	18
2	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	1	5	1	25	5
3	የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም	1	0	1	0	0
4	ቋንቋን መፈተን	0	0	0	0	0
5	የሥነጽሑፍ ችሎታ መዳበር	2	3	4	9	6
6	ቋንቋን የማስተማር-መማር ዘዴዎች	7	20	49	400	140
7	የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ	1	0	1	0	0
8	የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀት	1	1	1	1	1
9	የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት	1	2	1	4	2
	ድምር፡-	16	40	62	520	172

በሠንጠረዡ ላይ የሚታየው መረጃ ተወስዶ በአባሪ 4 አሠራር መሠረት የተዛምዶ ቀመሩ ሲሰላ የተገኘው ውጤት 0.58 ነው፡፡ ይህ ውጤትም በአባሪ 3 በተቀመጠው አተረጓጎም መሠረት የሚያመለክተው ደከም ያለ (በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ) ግንኙነት መኖሩን ነው፡፡ በዚህም መሠረት በመርሀ-ትምህርቱ ግምገማዎችና በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለው ግንኙነት የላላ ወይም ያልጠነከረ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ከአራቱም ሠንጠረዦች ለመገንዘብ የተቻለው በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉና በመርሀ-ትምህርቱ መካከል ያለው ግንኙነት በአብዛኛው በመካከለኛ ደረጃ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ በተዛምዶ ቀመሩ ስሌት መሠረት የግንኙነቱ ውጤት በመርሀ-ትምህርቱ ክፍሎች ቅደም ተከተል አንፃር 0.75፣ 0.62፣ 0.65 እና 0.58 ነው፡፡ የመርሀ-ትምህርቱ ዝርዝር አላማዎችና የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ግንኙነትን የሚያመለክተው የመጀመሪያው ውጤት ብቻ ከፍተኛ ግንኙነትን ሲያመለክት ሌሎቹ የሚያሳዩት ግን መካከለኛ (ደከም ያለ) ግንኙነትን ነው፡፡ ይህም የሚረጋገጠው የሁሉም ስሌቶች ውጤት አማካይ ነጥብ ሲወሰድ 0.65 ስለሚሆንና በቀመሩ ትርጉም መሠረት የመካከለኛ ግንኙነት አመልካች ነጥብ በመሆኑ ነው፡፡

ይህም ማለት በአንድ በኩል በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ከሰፈሩት ይዘቶች መካከል አንዳንዶቹ በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ እንዳልተካተቱ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል የተካተቱትም ቢሆኑ በተሟላ ወይም ከአቢይ የትምህርት አላማዎች ጋር በተመጣጠነ ሥርጭት አለመስፈራቸውን ያሳያል፡፡ ቢዚህም የተነሳ የተዛምዶ መለኪያው የሚያመለክተው ግንኙነት ደከም ያለ ሊሆን ችሏል፡፡ (ምክንያቶቹ በማብራሪያው ክፍል ተገልፀዋል)፡፡

ዱቢንና አልሸቴይን (1986 ፡ 168) በመርሀ-ትምህርትና በመማሪያ መጻሕፍት መካከል ያለው ግንኙነት የጠበቀ ሊሆን እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡ በተዛምዶ ቀመሩ ትርጉም መሠረት ጥናቱ የተካሄደባቸውን መጻሕፍት የግንኙነት ነጥብ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ የተወሰነ ለውጥ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል መነሻ ላይ ለቀረበው የግንኙነት ጥያቄ መርሀ-ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ ግንኙነት ቢኖራቸውም በከፍተኛ ደረጃ የሚጣጣሙ አለመሆናቸውን ጥናቱ መልሷል፡፡

4.1.2 ከመጠይቅ የተገኙ ምላሾች ትንተና

ለደሴና ለደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማዎች የማሟላት ብቃቱን የሚመለከቱ መጠይቆች ለሠልጣኞችና ለመምህራን ታድለው መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከሁለቱ ክፍሎች የተገኙት መረጃዎች ለየብቻ ተለይተው ይተነተናሉ፡፡ በመጠይቆቹ አማካይነት እንዲመለስ የተፈለገው ጥያቄ መጽሐፉ ለመምህርነት ሥልጠና ተስማሚ መሆኑና መሆኑን ለማዳበር መቻሉን የሚመለከት ነው፡፡

4.1.2.1 ከሠልጣኞች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በሠልጣኞቹ የተሞላው መጠይቅ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በነዚህ ሥር ለተካተቱ 17 ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ - 12፡- መጠይቁን የሞሉትን ሠልጣኞች የሚመለከቱ አጠቃላይ መረጃዎች

ተቋም	ጸታ		እድሜ			የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች					ድምር
	ወ	ሴ	15-19	20-24	25-29	አማርኛ	ኦሮምኛ	አገውኛ	አፋርኛ	ሽናሽኛ	
ደ.ብርሃን	69	41	15	91	4	92	7	9	1	1	110
ደሴ	85	21	13	85	8	105	-	1	-	-	106
	154	62	28	176	12	197	7	10	1	1	216

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው መጠይቁን ሞልተው የመለሱት ሠልጣኞች ብዛት 216 ሲሆን ይህም መጠይቁ ከታደላቸው 220 ተማሪዎች መካከል 98.2% ተሳታፊ መሆናቸውን ያሳያል። ከነዚህም መካከል ወንዶቹ 154 ሲሆኑ ሴቶቹ ደግሞ 62 ብቻ ናቸው። የሠልጣኞቹን ዕድሜ በተመለከተም 188ቱ ከ19 ዓመት በላይ ሲሆኑ 28 ሠልጣኞች ብቻ ከ19 ዓመት በታች እንደሆኑ መረጃው ይጠቁማል። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሁኔታም ሲታይ 197 (91.2%) በአማርኛ አፋቸውን የፈቱ ሲሆኑ ከዚያ ውጭ ያሉት 19 (8.8%) በሌሎች ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ናቸው።

<u>ሠንጠረዥ - 13</u>፡- የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን የይዘት ብቃት በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችና የተሰጡ መልሶች መግለጫ።

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	አማራጮች					
		ሀ	%	ለ	%	ሐ	%
1	በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች ለመምህርነት ሥልጠና ተስማሚ ናቸው?	76	35.3	135	62.8	4	1.9
2	በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት የትምህርት ይዘቶች አዳዲስ ግንዛቤን ከማስጨበጥ አንፃር ወቅታዊ ናቸው ?	28	13.1	157	73.4	29	13.5
3	የይዘቶቹ መልእክቶች ግልጽ ናቸው ?	89	41.6	120	56.1	5	2.3

የሠልጣኞቹ መልስ ለአንደኛው ጥያቄ አብዛኛዎቹ 62.8% በመጠኑ ተስማሚ ናቸው ማለታቸውን ያመለክታል። ለሁለተኛው ጥያቄም 73.4% በመጠኑ ወቅታዊ ናቸው ብለዋል። ለሶስተኛው ጥያቄም እንደዚሁ በመጠኑ ግልጽ ናቸው የሚሉት 56.1% ድርሻ ይዘዋል። ይህም የሚያመለክተው ብዙዎቹ ሠልጣኞች በመጽሐፉ ይዘቶች ብቃት መሉ በመሉ መተማመን አለመቻላቸውን ነው። ለይዘቶች ብቃት የመካከለኛ ደረጃ ምዘና መስጠታቸው ፍላጐታቸውን ለማርካት አለመቻላቸውን ይጠቁማል።

<u>መግለጫ</u>፡-

ሀ- መሉ በመሉ

ለ- በመጠኑ

ሐ- አይደለም (አይደሉም)

ሠንጠረዥ - 14፡- ስለ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ የሠልጣኞች መልስ መግለጫ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	አማራጮች							
		ሀ	%	ለ	%	ሐ	%	መ	%
4	ለማስተማሪያነት የተመረጡት ይዘቶች የቋንቋ ደረጃ እንዴት ነው ?	8	3.7	56	26.0	140	65.1	11	5.2
13	የተማራችሁበት መጽሐፍ የተዘጋጀበት የቋንቋ አጠቃቀም ይከብዳል ወይስ ይቀላል ?	14	6.5	75	35.0	109	51.0	16	7.5

ቋንቋን አስመልክቶ በ4ኛ ተራ ቁጥር ላይ ለቀረበው ጥያቄ ትምህርቱ የቀረበበትን የቋንቋ ደረጃ ሲያመለክቱ 65.1% የማይከብዳቸው መሆኑን አረጋግጠዋል። መጽሐፉን በአጠቃላይ ከቋንቋ አጠቃቀም አንፃር እንዲገመግሙት ለቀረበላቸው ለ13ኛው ጥያቄ በሰጡት መልስ በቁጥር 109 (51.0%) ቀላል መሆኑን በድጋሜ ገልፀዋል። ከዚህም መረዳት የሚቻለው በተጠቃሚዎቹ ምርጫ መሠረት መጽሐፉ በቋንቋ ረገድ ለሠልጣኞች ችሎታ የሚመጥን መሆኑን ነው። የሁለቱን ጥያቄዎች መልሶች አንድ ላይ ስናገናዝብ የቋንቃው ደረጃ በጣም ካልከበደ ወይም በጣም ካልቀለለ ተስማሚ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

መግለጫ፡-

ሀ- በጣም ከባድ

ለ- ከባድ

ሐ- ቀላል

መ- በጣም ቀላል

ሠንጠረዥ - 15፡- የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን መልመጃዎች በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ

ተ ቁ	ጥያቄዎች	መልሶች	
		ድምር	%
5	በመጽሐፉ ይዘት ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተሰጠውን ትምህርት ለመረዳት በቂ ናቸው ?		
	ሀ. ሙሉ በሙሉ በቂ ናቸው	27	12.5
	ለ. በመጠኑ በቂ ናቸው	70	32.4
	ሐ. በቂ አይደሉም	119	55.1
6	መልስህ (መልስሽ) በቂ አይደሉም የሚል ከሆነ ምክንያቱ የትኛው ነው ?		
	ሀ. መልመጃዎቹ ግልጽ አይደሉም	3	2.5
	ለ. መልመጃዎቹ በይዘቶቹ ላይ አልተመሰረቱም	13	10.9
	ሐ. የመልመጃዎቹ አጠያየቅ ውሱን ነው	60	50.4
	መ. መልመጃዎቹ በቁጥር አናሳ ናቸው	43	36.2
7	በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በአብዛኛው ትኩረት የሚሰጠውና ልምምድ የሚካሄድበት በየትኛው ተግባር ነው ?		
	ሀ- በመናገር	62	28.9
	ለ- በማንበብ	10	4.7
	ሐ- በመጻፍ	29	13.6
	መ- በሁሉም ክሂሎች	113	52.8

ሠልጣኞች በቋንቋው እንደልብ ለመገልገል ልዩ ልዩ ክሂሎችን ሊያዳብሩ የሚችሉት በመልመጃዎች አማካይነት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመምህራን ማሠልጠኛዎቹ መርሀ-ትምህርት አላማዎች ላይ የተዘረዘሩት ከ1-4 ያሉት ነጥቦች (ከአባሪ 1 ጋር ያገናዝቡ) የሠልጣኞችን የቋንቋ ክሂሎች መዳበር የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይህን ለማድረግ የሚቻለው ደግሞ በመጽሐፉ ውስጥ የተሟላ የመልመጃዎች ዝግጅት አቅርቦ ሠልጣኞችን በማለማመድ ነው፡፡ የመልመጃዎቹን ብቃት ለማወቅ በተራ ቁጥር 5 ላይ ለተጠየቀው የተገኘው ምላሽ በአብዛኛው አሉታዊ ነው፡፡ 119 (55.1%) የሆኑት ሠልጣኞች መልመጃዎቹ በቂ አለመሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ይህም መማሪያ መጽሐፉ በመልመጃዎች ዝግጅት ረገድ ጉልህ ድክመት እንዳለበት ያመለክታል፡፡

6ኛው ጥያቄ በ5ኛው ላይ የተመሠረተ ሆኖ መልመጃዎቹ በቂ ካልሆኑ ምክንያቶቹን እንዲያመለክቱ ተፈልጐ የቀረበ ነው። በዚያም መሠረት በቂ አይደሉም ያሉት ብቻ የበኩላቸውን ሐሳብ በምርጫቸው አማካይነት ጠቁመዋል።

ከመልሱ እንደምንረዳው የመልመጃዎቹ አጠያየቅ ውስንነትና በቁጥር አናሳነት እንደ ዋና ድክመቶች ታይተዋል። እነዚህን ምክንያቶች የሰጡት 103 (86.6%) ስለሆኑ ከፍተኛውን ቁጥር ይዘዋል። በአላማዎቹ የተጠቀሱትን ውጤቶች ለማስገኘት ሠልጣኞቹ የሚለማመዱባቸውና በተግባር የሚያሳዩባቸው በርካታ መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ ሊጠቀሱ እንደሚገባ ያመለክታል።

በተራ ቁጥር 7 የተጠየቀው በሠልጣኞቹ የሚሠሩት መልመጃዎች የተወሰነ ክሂልን በማዳበር ላይ ብቻ ያተኮሩ እንደሆነ ለመረዳት ነበር። ሆኖም በቁጥር 113 (52.8%) የሆኑት መላሾች መልመጃዎቹ በሁሉም ክሂሎች ላይ እንደሚያተኩሩ ገልፀዋል። ከሠንጠረዙ ላይ እንደሚታየው ግን ከሌሎቹ ጋር ሲነፃፀር የመናገር ክሂል የበለጠ ድርሻ እንደተሰጠው መገንዘብ ይቻላል። የማንበብ ድርሻ ደግሞ አነስተኛውን ይዟል።

ሠንጠረዥ - 16፡- የማስተማር-መማር ዘዴን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተገኙ ምላሾች መግለጫ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	አማራጮች					
		ሀ	%	ለ	%	ሐ	%
9	በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቆመሙት የማስተማር ዘዴዎች ለወደፊቱ ተግባርህ(ሽ) ምን ያህል ይጠቅምሃል (ይጠቅምሻል) ?	126	58.9	77	35.9	11	5.2
10	በመጽሐፉ ውስጥ ስለ ትምህርት መርጃ መሣሪያ አጠቃቀም የቀረበው መግለጫ ብቃት አለው ?	34	15.8	136	63.3	45	20.9
11	መጽሐፉ ስለማስተማር ዕቅድ አዘገጃጀት በሚገባ ለመረዳት አስችሎሃል (አስችሎሻል) ?	66	30.8	134	62.6	14	6.6
12	በመጽሐፉ ውስጥ ስለ አንደኛ ደረጃ የመጻሕፍት አጠቃቀም በቂ ሀሳብ አግኝተሃል (አግኝተሻል)?	88	41.1	114	53.3	12	5.6
14	ከመጽሐፉ ባገኛችሁት ሀሳብ መሠረት በቡድንና በግል የመሥራት ልምድን አዳብራችኋል ?	131	60.7	50	23.1	35	16.2

መግለጫ፡-

ሀ- በከፍተኛ ደረጃ

ለ- በዝቅተኛ ደረጃ

ሐ- አይጠቅምም (የለም)

		ድምር	%
8	በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚከናወነው በየትኛው መንገድ ነው ?		
	ሀ- መምህሩ የሚነግሩንን በመቀበል ላይ ብቻ ያተኮረ	7	3.3
	ለ- በእኛ ተሳትፎ ላይ ያተኮረ	13	6.1
	ሐ- በእኛና በመምህሩ ሀሳብ በመለዋወጥ ላይ የተኮረ	86	40.1
	መ- የመምህሩን ገለፃ በማዳመጥና አንዳንድ ጊዜ በመመለስ	108	50.5

በሠንጠረዡ ላይ የሰፈሩት ስድስት ጥያቄዎች ከማስተማር-መማሩ ዘዴ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው። በመጽሐፉ ውስጥ በያንዳንዱ የትምህርት ርዕስ መጨረሻ ገለፃ ማድረግ፣ ማስታወሻ መስጠት ወዘተ. . በሚል አቀራረብ መምህሩ በምን ሁኔታ እንደሚያስተምር የሚጠቁም ክፍል አለ። በመሆኑም በመጽሐፉ መነሻነትና በመምህሩ አቀናባሪነት የቀሰመት የማስተማር ዘዴ ዕውቀት በምን ያህል ደረጃ እንደጠቀማቸው እንዲያመለክቱ ለሚጠይቀው ለ9ኛው ጥያቄ የሰጡት መልስ ሲተነተን በከፍተኛ ደረጃ ያሉት 126 (58.9%)፣ በዝቅተኛ ደረጃ 77 (35.9%) ሲሆኑ አይጠቅመንም በማለት የመለሱት ግን 5.2% ብቻ ናቸው። ይህም ሥልጠናው የሚከናወንበትን የማስተማር ዘዴ እንደሚደግፉት ያመለክታል።

በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ተደግፎ የሚሰጥ ትምህርት የበለጠ ግልጽ፣ የማይረሳና ተጨባጭ ውጤትን እንደሚያስገኝ ናስር (1972:54) ይገልጻሉ። 10ኛው ጥያቄም በዚህ ላይ ያተኮረ ነበር። ስለትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም በመጽሐፉ ውስጥ የቀረበው መግለጫ ምን ያህል ብቃት እንዳለው ለተጠየቁት ሲመልሱ በከፍተኛ ደረጃ ያሉት 34 (15.8%) ብቻ ናቸው። አይጠቅመንም ያሉት በከፍተኛ ደረጃ ይጠቅመናል ከሚሉት የበለጡ ናቸው። አብዛኞቹ ግን 136 (63.3%) በዝቅተኛ ደረጃ እንደጠቀማቸው አመልክተዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በመጽሐፉ ውስጥ የቀረበው ማብራሪያ የተሟላ አለመሆኑን ነው።

የትምህርት ሥራ በዕቅድ መመራት እንዳለበት ኤጅ (1993)፣ ዶድ (1970) እና ብራውንና ሌሎች (1982) መግለፃቸው በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ላይ ተብራርቷል። በተቋሞቹ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል አንዱ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀምን የሚመለከተው ክፍል ነው። ሠልጣኞቹ በተራ ቁጥር 11 ላይ ስለዚሁ ሲመልሱ አብዛኞቹ 134 (62.6%) በዝቅተኛ ደረጃ የሚረዳቸው መሆኑን ነው የገለጹት። 14 (6.6%) የሆኑት ደግሞ ጨርሶ እንዳልጠቀማቸው ነው ያመለከቱት።

ሠልጣኞቹ የሚዘጋጁት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (1ኛ - 4ኛ ክፍል) ለማስተማር መሆኑ ይታወቃል። በሥልጠናውም ወቅት ከ1ኛ ደረጃ የአማርኛ ማስተማሪያ መጻሕፍት (መርሀ-ትምህርት፣ የተማሪው መጽሐፍና የመምህሩ መምሪያ) ጋር ይተዋወቃሉ። ከማሠልጠኛው መርሀ-ትምህርት አላማዎች አንዱ ከመጻሕፍቱ ጋር ትውውቅ እንደመሆኑ በመማሪያ መጽሐፉም ውስጥ ይህንን የሚመለከት ይዘት አለ።

ስለትምህርቱ ይዘት በቂ ዕውቀት ማግኘታቸውን ለመረዳት በተራ ቁጥር 12 ላይ ተጠይቀዋል። 88 (41.1%) በከፍተኛ ደረጃ ሐሳብ አግኝተንበታል ሲሉ አብዛኛዎቹ 114 (53.3%) በዝቅተኛ ደረጃ መረዳታቸውን ገልፀዋል። በዚህ በኩል የሚታየው ድክመት ደግሞ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ በማሟላት ረገድ ያለው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም።

የማስተማር ስልትን በተመለከተ ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል ሠልጣኞች በቡድንና በግል የመሥራት ልምድን የማዳበራቸውን ሁኔታ የሚመለከተው በተራ ቁጥር 14 ላይ የተጠየቀው ይገኝበታል። ሠልጣኞቹ ለዚህ ጥያቄ የአዎንታ መልሳቸውን በደረጃ ሲያስቀምጡ 131 (60.7%) በከፍተኛ ደረጃ ሲሉ፣ 50 (23.1%) በዝቅተኛ ደረጃ ብለዋል። አብዛኛዎቹ በቂ ልምድ ማዳበራቸውን ስለገለጹ ይህም በተራ ቁጥር 9 ላይ ለተጠየቁትና የማስተማር ዘዴው ለወደፊቱ ተግባራችን በከፍተኛ ደረጃ ይጠቅመናል በማለት ከመለሱት ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ ምድብ ውስጥ በመጨረሻ የምናየው በተራ ቁጥር 8 ላይ የተጠየቀውን ነው። በዚህ ጥያቄ ለማወቅ የተፈለገው መምህሩ በመጽሐፉ በመመራት በክፍል ውስጥ የሚጠቀምበትን የማስተማር ዘዴ ነው። በርግጥ መምህሩ በዚህ መንገድ አስተምር ተብሎ በመጽሐፉ ላይ የሰፈረለትን በቀጥታ ላይከተል ይችላል። ሆኖም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመጽሐፉ መጠቀሙ ስለማይቀር መረጃ ማግኘት እንደሚቻል ይገመታል። ሠልጣኞቹ በሰጡት መልስ 115 (53.8%) የመምህሩ ገለፃ እንደሚበዛ አመልክተዋል። የተማሪው ተሳትፎ መኖሩን የጠቆመት 99 (46.2%) ብቻ ናቸው። ይህም በአብዛኛው መምህር-መራሽ (Teacher-Centered) የማስተማር ዘዴ እንደሚካሄድ ያመለክታል። ይህ ሐሳብ ግን ለ9ኛው ጥያቄ ከሰጡት መልስ ጋር የሚጋጭ ይመስላል። በአንድ በኩል መምህር-መራሽ የማስተማር ዘዴ ሥራ ላይ እንደዋለ እየገለፁ በሌላ በኩል ሥልጠናው የሚከናወንበት የማስተማር ዘዴ በከፍተኛ ደረጃ ጠቅሞናል የሚለው ሐሳብ አብሮ አይሄድም። ለዚህም ሊሰነዘሩ ከሚችሉ ምክንያቶች መካከል ሠልጣኞቹ ከተለያዩ የማስተማር ዘዴዎች ጋር ካለመተዋወቅና ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ የመለሱት ሊሆን ይችላል። እነርሱ ይበልጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት ተማሪ-መራሽ (Student-centered) ዘዴ ሥራ ላይ ቢውል ነበር። (ፍሪማን፣ 1986፤ ማርቶን፣ 1982፤ ኑናን፣ 1991) ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጥ ዘዴ ተማሪን ማዕከል ያደረገና ተግባቦታዊ ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ። ተማሪዎች ዋነኞቹ ተዋንያን የማይሆኑበት የገለፃ ዘዴ የተማሪዎችን ችግር ሊያቃልል እንደማይችል ይታወቃል።

ሠንጠረዥ - 17፡- በራስ መተማመንን በሚመለከት ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች መግለጫ

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	አማራጮች							
		ሀ	%	ለ	%	ሐ	%	መ	%
15	በተቋሙ ውስጥ በአገኛችሁት የአማርኛ ቋንቋ እውቀት የቱን ያህል ትተማመናላችሁ ?	50	23.4	96	44.8	55	25.7	13	6.1
16	በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይነት ለመምህርነት ሙያ ያላችሁ ብቃት ምን ያህል ነው ?	54	25.1	61	28.4	68	31.6	32	14.9

መግለጫ፡-

ሀ- በጣም ከፍተኛ

ለ- ከፍተኛ

ሐ- ዝቅተኛ

መ- በጣም ዝቅተኛ

ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ጥያቄዎች የመምህራን ማሠልጠኛ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሳካ ወጤት አስገኝቶ እንደሆነ ለማረጋገጥ የሚረዱና የሠልኞችን በራስ የመተማመን ችሎታ የሚመለከቱ ናቸው። ትምህርቱ ውጤታማ ከሆነ የማስተማሪያ መጽሐፉ የበኩሉ አስተዋጽዖ ይኖረዋል በሚል የቀረቡ ናቸው። ኬነዲ (1979 : 42) "ሠልጣኞች ለትምህርት ዓይነቱ የተዘጋጀውን መጽሐፍ ሲገለገሉ በራስ የመተማመን ስሜት ሊያድርባቸው ይገባል" ያሉትን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ጥያቄ 15 ተዘጋጅቷል።

ሠልጣኞቹ በሰጡት መልስ 146 (66.2%) ባገኙት የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀት ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚተማመኑ ሲገልጹ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ ያሉት ግን 68 (31.8%) ብቻ ናቸው። ከመልሳቸው መረዳት እንደሚቻለው ብዙዎቹ ከትምህርቱ ጠቃሚ ዕውቀት እንዳገኙ መስክረዋል።

በተራ ቁጥር 16 ላይ የሰፈረው ለአማርኛ ቋንቋ የመምህርነት ሙያ ያላቸውን ብቃት ለማወቅ የቀረበ ነው። ትምህርቱ በአብዛኛው የሚመሠረተው በመጽሐፉ ላይ በመሆኑ የሚሰጠው መልስ ከመጽሐፉ ብቃት ጋር መያያዙ የማይቀር ነው። በዚህም መሠረት 115 (53.5%) ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ የሚል መልስ ሲሰጡ 100 (46.5%) ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል። በዚህ ጥያቄ ላይ አዎንታዊና አሉታዊ መልስ የሰጡት ሠልጣኞች ቁጥር ተቀራራቢነት ታይቶበታል። ለጥያቄ 15 ከሰጡት መልስ ጋርም የሚቃረን ነው። በዚህ ረገድ ተገቢውን ጥንቃቄ ያደረጉና የጥያቄዎችን መዛመድ ያጤኑ አይመስሉም።

ሠልጣኞቹ ለዝግ ጥያቄዎች ከሰጧቸው መልሶች በተጨማሪ የራሳቸውን ነፃ አስተያየት ሰፋ አድርገው ሊገልጹ እንዲችሉ የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር።

- ስለ አማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ያለህን (ያለሽን) አጠቃላይ አስተያዬት ዘርዘር አድርገህ (አድርገሽ) አስፍር (አስፍሪ)።

ለዚህ ጥያቄ 195 ተማሪዎች መልስ ሲሰጡ 21 በክፍት ቦታ ላይ ምንም ሳይጽፉ መጠይቁን አስረክበዋል። አስተያየት ከሰጡት መካከል የአንዳንዶቹ ሐሳብ እንደሚከተለው ባጭሩ ሰፍሯል፦

- የመጀመሪያው ሴሚስተር ትምህርት ለማስተማሩ ሥራ አይረዳም፤
- በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች አሰልቺ ናቸው፤
- ስለ አንደኛ ደረጃ መጻሕፍት በደንብ ልናውቅ ይገባል፤
- መጽሐፉ ከአሮጌው መጽሐፍ ብዙም ለውጥ የለውም፤
- ስለ ዕቅድ አዘገጃጀት የቀረበው በቂ አይደለም፤
- መምህሩ "ኖት" ካልሰጡን የመጽሐፉ ብቻ አይበቃም፤
- መጽሐፉን ሲያብራሩ መምህሩ በገለፃ ጊዜ ያሳልፋሉ፤
- የመጽሐፉ ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ በአጠቃቀም ላይ ችግር አስከትሎብናል ወዘተ . .

አስተያየት ከተሰጠባቸው ነጥቦች መካከል ስለ ቋንቋዎች ባህሪይ የሚገልፀው የመጽሐፉ የመጀመሪያ ክፍል ጠቃሚ አይደለም የሚለው ይገኝበታል። ይህ ሀሳብ የተሰነዘረው በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ከማስተማር-መማር ዘዴ በተጨማሪ የሠልጣኞችን የቋንቋ ዕውቀት ማዳበር እንደ አንድ አላማ መያዙን ካለመረዳት ይመስላል። ለጥያቄ 15 በሰጡት መልስ በአማርኛ ቋንቋ ዕውቀታቸው እንደሚተማመኑ ገልፀው በነፃ

አስተያየት መስጫው ላይ ግን የመጽሐፉን ጉድለቶች ማብዛታቸው የሚስማማ ሀሳብ አይደለም።

4.1.2.2 ከመምህራን መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች መግለጫ

በደብረ ብርሃንና በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ለሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጀው መጠይቅ አራት ክፍሎች አሉት። ክፍል አንድ የመምህራንን የግል ሁኔታ የሚመለከት ሲሆን በክፍል ሁለት ደግሞ ስለ መርሀ-ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ አቅርቦት፣ አጠቃቀም ወዘተ. የሚጠይቅ ነው። በክፍል ሶስት ስለመማሪያ መጽሐፉ ብቃት የሚያወሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። የመጨረሻው ክፍል በመርሀ-ትምህርቱና መማሪያ መጽሐፉ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው። መምህራኑ የሰጧቸው መልሶች በየዘርፋቸው ተተንትነው በዝርዝር ተቀምጠዋል።

4.1.2.2.1 የመምህራኑን የግል ሁኔታ በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ መልሶች

በዚህ ክፍል የቀረቡ ጥያቄዎች ስለመምህራኑ አጠቃላይ መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ ሲሆኑ የመምህራኑን ጸታ፣ እድሜ፣ የትምህርት ደረጃና የሥልጠና ሁኔታ የሚጠይቁ ናቸው።

ሠንጠረዥ - 18፡- ከመምህራን የተገኙ አጠቃላይ መረጃዎች መግለጫ

ጸታ		እድሜ		የሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት					የት/ደረጃ		አገልግሎት	
ወ	ሴ	ከ40 በታች	ከ40 በላይ	አቢይ			ንዑስ		ኤምኤ	ቢኤ	ከ20 በታች	ከ20 በላይ
				አማርኛ	ልዩ ትም.	ፒዳ ጐጂ	አማርኛ	-				
4	-	1	3	1	1	2	2	-	2	2	3	1

የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ሁለቱ የማሠልጠኛ ተቋሞች (ደብረ ብርሃንና ደሴ) ብቻ በመሆናቸው በተቋሞቹ ውስጥ ያሉት አራቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል። ከሠንጠረዡ እንደሚታየው አራቱም መምህራን ወንዶች ሲሆኑ የሰለጠኑበት አቢይ የትምህርት ዓይነት የአንዱ ብቻ አማርኛን ማስተማር (TEAM) ሲሆን

የሁለቱ ፔዳጐጂ የሌላው ደግሞ ልዩ ትምህርት ነው፡፡ ፔዳጐጂ ያጠኑት ንዑስ ትምህርታቸው አማርኛ ነው፡፡ ልዩ ትምህርት ያጠኑት ግን ንዑስ የትምህርት ዓይነት የላቸውም፡፡ የአገልግሎት ዘመናቸው ሲታይ 3ቱ ከፍተኛ አገልግሎት አላቸው፡፡

4.1.2.2.2 <u>መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን በሚመለከት ለመምህራን ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች</u>

መምህራን ለማስተማሩ ሥራ ስለሚገለገሉበት መጽሐፍ ከማንም የበለጠ እንደሚያውቁ ግልጽ ነው፡፡ ስለመጽሐፉ ከነርሱ የሚገኘው መረጃ አስተማማኝ ስለሚሆን የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ተገቢውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

<u>ሠንጠረዥ - 19</u>፡- የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን የይዘት ብቃት በተመለከተ የመምህራን መልሶች መግለጫ

ተ.ቁ.	ጥያቄዎች	አማራጮች							
		በጣም እስማማለሁ	%	እስማማለሁ	%	አልስማማም	%	በጣም አልስማማም	%
1	በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች የተፈለገውን ሥልጠና ተግባራዊ ለማድረግ ተስማሚ ናቸው፡፡	2	50	2	50				
7	በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት የትም/ይዘቶች አዳዲስ ግንዛቤን በማስጨበጥ ረገድ ወቅታዊ አይደሉም፡፡			1	25	3	75		
10	በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች ሠልጣኞቹን የሚስቡ ናቸው፡፡			2	50	2	50		
14	የመጽሐፉ ይዘቶች በተገቢው ቅደም ተከተል የቀረቡ ናቸው፡፡			2	50	2	50		
17	የመጽሐፉ የትም/ይዘቶች ለሠልጣኞች ደረጃ የሚመጥኑ አይደሉም፡፡			1	25	3	75		

በተራ ቁጥር 1 ለተጠየቀው 4ቱም መምህራን የተስማሙበት መጽሐፉ የመምህርነት ሥልጠናውን ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚያስችል ነው፡፡ የይዘቶቹን ወቅታዊነት አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄም በአሉታዊ የተቀመጠውን ሐሳብ በመቃወም 3ቱ (75%) በወቅታዊነቱ የሚስማሙ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በተራ ቁጥር 10 የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ ግን በከፊል መስማማትንና በከፊል አለመስማማትን የያዘ መልስ ስለተሰጠበት ይዘቱ ሠልጣኞችን ሙሉ በሙሉ እንደማይስብ ያመለክታል፡፡ የይዘቱን ቅደም ተከተል አጠባበቅ በተመለከተም የአዎንታዊና አሉታዊ ቅልቅል መልስ ተሰጥቷል፡፡ የተጠያቂዎቹ ቁጥር አራት ብቻ መሆኑም ወደ አንዱ ወገን ለማዘንበል አያስችልም፡፡ እንደዚያም ሆኖ የመጽሐፉ ይዘቶች ቅደም ተከተል አጠባበቅ ችግር እንዳለበት አስተያየቱ ይጠቁማል፡፡

የመጽሐፉ ይዘቶች ለሠልጣኞች ደረጃ ስለመመጠናቸው በተራ ቁጥር 17 ላይ በአሉታዊ አገላለጽ ለተቀመጠው የመምህራኑ መልስ 3ቱ (75%) እስማማለሁ ሲሉ አንዱ ብቻ ሐሳባቸውን በተቃራኒው ገልፀዋል፡፡ የሶስቱን ሀሳብ በመውሰድ ይዘቶቹ ለሠልጣኞቹ ደረጃ እንደሚመጥኑ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ - 20፡- የመጽሐፉን መልመጃዎች አቀራረብ በተመለከተ በመላሾች የተሰጡ ሐሳቦች መግለጫ

ተ.ቁ.	ጥያቄዎች	አማራጮች							
		በጣም እስማማለሁ	%	እስማማለሁ	%	አልስማማም	%	በጣም አልስማማም	%
11	በመጽሐፉ ይዘት ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የተለያዩና ብቃት ያላቸው ሆነው አልተዘጋጁም፡፡			3	75	1	25		
16	በይዘቱ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ሠልጣኞቹ ትምህርቱን መከታተላቸውን ለመገምገም ያስችላሉ፡፡			1	25	3	75		
3	በመጽሐፉ ይዘት ውስጥ በሚገኙ መልመጃዎች ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው የቋንቋ ክሂል ነው?								
	ሀ/ ለመናገር								
	ለ/ ለማንበብ								
	ሐ/ ለመጻፍ								
	መ/ ለአራቱም ክሂሎች			4	100				
4	ለ3ኛ ጥያቄ የሰጡት መልስ 'መ' የሚል ከሆነ የክሂሎቹ ቅንጅት አጥናጋቢ ነው ?								
	ሀ/ በጣም እስማማለሁ								
	ለ/ እስማማለሁ			1	25				
	ሐ/ አልስማማም			3	75				
	መ/ በጣም አልስማማም								

በ11ኛው ጥያቄ ስለመልመጃዎች ብቃትና በተለያየ መንገድ መቅረብ ተጠይቆ 3ቱ መምህራን አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። (ስለ መልመጃዎቹ ዓይነቶች ሠንጠረዥ 7ን ይመልከቱ)። በተራ ቁጥር 16 ላይ የተጠየቀው በመጽሐፉ ውስጥ ባሉት መልመጃዎች አማካይነት ሠልጣኞችን በትክክል መገምገም ይቻል እንደሆነ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ተፈልጐ ነበር። ለዚህም የተገኘው ምላሽ እንደ ላይኛው በአብዛኛው አሉታዊ ነው። በሀሳቡ የተስማሙት አንደኛው መምህር ብቻ ናቸው።

ሂል እና ደቢን (1979 ፡ 4) ለመምህርነት ለሚዘጋጁ ሠልጣኞች ከማስተማር ዘዴው ጐን ለጐን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የሚያዳብር ትምህርት መስጠት እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ። ካሮልሪድ (1984 ፡ 73) በበኩላቸው የክሂሎች ቅንጅት የተማሪዎች አጠቃላይ የቋንቋ ችሎታን እንደሚያዳብር አብራርተዋል። ከዚህ ሐሳብ ጋር ተያይዞ ለቀረበው ለ3ኛው ጥያቄ በተሰጠው መልስ ለሁሉም ክሂሎች ትኩረት እንደተሰጠ ያስረዳል። ሆኖም የክሂሎቹ ቅንጅት አጥጋቢ አለመሆኑን ከ4ኛው ጥያቄ መልስ ማወቅ ይቻላል። ሶስቱ መምህራን (75%) አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። በአጠቃላይ ከጥያቄዎቹ ምላሾች መገንዘብ የሚቻለው መልመጃዎቹ ብቃት የሚጐድላቸውና የሥልጠናውን አላማ በሚገባ ለማሟላት የማይችሉ መሆኑን ነው።

ሠንጠረዥ - 21፡- የማስተማር-መማር ዘዴን በተመለከተ ከመምህራን የተገኙ መልሶች መግለጫ

ተ.ቁ.	ጥያቄዎች	አማራጮች							
		በጣም እስማማለሁ	%	እስማማለሁ	%	አልስማማም	%	በጣም አልስማማም	%
2	የመማሪያ መጻሐፉ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀትና ለመጠቀም የሚያስችል በቂ ይዘት አካትቷል፡፡			1	25	3	75		
6	በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የዕቅድ አዘገጃጀት መግለጫዎች የተሟሉ ናቸው፡፡			1	25	3	75		
12	በመጽሐፉ ይዘት አማካይነት የተጠቀሰው የማስተማር ዘዴ ሠልጣኞችን በቡድንና በግል እንዲሠሩ የሚያደርግ ነው፡፡	1	25	3	75				
15	በመጽሐፉ ይዘቶች ስለአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ትውውቅ በበቂ ሁኔታ አልቀረበም፡፡			3	75	1	25		

ተራ ቁጥር	ጥያቄ	መልሶች	
		ድምር	%
5	በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የየምዕራፉ የትም/ይዘቶች አመቺ የሚሆኑት ለየትኛው የማስተማር ዘዴ ነው ? ሀ- ለገለፃ ዘዴ ለ- ለውይይት ዘዴ ሐ- ለግል ሥራ ዘዴ መ- ለድርጊት ዘዴ	3 2	
8	በመጽፉ ውስጥ የተጠቀሰው የማስተማር ዘዴ አይነት በየትኛው ሊመደብ ይችላል ? ሀ- በመምህር መራሽ ለ- በተማሪ መራሽ ሐ- በሁለቱም	2 1 1	50 25 25

ከላይ የቀረቡት 6 ጥያቄዎች በሙሉ በማስተማር-መማሩ ዘዴዎች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የማስተማር-መማር ዘዴ ከስምንቱ አቢይ አላማዎች አንዱ በመሆኑ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተገቢው ይዘት ሰፍሮለታል፡፡

መርዶክ (1996 ፡ 49) ለመምህራን ማሠልጠኛዎች የሚዘጋጅ የቋንቋ ትምህርት ከሌላው የሚለየው ለማስተማር ዘዴ በሚሰጠው የተለየ ትኩረት መሆኑን ገልፀዋል። በመሆኑም በማስተማር-መማር ዘዴ ሥራ ለሚጠቃለሉት ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች በጥንቃቄ ሊጤኑ ይገባል።

የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን አዘገጃጀት ለሚመለከተው ለ2ኛው ጥያቄ 3ቱ መምህራን የሰጡት መልስ መጽሐፉ የተሟላ ሀሳብ አለማካተቱን የሚገልጽ ነው። ውጤታማ የዕቅድ አጠቃቀም ለትምህርት ሥራ መሳካት የሚኖረው ጠቀሜታ በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ክፍል ተገልጿል። ሆኖም መጽሐፉ ስለዕቅድ አዘገጃጀት የተብራራ ሐሳብ አለመያዙን ሶስቱ መምህራን አመልክተዋል።

ሠልጣኞች በቡድንና በግል እንዲሠሩ መደረጉ በሥልጠናው ወቅት የቀሰሙትን ዕውቀት ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚያስችላቸው ይታወቃል። ይህንን ለሚመለከተው ለ12ኛው ጥያቄ መምህራኑ የሰጡት መልስ ሠልጣኞቹ ተገቢውን ልምምድ እንደሚያካሂዱ የሚጠቁም ነው።

ከአንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መጻሕፍት ጋር ስለሚኖረው ትውውቅ በ15ኛው ጥያቄ ላይ ተነስቷል። ይህን በተመለከተ በአሉታዊ መልክ ለቀረበው አስተያየት ከመረጃ ሰጭዎቹ 75% የሆኑት መምህራን እስማማለሁ የሚል ነው። ይህ የማስተማሪያ መሣሪያዎች ትውውቅ ይዘት ተጠናክሮ አለመቅረቡን አስተያየቱ ያስገነዝባል። ሻው (1987 ፡ 12) አንድ ሠልጣኝ ሊቀዳጃቸው ስለሚገቡ ሥነ ትምህርታዊ ክሂሎች (Pedagogical skills) ሲያብራሩ ለሠልጣኙ የሚቀርብለት የትምህርት ዓይነት ከሥልጠናው በኋላ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር መጣጣም እንደሚኖርበት ያሳስባሉ። ይህ ባለመሟላቱ የመምህራኑ አስተያየት አሉታዊ ሊሆን ችሏል።

የማስተማር ዘዴን በተመለከተ በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሰው አቀራረብ አመቺ የሚሆነው ለገለፃ ዘዴ መሆኑን ሶስቱ መምህራን ለጥያቄ 5 በሰጡት መልስ ገልፀዋል። ሁለቱ መምህራን በተጨማሪም ለውይይት ዘዴ እንደሚረዳ አመልክተዋል። የገለፃው ዘዴ በይበልጥ ሥራ ላይ መዋሉ የመምህሩን ተግባር ብቻ ስለሚያገላ በምሁራን ገለፃ መሠረት (ፍሪማን፣ 1986፣ ኑናን፣ 1991) ተማሪን ማዕከል ያደረገ እንቅስቃሴ አለመኖሩን ያረጋግጣል። ይህንን በተመለከተ ለ8ኛው ጥያቄ መምህራን ሲመልሱ የማስተማር ዘዴው በመምህር-መራሽ እንደሚመደብ ሁለቱ ሲገልጹ አንዱ ተማሪ-መራሽ

ሌላው ደግሞ በሁለቱም ሲሉ አስፍረዋል። ሁለቱ መምህራን (50%) የሰጡት ሐሳብ ብልጫ አለው።

<u>ሠንጠረዥ - 22</u>፡- በመርሀ-ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ ግንኙነት ላይ የተሰጡ የመምህራን ምላሾች መግለጫ

ተራ ቁጥር	ጥያቄዎች	መልሶች	
		ድምር	%
18	የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መርሀ-ትምህርቱን በመከተል የተዘጋጀ ነው ? ሀ- ሙሉ በሙሉ ነው	3	75
	ለ- በከፊል ነው	1	25
	ሐ- አይደለም		
19	ለ18ኛው ጥያቄ መልስዎ 'ሙሉ በሙሉ' ወይም 'በከፊል' የሚል ከሆነ የሁለቱ ግንኙነት የተመሠረተው በየትኛው ምክንያት ነው ? ሀ- በርዕስ ቅደም ተከተል መመሳሰል	2	50
	ለ- በይዘትና አላማ ስምረት	1	25
	ሐ- የተወሰኑ ይዘቶች በሁለቱም ላይ በመገኘታቸው	1	25
23	የመማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ከማስፈጸም አንፃር ሲመዘን ሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች ግንኙነት አላቸው ? ሀ- ሙሉ በሙሉ አላቸው	1	25
	ለ- በከፊል አላቸው	3	75
	ሐ- ግንኙነት የላቸውም		
25	የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘቶች የመርሀ-ትምህርቱን አላማዎች ግብ ለማስመታት ያስችላሉ ? ሀ- ሙሉ በሙሉ ያስችላሉ	1	25
	ለ- በከፊል ያስችላሉ	3	75
	ሐ- አያስችሉም		

ስለ መርሀ-ትምህርቱና የመማሪያ መጽሐፉ ግንኙነት መምህራኑ ለ4ቱ ጥያቄዎች መልስ ሰጥተዋል። መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ በመርሀ-ትምህርቱ መሠረት ለመዘጋጀቱ ሶስቱ መምህራን ተስማምተውበታል። 19ኛው ጥያቄ በ18ኛው ላይ የተመሠረተ ሆኖ "ሙሉ በሙሉ እና በከፊል" የሚለውን መልስ የሰጡ የሚሳተፉበት ነው። ለግንኙነቱ መሠረት በሆኑ ነጥቦች ላይ ግን መምህራኑ የተለያዩ መልሶች ሰጥተዋል። ሁለቱ "በርዕሱ ቅደም ተከተል መመሳሰል" ሲሉ፣ አንዱ "በይዘትና አላማ ስምረት" ሌላው ደግሞ "በተወሰኑ ይዘቶች መመሳሰል" በማለት መልሰዋል።

የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘቶች፣ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ግብ ለማስመታት የሚያስችሉ እንደሆነ በጥያቄ 25 ላይ ለቀረበው ሀሳብ ሶስቱ መምህራን (75%) በከፊል ግብ ያስመታሉ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የመርሀ-ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሐፉን ግንኙነት አስመልክቶ ለቀረቡት ጥያቄዎች የመምህራኑ መልሶች ሲጠቃለሉ፡-

- መማሪያ መጽሐፉ መርሀ-ትምህርቱን የተከተለ ቢሆንም ግንኙነቱ የተመሠረተው በርዕስ ቅደም ተከተል መመሳሰል መሆኑ በሁለቱ መምህራን (50%) ተገልጿል።
- መማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማዎች ግብ ከማስመታት አንፃር የሁለቱ መማሪያዎች ግንኙነት በከፊል መሆኑን ከአራቱ ውስጥ ሶስቱ መምህራን አረጋግጠዋል።

ይህም የሚያመለክተው በመምህራኑ አስተያየት መሠረት መማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ሙሉ በሙሉ ለማሳካት የማይችል መሆኑን ነው።

ሠንጠረዥ - 23፡- አጠቃላይ በሆኑ ጉዳዮች የመምህራን መልሶች መግለጫ

ተ.ቁ.	ጥያቄዎች	አማራጮች							
		በጣም እስማማለሁ	%	እስማማለሁ	%	አልስማማም	%	በጣም አልስማማም	%
9	በመጽሐፉ ውስጥ በቀረቡት ይዘቶች አማካይነት የሠልጣኞችን የዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ባህሪያትን መቅረጽና ማዳበር ይቻላል።			3	75	1	75		
13	የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ሠልጣኞችን ለአንደኛ ደረጃ መምህርነት የሚያዘጋጅ ነው።			3	75	1	25		

ሁለቱ ጥያቄዎች የመጽሐፉን ብቃት ለመገምገም የሚረዱ አጠቃላይ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው፡፡ 3ቱ መምህራን (75%) በመጽሐፉ ጠቃሚነት የሚስማሙ መሆኑን በምርጫቸው አሳውቀዋል፡፡ ይህም መጽሐፉ ለመምህርነት ሥልጠና ሊረዳ እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ሆኖም ለሁለቱም ጥያቄዎች "በጣም እስማማለሁ" የሚል መልስ ባለመስጠቱና አንዱ መምህር ደግሞ የተቃውሞ ሀሳባቸውን በመግለፃቸው የመጽሐፉ ጠቀሜታ በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

4.1.2.2.3 <u>ተጨማሪ አስተያየትን ከሚጋብዘው የመጨረሻው ጥያቄ ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች መግለጫ</u>

መምህራኑ በመጨረሻ ላይ አስተያየታቸውን አብራርተው እንዲያስቀምጡ የሚከተለው ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፡፡

- ስለ ተቋሙ የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት መሣሪያዎች (መርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ) ያለዎትን አጠቃላይ አስተያየት ሰፋ አድርገው ቢያሰፍሩ፡፡

አራቱም መምህራን የየራሳቸውን ነፃ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ መምህራኑ ከሰነዘሯቸው ሀሳቦች መካከል፡-

- መጽሐፉ በክልል ደረጃ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶበት ከስምምነት ላይ የተደረሰ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ሥራ ላይ አልዋለም፡፡
- መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ በተቋማት የጋራ ግንኙነትና በሌሎችም ክፍሎች የተሻሻሉ ይዘቶች ቢጨመሩበት ጥሩ ነው፡፡
- መማሪያ መጽሐፉም ሆነ መርሀ-ትምህርቱ እንደገና ታይቶ ሊለወጥና ሊሻሻል ይገባል ወዘተ. .

የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከመምህራኑ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚጠቁመት በማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የትም/ይዘቶች ከሥልጣኞች ደረጃ በላይ አለመሆናቸውን፣ ይዘቱ የቀረበበት የቋንቋ አጠቃቀም ተገቢ መሆኑን የሚገልጹ ቢሆንም ስለመልመጃዎች አዘገጃጀት፣ ለመማር-ማስተማሩ ተግባር ድጋፍ ሰጭ ስለሆኑ ጉዳዮች፣ የቀረቡት ይዘቶች አለመሟላታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ በዚህም መሠረት የመጽሐፉ መሻሻል ለትምህርቱ ሥራ ውጤታማነት ሊረዳ እንደሚችል በመፍትሔ ሀሳባቸው ላይ ጠቁመዋል፡፡

4.1.3 ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ርዕስ ሥር የሚጠቃለለው የአንድ የትምህርት ባለሙያና የአንድ መምህር አስተያየት ነው፡፡ የትምህርት ባለሙያው በሥርዓተ ትምህርት መምሪያ አባልነታቸው ለመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የሚያገለግለውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የዝግጅት፣ የማሻሻልና የህትመት ተግባርን በኃላፊነት የሚመሩ ናቸው፡፡ በመምሪያው ውስጥ ያሉት የትምህርት ባለሙያዎች በሙሉ ሀሳባቸውን ቢያካፍሉ ጠቀሜታው የጐላ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ምክንያት የአንዱን ባለሙያ አስተያየት ብቻ ለማግኘት ተችሏል፡፡ መረጃውን ከተለያየ አቅጣጫ ለማጠናከር ሲባል በቅርብ ለተገኙት ለአንዱ የመጽሐፉ ረቂቅ አዘጋጅ መምህር ቃለመጠይቅ ተደርጓል፡፡ (ቃለመጠይቆቹን በአባሪ 7 እና 8 ይመልከቱ)

ሠንጠረዥ - 24፡- ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ባለሙያዎች አጠቃላይ መረጃ መግለጫ

ተ.ቁ.	የሥራ ቦታ	የሥራ መደብ	የት/ደረጃ	አገልግሎት	የሠለጠኑበት የትም/ዓይነት	
					ዋና	ንዑስ
1	የአማራ ክልል ትም/ቢሮ	የመምሪያ ኃላፊ	ኤም.ኤ	14	ካሪኩለም	-
2	ጢጣ ልዩ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት	መምህር	ቢ.ኤ	12	ሥነ-ልሣን	-

ቃለ መጠይቁ የተደረገላቸው የመምሪያ ኃላፊ አሁን ባሉበት በትምህርት ቢሮ አባልነት 5 ዓመታት ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የሥርዓተ ትምህርት መምሪያ ኃላፊ በመሆን እየሠሩ ናቸው፡፡ የአማርኛ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት ተጀምሮ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ጉዳዩን በኃላፊነት እየተከታተሉ ስለቆዩ ከርሳቸው የሚገኘው መረጃ የጐላ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

መምህሩ ደግሞ ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ከመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ተዛውረው በሌላ ት/ቤት የሚሠሩ ቢሆንም ቀድሞ ስላዘጋጁት መጽሐፍ የሚያውቁትን ቢገልጹ መረጃው እንደሚጠናከር ይገመታል፡፡

ቃለመጠይቁ የተደረገላቸው ሰዎች እንዳረጋገጡት (አባሪ 9 እና 10ን ይመልከቱ) በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞቹ የሚሠራበት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በቅድሚያ ረቂቁ የተዘጋጀው በመምህራን ነው። መምህራኑም ልምድ ያላቸው እንደነበሩ ተገልጿል። ከሁለቱም ተጠያቂዎች ሐሳብ መረዳት እንደተቻለው ለመጽሐፉ ዝግጅት የተሰጠው ጊዜ በጣም አጭር ነበር። መጽሐፉ በጥቂት ወራት ተዘጋጅቶና በ5 ቀናት ወርክሾፕ አስተያየት ተሰጥቶበት በቀጥታ ሥራ ላይ ውሏል። የመጻሕፍትና የመጠይቅ ትንተና በሚሉት ርዕሶች ሥር የተጠቆመት አንዳንድ ድክመቶችም መንስኤ ይኸው የችኮላ ተግባር ሊሆን ይችላል።

መጽሐፉ ለሠልጣኞችና ለመምህራን በጋራ የሚያገለግል መሆኑና ለመምህርና ተማሪ የተለያዩ መጻሕፍትን ማዘጋጀት አስፈላጊ ቢሆንም በጊዜ እጥረት ምክንያት ማድረግ እንዳልተቻለ መምህሩ አስረድተዋል። ከዚህም በተጨማሪ የመምህር መምሪያ ሊኖር ሲገባ እስካሁን ማዘጋጀት እንዳልተቻለ በተጠያቂው ተገልጿል። የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ሠልጣኞችን ለመምህርነት መሥያ የሚያዘጋጅ ስለመሆኑም የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሳካት ስለመቻሉ ሁለቱም ተጠያቂዎች አምንታዊ መልስ ሰጥተዋል። በሌላ በኩል ለመምህርነት መሥያ መዳበር ይበልጥ የሚረዱት ልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ማስተዋወቅ፣ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅትና የ1ኛ ደረጃ መጻሕፍት ትውውቅን በተመለከተ የቀረበው ይዘት የተሟላ አለመሆኑን መምህራንና ሠልጣኞች መግለጻቸው ቀደም ብሎ ተወስቷል።

ቃለ መጠይቁ የተደረገላቸው ባለሙያዎች ሀሳብ ሲጠቃለል (አባሪ 9 እና 10ን ይመልከቱ) መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ሠልጣኞችን ሊጠቅም የሚችልና የመርሀ-ትምህርቱን አላማ የሚያራምድ መሆኑን የሚገልጽ ነው።

4.2 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

4.2.1 የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞቹ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍና የመርሀ-ትምህርቱ ግንኙነት፡

በመረጃዎች ትንተና ክፍል እንደተገለፀው በመርሀ-ትምህርቱ አራት ክፍሎችና በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች መካከል ያለው ግንኙነት የላላ ሆኖ ተገኝቷል። በተዛምዶ ቀመሩ አሠራር መሠረት የሁሉም ስሌቶች አማካይ ውጤት 0.65 ሲሆን

ይህም መካከለኛ ግንኙነትን አመልካች ነጥብ እንደሆነ ተገልጿል። በአጠቃላይ ሲታይ በሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች (መርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ) መካከል ያለው ግንኙነት የሚፈለገውን ያህል ከፍተኛ ሆኖ አልተገኘም። በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የተጠቀሱት ምሁራን (ካኒንግወርዝ፣ 1984፤ ግራንት፣ 1989፤ ሀርመር፣ 1991) መርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ የጠበቀ ግንኙነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ያስገነዘቡትን ማስታወስ ይገባል።

በሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለመኖሩ መማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጀበትን የሥልጠና አላማ ሙሉ በሙሉ ለማሳካት አያስችለውም። ከተገኘው መረጃ በመነሳት ለግንኙነቱ መላላት ሊጠቀሱ የሚችሉ ምክንያቶች አሉ። አንደኛው የመርሀ-ትምህርቱም ሆነ የመማሪያ መጻሐፉ የትኩረት አቅጣጫ በመማር-ማስተማር ዘዴ ላይ በመሆኑ ቢመሳሰሉም ይህ አቢይ ጉዳይ በሁለቱ ሰነዶች ውስጥ በተመጣጠነ ሥርጭት አለመቅረቡ ነው። ከዚህም በተጨማሪ አንዱ አቢይ ርዕስ በአንዱ ክፍል አነስተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በሌላው ክፍል ግን የጐላ ድርሻ ይኖረዋል። ለምሣሌ "ሥነ ጽሑፍ" በግምገማ ላይ ከሌሎች የቋንቋ ዘርፎች የበለጠ ድርሻ አለው።

በሁለተኛ ደረጃ በአንዱ የትምህርት መሣሪያ ላይ የተጠቀሰው የትምህርት አላማ በሌላው ላይ አለመስፈሩ ነው። "የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም" የሚለው ርዕስ፣ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በትምህርትነት ሲቀርብ በመማሪያ መጽሐፉ መልመጃ ላይ ግን አልተጠቀሰም። "ቋንቋን መፈተን" የሚለው ደግሞ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ሲገኝ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ግን አልተካተተም።

ሦስተኛው ምክንያት በመርሀ-ትምህርቱ ዝርዝር አላማዎችና ይዘቶች ውስጥ የተጠቀሱት ተግባራት በመጽሐፉ መልመጃዎች ውስጥ አለመካተታቸው ነው። ይህንንም መረዳት የሚቻለው የመልመጃዎቹ ብዛት በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ከተጠቀሱት ተግባራት ያነሱ ሆነው በመገኘታቸው ነው። ለምሣሌ ያህል "የትምህርት መሣሪያዎች ትውውቅ" የሚለው በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ በአቢይ አላማነት የተጠቀሰ ሲሆን በመጽሐፉ መልመጃዎች ውስጥ ግን ተዘንግቷል።

በዚህም የተነሳ የሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች ግንኙነት በቀመሩ ስሌት እንደተገለፀው የጠበቀ ሳይሆን ቀርቷል። በሠንጠረዥ 22 ሥር ለቀረቡት ጥያቄዎች መምህራን የሰጡት መልስም ከዚህ ጋር የሚገናዘብ ነው። የመምህራኑ መልስ እንደሚያስረዳው ሁለቱም መሣሪያዎች ግንኙነት ቢኖራቸውም ግንኙነታቸው በቅርጽ ላይ

የተመሠረተ ነው። መማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ሊያሳካ የሚችለውም በከፊል ነው። ከዚህ በመነሳት የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ በተሟላ መልኩ ግብ ማስመታት እንደማይችል ማወቅ አያዳግትም።

4.2.2 ከመጠይቅ የተገኙ ውጤቶች

ለመምህራንና ሠልጣኞች በቀረበው መጠይቅ አማካይነት ለማወቅ የተፈለገው የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞቹ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለመምህርነት ሥልጠና ተስማሚ መሆኑንና አለመሆኑን ነው። በአብዛኛው የሠልጣኞቹና የመምህራን ሐሳብ ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል። ሠልጣኞቹ ስለአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፋቸው የይዘት ብቃት ከፊል አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። የመምህራኑም መልስ ከዚህ ጋር የሚሰማማ ነው።

የቋንቋ አጠቃቀምን አስመልክቶ ሠልጣኞቹ በሰጡት ምላሽ መጽሐፉ የተዘጋጀበት ቋንቋ ለደረጃቸው የሚመጥን መሆኑን አብዛኛዎቹ (65%) አረጋግጠዋል። በአስተያየት ሰጭዎቹ ሀሳብ መሠረት መጽሐፉ በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ ጠንካራ ጐን አለው።

የመጽሐፉን መልመጃዎች በተመለከተ ግን ከሠልጣኞችም ሆነ ከመምህራን የተገኘው ምላሽ አሉታዊ ነው። እነርሱ እንዳመለከቱት በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች በተለያየ የአጠያየቅ ስልት አልቀረቡም። ቁጥራቸውም የተወሰነ ሲሆን ትምህርቱን ለመረዳትም አያግዙም እንዲሁም ለክሂሎች ቅንጅት ትኩረት አይሰጡም። (የሠንጠረዥ 15 እና 20ን ማብራሪያ ይመልከቱ)።

የመምህራኑና የሠልጣኞቹ አስተያየት የጥናቱ አቅራቢ የመልመጃዎችን ሥርጭት የያዘውን ሠንጠረዥ 7ን ሲገመግም ከሰጠው ትንታኔ ጋር የሚስማማ ነው። የቋንቋን ትምህርት በተግባራዊ ክንዋኔ ለማዳበር የመልመጃዎች በብቃት መዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ሳለ መጽሐፉ በዚህ ረገድ የጐላ ድክመት እንዳለበት ከተገኘው ምላሽ ተረጋግጧል። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች በመርሀ-ትምህርቱ አላማ መሠረት የሥልጠናውን ተግባር ያሟሉ ዘንድ በልዩ ልዩ የአጠያየቅ ስልት ተቀናብረው፣ ለክሂሎች ቅንጅት ትኩረት ሰጥተውና በርክት ብለው ሊቀርቡ ይገባል።

ሠልጣኞችና መምህራን አስተያየት የሰጡበት ሌላው ጉዳይ የማስተማር መማር ዘዴ ነው። በመጽሐፉ ይዘት ላይ ተመስርተው መምህራኑ ቋንቋውን የሚያስተምሩበትን

ዘዴ እንዲገልጹ ከተጠየቁት ሠልጣኞች መካከል 60.5% የመምህሩ ገለፃ እንደሚበዛ አረጋግጠዋል። ይህም 3ቱ መምህራን የመጽሐፉ ይዘት አመቺ የሚሆነው ለገለፃ የማስተማር ዘዴ ነው በማለት ከመለሱት ጋር ይስማማል። ለውጤታማ የትምህርት ሥራ የትኛው የማስተማር ዘዴ ሊመረጥ እንደሚገባ የምሁራንን አስተያየት ማስታወስ ያስፈልጋል።

> የማስተማር ዘዴን በተመለከተ የመምህሩ ተግባር ከሚገባ በላይ ስለ ቋንቋ ገለፃ ማድረግ ወይም ስለሞዴሎች ማስተማር አይደለም። ከዚህ ይልቅ በክፍሉ ውስጥ አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠርና ተማሪዎችን በልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ በማሳተፍ ራሳቸው እንዲማሩ ማድረግ ይኖርበታል። (መርዳክ፣ 1996፡48)

የገለፃ ዘዴ ግን ሽምደዳና የቃል ዕውቀትን የሚጋብዝና መምህራንን የዕውቀት ሁሉ ምንጭ የሚያደርግ እንደሆነ ይገለፃል። የጥናቱ አቅራቢ መጽሐፉን ሲመረምር እንደተረዳው በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ፡-

ገጽ 20 - ስለ ሥርዓተ ነጥብ

ከገጽ 26 - 27 - ስለ ዐነገር አይነቶች

ገጽ 27 - ስለ አያያዥ ቃላት የቀረበው ይዘት ከአውድ (Context) ውጭ ትርጉምን በቅደም ተከተል በመደርደር በቃል ለመሸምደድ በሚያስችል መልክ የተዘጋጀ ነው። ይህም የቋንቋ ዘርፎችን በተናጠል በቃል በማጥናት ላይ ለሚያተኩረው ለሰዋስዋዊ ትርጉም ዘዴ ብቻ የሚስማማ አቀራረብ ነው።

ኪኒዲ (1979፡ 42) ለመምህርነት ሥልጠና የሚስማማ የቋንቋ ትምህርት የቋንቋውን ልዩ ልዩ ዘርፎች (ሰዋስው፣ ቃላት፣ ክሂሎች ወዘተ..) ሲያቀርብ ከቋንቋ ተግባቦታዊ ባህሪይ አንፃር በሳይንሳዊ መንገድ መመመልከት ይጠበቅበታል በማለት ያስረዳሉ። ለመምህራን ማሠልጠኛዎቹ በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት መግቢያ ላይም ለተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ የሚስማማ ይዘት የተመረጠ መሆኑን ስለሚገልጽ ከላይ የተጠቀሰው ከገጽ 20 - 27 የቀረበው ይዘት ከዚህ ሐሳብ ጋር የማይጣጣም ነው።

በመምህራንና ሠልጣኞቹ አስተያየት የተሰጠባቸውና በዚሁ በማስተማር መማር ዘዴ ውስጥ የሚካተቱት ጉዳዮች፡-

1. የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም፤
2. የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም፤
3. የ1ኛ ደረጃ መጻሕፍት ትውውቅ በሚል የቀረቡት ይዘቶች ናቸው።

ለመምህርነት ሙያ የሚዘጋጅ ሠልጣኝ በተጠቀሱት ነጥቦች ብቁ ችሎታ ሊኖረው እንደሚገባ ሻው (1987፡ 12) ያሳስባሉ። የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ባወጣው የአንደኛ ደረጃ መምህራን የባህሪይ ገጽታ (ፕሮፋይል) ተራ ቁጥር 2 ላይም ከላይ በተጠቀሱት ተግባራት ሙያዊ ብቃት ሊኖር እንደሚገባ ተጠቁሟል። (ከአባሪ 2 ጋር ያገናዝቡ) ሆኖም አብዛኛዎቹ ሠልጣኞችና 3ቱ መምህራን የትምህርት ዕቅድ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝግጅትና የ1ኛ ደረጃ መጻሕፍት ትውውቅን በተመለከተ መጽሐፉ የተሟላ ይዘት እንደሌለው ገልፀዋል። ሠልጣኞቹ ነፃ አስተያየታቸውን በሰጡበት ክፍል ይህንኑ ሀሳብ በድጋሚ አጠናክረውታል።

የጥናቱ አዘጋጅም መጽሐፉን ሲመረምር በመምህራኑና ሠልጣኞቹ የተሰነዘሩት አስተያየቶች ትክክለኛ ሆነው አግኝቷቸዋል። ከገጽ 84- 87 ስለአንደኛ ደረጃ (1ኛ - 4ኛ ክፍል) መጻሕፍት ትውውቅ የሰፈረው ይዘት የየክፍሉን መርሀ-ትምህርቶችና መማሪያ መጻሕፍትን ርዕስ ከማስተዋወቅ በቀር እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው በዝርዝር የሚያብራራ አይደለም። ስለትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት በመጽሐፉ የቀረበው ይዘትም (ከገጽ 88 - 92) ስለ ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ብቻ የሚናገርና ናሙናውን የሚያሳይ እንጂ የተለያዩ የዕቅድ አይነቶችን (ዕለታዊ፣ ሣምንታዊና፣ አመታዊ) አዘጋጅተው በተግባር የሚለማመዱበትን ማብራሪያ አልያዘም።

ለመምህራንና ሠልጣኞቹ የቀረቡት መጠይቆች አይነተኛ አላማ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ለመምህርነት ሥልጠና የቱን ያህል ተስማሚ እንደሆነ ለማወቅ ነው። በመጠይቆቹ ማጠቃለያ ላይ መጽሐፉ ለሥልጠና ያለውን ብቃት የሚመለከት ሀሳብ ሠልጣኞች በጥያቄ 16፣ መምህራን በጥያቄ 13 ላይ ተጠይቀው ነበር። ሠልጣኞቹ ተቀራራቢነት ያለው የአዎንታዊና አሉታዊ መልስ ሲሰጡ ከመምህራኑ መካከል ሦስቱ መጽሐፉ መጠነኛ ብቃት እንዳለው አረጋግጠዋል።

እስካሁን ከተዘረዘሩት የመምህራንና ሠልጣኞች የተለያዩ መረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ብቃት የመካከለኛ ደረጃ የሚሰጠው መሆኑን ነው። በመረጃዎች ትንተና የመጀመሪያ ክፍል የተዛምዶ ቀመሩ ስሌት ያሳየውም ይህንኑ ውጤት ነው። መጽሐፉ የተጠቃሚዎቹን ፍላጐት በአጥጋቢ ሁኔታ ሊያረካና ለመሥያው መዳበር ሊያግዝ የሚችለው የተጠቆመሙት ድክመቶች ሲስተካከሉ ሲሆን አሁን ባለበት ደረጃ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ሙሉ በሙሉ ግብ ለማስመታት እንደማይችል መረጃዎቹ ያረጋግጣሉ።

4.2.3 ከቃለመጠይቅ የተገኙ ውጤቶች

ቃለመጠይቁ ያስፈለገበት ምክንያት መምህራንና ሠልጣኞች የሰጡትን አስተያየት ከሌሎች ባለሙያዎች ሀሳብ ጋር ለማገናዘብ እንዲያመች ነው። መጽሐፉ በአግባቡ የተዘጋጀ ነው ወይ ? የሚለውን በጥናቱ መነሻ ላይ የቀረበውን ጥያቄ የሚመለስውም ይህ ክፍል ነው።

ከቃለ መጠይቁ ምላሽ እንደተረዳነው ለደብረ-ብርሃንና ለደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የሚያገለግለው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተሪያ መጽሐፍ ረቂቅ በቅድሚያ የተዘጋጀው በአንደኛው ተቋም መምህራን ነው። ከአዘጋጂዎቹ መምህራን መካከልም ሁለቱ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በማዘጋጀት ረገድ ልምድ ያላቸው ሲሆኑ በተለይም አንደኛው በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው የተቋሞች የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዝግጅት ላይ ስለተሳተፉ ሁለቱን መሣሪያዎች ለማገናኘት እንደ ድልድይ ሆነው ሊያገግሉ እንደሚችሉ ይገመታል።

በመጻሕፍት ዝግጅት ወቅት የመምህራን ተሳትፎ መኖሩ በምሁራን ይደገፋል። ጥሩ የሚባሉት መጻሕፍት በመምህራንና ችሎታው ባላቸው ባለሙያዎች የሚዘጋጁ መሆናቸውን ሀርመር (1991፡ 257 -58) ፋረልና ሄንማን (1989፡45) ያስረዳሉ። መጽሐፉ በአካባቢ ደረጃ መዘጋጀቱም የተጠቃሚውን ክፍል ፍላጐት በቅርብ ለማወቅና ለማሟላት ስለሚረዳ ምሁራኑ ይስማሙበታል።

በሌላ በኩል ለዝግጅቱ የተሰጠው ጊዜ አጭር እንደነበረ በሁለቱም ተጠያቂዎች ተነግሯል። በጥድፊያ በሚከናወን ሥራ ደግሞ የተሻለ ውጤት መቀዳጀት አይቻልም። በዚህም የተነሳ በየምዕራፉ የተጠቆሙት የሚከተሉት ድክመቶች ሊከሰቱ ችለዋል።

- በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱት ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተሟላ ሁኔታ አለመካተት፣
- በቂና የተለያዩ መልመጃዎች አለመቅረብ፣
- የቃንቋ ክሂሎች ቅንጅት አለመጠበቅ፣
- ለልዩ ልዩ የማስተማር ዘዴዎች አመቺ የሆኑ ይዘቶችን አለመያዝ፣
- ለመማር-ማስተማሩ ሂደት ድጋፍ ሰጭ ለሆኑ ተግባራት ትኩረት አለመስጠት፡ ወዘተ.

በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች በተለወጠው (በአሮጌው) መጽሐፍ ላይ የተመሠረቱና ተሻሽለው የቀረቡ መሆኑ በአዘጋጁ መምህር ተገልጿል። ሠልጣኞቹ ነባ አስተያየት በሰጡበት የመጠይቁ ክፍልም አዲሱ መጽሐፍ ከዱሮው በቅርጽም በይዘትም እንደማይለይ ካመለከቱት ጋር የሚገናዘብ ነው። ይህም ከጊዜ ማጠር የመነጨና ለድክመቱ የበኩሉን አስተዋፅዖ የሚያደረግ ምክንያት ሊሆን ይችላል። አባኒያ (1985፡ 62) የማስተማሪያ መሣሪያዎች ሥራ ላይ ለማዋል የተለያዩ ደረጃዎችን ማለፍ እንደሚኖርባቸው ያስገነዘቡት ትኩረት አላገኘም።

ከትምህርት ባለሙያው የቃለመጠይቅ መልስ እንደተረዳነው መጽሐፉ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በመምህራን ተገምግሞ በሁኔታዎች አለመመቸትና በጊዜ እጥረት ምክንያት የማሻሻሉ ሥራ ሳይካሄድ ቀርቷል። ይህ ሁኔታ በመምህራንም ዘንድ ቅሬታ ማስከተሉን ነባ አስተያየታቸውን በሰጡበት በተራ ቁጥር 4.1.2.2.3 ሥር ተመልክቷል።
የትምህርት ባለሙያውም በመጽሐፉ ላይ የመስክ ጥናት እንዳልተደረገበት የጠቆመ ሲሆን በሌላ በኩል ስለመጽሐፉ ብቃት በሰጡት መልስ መርሀ-ትምህርቱን መሠረት አድርገው የተዘጋጀ ስለሆነ በሠልጣኞች ላይ ተገቢውን የባህሪይ ለውጥ ሊያስገኝ እንደሚችል ገልፀዋል።

ይሁን እንጂ ከማስተማሩ ተግባር ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባላቸውና ሠልጣኞቹ ወደተግባር ሲሰማሩ ሥራ ላይ በሚያውሏቸው የትምህርት ዕቅድ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝግጅትና የ1ኛ ደረጃ መጻሕፍት ትውውቅ ይዘቶች ረገድ ድክመት እንደሚታይ በመጠይቅ ምላሽ ተጠቁሟል። እነዚህን ሳያሟላ ባለሙያዎቹ እንዳሉት ሠልጣኞችን ለመምህርነት ተግባር ያዘጋጃል ለማለት አያስደፍርም። ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፉ እንደ መማሪያም እንደ ማስተማሪያም ሆኖ ለመምራንና ሠልጣኞች በጋራ የሚያገለግል መሆኑን፣ በቁጥር አነስተኛ ስለሆነ ለሠልጣኞች የማይዳረስ መሆኑን፣ የመምህሩ መምሪያ ባለመዘጋጀቱ በማስተማሩ ተግባር ላይ ችግር እንደሚያስከትል በአዘጋጁ መምህር ተወስቷል።

እነዚህ ሁሉ ተጠቃለው ሲታዩ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን አላማዎች በአጥጋቢ ሁኔታ ግብ ለማስመታት እንደማይችል መገንዘብ ይቻላል።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳቦች (CONCLUSION AND RECOMMENDATION)

5.1 ማጠቃለያ (Conclusion)

ይህን ጥናት ለማካሄድ አነሳሽ ምክንያት የሆነው ከዚህ በፊት በማዕከል ይሠራጩ የነበሩት የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ማስተማሪያ መጻሕፍት በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት በየአካባቢው አንዲዘጋጁ በመደረጉ በነርሱ ላይ ግምገማ ማካሄዱ ለትምህርቱ ሥራ ውጤታማነት የበኩሉን ዕገዛ እንደሚያደርግ በማሰብ ነው። በሌላ በኩል በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍት ላይ የተለያዩ የቅድመና ድህረ ምረቃ ጥናታዊ ጽሑፎች የተዘጋጁ ሲሆን (አያሌው፣ 1985 ዓ.ም፤ ጌታቸው፣ 1986 ዓ.ም፤ አሥራቴ፣ 1988 ዓ.ም) የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ማስተማሪያ መጻሕፍት ግን ቀድሞም በሆነ ለጥናት ርዕስነት የተተኮረባቸው አይመስልም።

በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ይሰጥ የነበረው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት እስከ 1972 ዓ.ም ድረስ መደበኛ መርሀ-ትምህርትም ሆነ በርሱ መሠረት የተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ ሳይኖረው በተለያዩ ጽሑፎች አማካይነት ሲካሄድ ቆይቷል። ከ1972 እስከ 1986 ዓ.ም የሥርዓተ ትምህርት ንድፍ በሚል መመሪያና ተሻሽሎ በተዘጋጀ ማስተማሪያ መጽሐፍ የቋንቋው ትምህርት ይሰጥ ነበር።(ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1972 ዓ.ም)

አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ (1986 ዓ.ም) በሚፈቅደው መሠረት ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ መርሀ-ትምህርቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅቶ የተሠራጨ ቢሆንም የማስተማሪያ መጽሐፉ ግን በየክልሎቹ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረትም በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር ለሚገኙት ለደሴና ለደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሳካት የሚያስችል መሆኑን ለመገምገም ነበር፡

የመማሪያ-ማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት ትኩረትን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአዲስ መልክ የሚዘጋጁ የትምህርት መሣሪያዎች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊትም ሆነ በሥራ ላይ እያሉ በየወቅቱ ሊገመገሙና ሊሻሻሉ እንደሚገባቸው ካኒግወርዝ (1984) ግራንት (1989) ያስገነዝባሉ፡፡

በዚህ ሥራ ውስጥ ዱቢንና አልሾቴይን (1986 ፡ 28-30) የዘረዘሯቸው መጻሕፍትን የመገምገሚያ ነጥቦች ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ግምገማው ሲካሄድ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር የሚጣጣም መሆኑን፣ መጽሐፉ ለመምህርነት ሥልጠና ተስማሚ መሆኑን፣ በአካባቢ ደረጃ የተከናወነው የመጽሐፉ የዝግጅት ሂደት የተሟላ መሆኑን ለመፈተሽ የሚያስችሉ መሠረታዊ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

በመርሀ-ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ መካከል ያለውን መጣጣም ለመመርመር የመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎች ከመርሀ-ትምህርቱ ዝርዝር አላማዎች፣ ይዘቶች፣ የማስተማር-መማር ክንውንና ግምገማዎች ጋር ተነፃፅረዋል፡፡ በተገኘው የተዛምዶ ቀመር ውጤት መሠረት በአጠቃላይ ሲታይ በሁለቱ የትምህርት መሣሪያዎች መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡ በመሣሪያዎቹ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ላለመኖሩ ከሚጠቀሱት ምክንያቶች መካከል የአቢይ ርዕሶች ሥርጭት አለመመጣጠንና በአንዱ መሣሪያ ላይ የቀረበው ርዕስ በሌላው ላይ አለመኖሩ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ሠልጣኞችን ለመምህርነት ተግባር ለማዘጋጀት ተስማሚ መሆኑን ለማወቅ ለመምህራንና ለሠልጣኞች ታድለው ከተሰበሰቡት መጠይቆች መረጃዎች ተገኝተዋል፡፡ ከመረጃዎቹ በተገኘው ውጤት መሠረት ይዘቶቹ የቀረቡበት ቋንቋ ለሠልጣኞች የእድሜና የችሎታ ደረጃ የሚመጥን ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌሎች በርካታ ነጥቦች ላይ ግን ከፊል አዎንታዊ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ይህም ግራንት (1989 ፡ 118) ተመራጭነት ያለው የማስተማሪያ መጽሐፍ፡-

- ለተማሪዎች ፍላጐትና ዝንባሌ ተስማሚ የሆነ፣
- ለመምህራን የማስተማር ሁኔታ ምቹ የሆነ፣
- የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ማሟላት የሚችል፣

መሆን አለበት በማለት የገለጹትን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ እንደማያስችል ያሳያል።

ከመርሀ-ትምህርቱ አቢይ አላማዎች አንዱ የቋንቋ ክሂሎችን ማዳበር ሲሆን ክሂሎች ሊዳብሩ የሚችሉት ደግሞ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባሉት መልመጃዎች አማካይነት መሆኑ ይታወቃል። ናታል (1982 : 134) በመጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎች የተለያዩ የአጠያየቅ ስልቶችን የያዙና በበቂ ሁኔታ የቀረቡ መሆን እንዳለባቸው ያስታውሳሉ። ይህንኑ ለመረዳት በመጠይቁ ውስጥ ለሰፈሩት ሀሳቦች ሠልጣኞችና መምህራን በሰጡት ምላሽ መልመጃዎቹ በአብዛኛው አንድ ዓይነት መሆናቸውን፣ በቁጥር አናሳ መሆናቸውንና የተለያዩ ክሂሎችን ለማዳበር እንደማያስችሉ አረጋግጠዋል።

የመማር-ማስተማር ዘዴን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ መጽሐፉ የመምህራንን ሚና ብቻ አጉልቶ ለሚያሳየው የገለፃ ዘዴ አመቺ መሆኑንና ለተግባራዊ የማስተማር ሥራ የሚረዱትን እንደ ዕቅድ አዘገጃጀት፣ የትምህርት መሣሪያዎች አጠቃቀምና የ1ኛ ደረጃ መጻሕፍት ትውውቅ ለመሳሰሉት ይዘቶች መጽሐፉ የተብራራ ሀሳብ እንደሌለው መምህራኑና ሠልጣኞቹ አመልክተዋል። ሻው (1987:12) ለመምህርነት ሥልጠና የሚዘጋጁ ተማሪዎች እንደ ትምህርት ዕቅድና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝግጅት ወዘተ. . ያሉትን ሥነ ትምህርታዊ ክሂሎች (Pedagogical Skills) በአግባቡ ሊያዳብሩ እንደሚገባ አጥብቀው ይመክራሉ። ይሁን እንጂ ይህን ለማሟላት ባለመቻሉ መረጃ ሰጭዎቹ በመጠይቁ ላይ አስተያየታቸውን እንደገለጹት መጽሐፉ ለመምህርነት ሥልጠና ተግባር ሊረዳ የሚችለው በመጠነኛ ደረጃ ብቻ ነው።

መጽሐፉ አላማውን ሊያሳካ የሚችለው በዝግጅቱ ጥራት የተነሳ በመሆኑ አዘገጃጀቱን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የተቻለው በቃለመጠይቅ አማካይነት ነበር። የቃለመጠይቁ ውጤት እንደሚያመለክተው መጽሐፉ በአጭር ጊዜ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ የዋለ ነው። በሌላ በኩል መጽሐፉ የተዘጋጀበትን አላማ በትክክል እንደሚያሟላ በቃለ መጠይቅ ሰጭዎቹ ተገልጿል። ምንም እንኳን የትምህርት ባለሙያዎች ይህን አስተያየት ቢሰጡም በመምህራንና ሠልጣኞች የመጠይቅ መልስና በአጥኚው የመጻሕፍት ትንተና ውጤት መሠረት የመጽሐፉ ዝግጅት አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም።

በአጠቃላይ ሲታይ መጽሐፉ፡-

- በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ይዘቶች በተሟላ ሁኔታ አለመያዝ፣
- በቂና የተለያዩ መልመጃዎች አለማቅረብ፣
- የቋንቋ ክሂሎችን ቅንጅት አለመጠበቅ
- ለልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች አመቺ የሆኑ ይዘቶችን አለማካተት፣
- ለመማር-ማስተማሩ ሂደት ድጋፍ ሰጭ ለሆኑ ጉዳዮች (የዕቅድ፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ዝግጅት ወዘተ. .)

ተገቢውን ትኩረት አለመስጠትና የመሳሰሉት ድክመቶች እንዳሉበት ጥናቱ ይጠቁማል።

5.2 የመፍትሔ ሀሳቦች (Recommendations)

ለደሴና ለደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመምህርነቱን ሥልጠና ውጤት ለማሳካት ይችል ዘንድ ከዚህ ጥናት ማጠቃለያ በመነሳት የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል።

ሀ- የመማሪያ መጽሐፉ መልመጃዎችና የመርሀ-ትምርቱ ዝርዝር አላማዎች፣ ይዘቶች፣ የማስተማር ዘዴዎችና ግምገማዎች ግንኙነት የሚፈለገውን ያህል የጠበቀ ባለመሆኑ ሁለቱ መሣሪያዎች ካሁኑ በበለጠ ተጣጥመው የትምህርቱን አላማ ውጤታማ ያደርጉ ዘንድ መጽሐፉ በተሻለ መንገድ መዘጋጀት ይኖርበታል።

ለ- በመጽሐፉ ይዘቶች ውስጥ ከተካተቱት ጽሑፎች መካከል በመርሀ-ትምህርቱ ውስጥ ለተጠቀሰው ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ አመቺ ያልሆኑት በሌሎች ተስማሚ ጽሑፎች መተካት አለባቸው።

ሐ- በዚህ ጥናት መሠረት ገሳ ብሎ የታየው የመልመጃዎች አዘገጃጀት ድክመት በመሆኑ መልመጃዎቹ የተለያዩ የባህሪይ ገጽታዎችን ሊያዳብሩ እንዲችሉ በአይነትና በመጠን ጨምረው እንደገና መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

መ- መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ የተዘጋጀው ዕጩ መምህራንን ለማሠልጠን ስለሆነ በልዩ ልዩ የመማር-ማስተማር ዘዴዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

ስለሆነም፡-

- የተለያዩ የማስተማር ዘዴዎችና ስልቶች ለምሳሌ እንደ የቡድን ውይይት፣ የግል ሥራ፣ የሠርቶ ማሳያ ወዘተ. . ለመለማመድ የሚያስችል ይዘት ሊኖረው ይገባል፡፡
- የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በእድሜም ሆነ በአስተሳሰብ ለጋ ስለሆኑ ለነርሱ የሚቀርብ ትምህርት ልዩ ጥረትና ጥንቃቄ ሊኖር እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ሠልጣኞቹ ትምህርቱን ግልጽ በሆነ አቀራረብ ለማስተላለፍ እንዲችሉ በተቋሞቹ ውስጥ እያሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀምን አውቀው በተግባር መለማመድ ይኖርባቸዋል፡፡ መጽሐፉም ለዚህ ይበልጥ እንዲረዳ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡፡
- በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ውስጥና በ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት ግንኙነት እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ሠልጣኞች የ1ኛ ደረጃውን (1ኛ - 4ኛ) ማስተማሪያ መሣሪያዎች (መርሀ-ትምህርት፣ የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መጽሐፍ) በማሠልጠኛው ውስጥ እያሉ በሚገባ ማወቅ፣ መገምገምና እንዴት እንደሚያስተምሯቸው መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለሆነም በመጽሐፉ ይዘት ውስጥ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት ዕጩ መምህራኑም በመሣሪያዎቹ በመጠቀም ረገድ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲለማመዱ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ሠ- እስካሁን የተጠቆሙትን ድክመቶች ለማሻሻል መጽሐፉን እንደገና ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ በዝግጅቱ ሂደትም ከየተቋመ. የተውጣጡ ባለሙያዎች ተሳትፈውበት፣ በቂ ጊዜ ተሰጥቶትና በመምህራንና ሠልጣኞች አስተያየት ዳብሮና ተሻሽሎ ከበቂ የመ.ከራ ጊዜ በኋላ ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡

ሠ- የዚህ ጥናት ትኩረት በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ላይ ብቻ ስለሆነ በመርሀ-ትምህርቱም ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት ቢካሄድ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ መማሪያ መጽሐፉም ሆነ መርሀ-ትምህርቱ ከአሁኑ በተሻለ ደረጃ በጥራት ቢዘጋጁ ለሥልጠናው አላማ ውጤታማነት ዕገዛ እንደሚያደርጉ ይታወቃል፡፡

ፃቢ. (BIBLIOGRAPHY)

Abebe Bekele. (1974). "Some thoughts on the basis for development of Educational objectives." The Ethiopian Journal of Education. Vol. VII No.1 pp.25-38.

Abreham Hussain. (1986). "The State of Teacher Education in Ethiopia: A Comparative Study." Addis Ababa: Addis Ababa University. The Institute of Educational Research.

Amdeselasie G. Kirkos. (1993). "Assessing the TTI Amharic Syllabus." M.A Thesis. Addis Ababa University.

Beardon, T. et.al. (1992). "School-led Initial Teacher Training". Cambridge Education Papers No. 2. Department of Education. University of Cambridge.

Billows, F.L. (1961). The Techniques of Language Teaching. London: Longman.

Brown, et.al. (1982). Curriculum and Instruction: An Intoduction to Methods of Teaching. London: Macmillan Education Ltd.

Bright, J.A and G.P. McGregor. (1978). Teaching English as a second Language. London : Longman.

Brumfit, C.J ed. (1984a) General English Syllabus Design. Oxford : Pergamon.

Carolread. (1984). "Integrating skills at the Bignner level." Teaching and the Teacher. ed, susan Holden. Hongkong: MEP Ltd.

Clark, J.L (1987). Curriculum Renewal in School Foreign Language Learning. Oxford: Oxford University Press.

Cross, D. (1987). "Producing an Inset syllabus Language Teacher Education: An Integrated Programme for ELT Teacher Training. ELT Documents 125. London: Modern English Publications.

Cunningsworth, A. (1984). Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials. London: Heinemann, Educational books Ltd.

Dodd, W.A. (ed). (1970). The Teacher at Work. London: Oxford Uiversity Press.

Dubin, F. and E.Olshtain. (1986). Course Design Developing Programme and Materials for Longuage Learning. Cambridge: Cambridge University Press.

_____.(1990) Materials for Language Learning. Newyork: Cambridge University Press.

Edge,J. (1993). Essentials of English Language Teaching. NewYork: Longman.

Farrell, T. and Pan Heynman. (1989). Text Books in the Developing World: Economic and Educatinal Choices. Washington: Worldbank.

Finoccharo, M. (1984). "Pre Service and In-service Teacher Training". Teaching and the Teacher. ed, Susan Holdan oxford: MEP Ltd.

Freeman, D.C (1986) Techniques and Principles in Language Teaching. oxford : Oxford Univercity Press.

_____.(1989) "Teacher Training Development and Decison Making: A Model of Teaching and Related strategies for Language Teacher Education" TESOL Quarterly, V. 23 No.1 27-45).

Grant, N. (1989). Making the most of your Text book London: Longman.

Hailom Banteyerga. (1993) "Exploration in the preparations of pre-service EFL Teachers:- A learning Centerid approach" PhD. Thesis. Addis Ababa University.

Harmer, J. (1983). The Practice of english Language Teaching. NewYork : Longman.

_____. (1991). The practice of Enslish Language Teaching. NewYork : Longman U.K. ltd.

Hill, LA. and M. Dobbyn. (1975). A Teacher Training Course: Lecturer's book. London : Cassell Ltd.

_____.(1979). A Teacher Training Course For Teachers of EFL: Trainees book London : Cassell

Hutchinson, T and A. Waters. (1987). English For Specific Purposes : A Learning Centered approach. Cambridge: Cambridge University Press.

Institute of Curriculum Development and Research (1997). "Teacher Education and Training Curriculum", Part three (Unpublished).

Kennedy, C.M. (1979). "The Training of Teachers For Esp" Teacher Training ed, Susan Holden Hongkong : MEP Ltd.

Kral, T. (ed). (1996). Teacher Development Making the Right Moves, Selected Articles from the English Teaching Forum 1989-1993. Washington : English Language Programme Division.

Lew,YA. (ed). (1977). Handbook of Curriculum Evaluation Paris: UNESCO.

Mackey, W.F. (1965) Language Teaching Analysis London: Longman Group Ltd.

Mariani, L. (1987). "Some Guide lines For Teacher Training Programme." Teacher Training, ed, Susan, Holden. Hongkong: MEP Ltd.

Marton, W. (1982). Methods in English Longuage Teaching: Frameworks and Options NewYork: Prentice Hall.

Mehrens, W.A. and Lehmann, I.J. (1991) Measurement and Evaluation in Education and Psychology(4th ed). San Diego: Harcourt Brau College Publishes.

Mcdonough, J. and C. Shaw. (1993), Materials and Methods in ELT: A Teacher's Guide. USA: Black well.

Murdoch. G.S (1996). "Practising what we Preach: A Trainee-Centred Approach to In-service Training." Teacher Development Mating The Right Moves ed Kral. Washington: English programe Division.

Nassar, R.T. (1972). Teaching and Learning English London: Longman.

Nunan, D. (1988) Syllabus Design. Oxford: Oxford University Press.

_____. (1991). Longuage Teaching Methodology: A Textbook for Teachers. NewYork: Printice Hall International.

Nuttall, C. (1982). Teaching Reading Skills in a Foreign Language. London: Heinemann.

Obanya, P. (1985). Teaching Methods across the Curriculum. London: Collins Intirnational

Richards, J.C. (1987). The Context of Language Teaching. NewYork: Cambridge University Press.

_____.and D.Nunan (eds), (1990) Second Longuage Teacher Education.(2nd ed). Cambridge: cambridge university Press.

Rodgers, T. (1979). "Teacher Training in Progress." ELT Document 104 Developments in the Training of Teachers of English. Oxford: British Council.

Shaw, P.A. (1987). "Handling A longuage Component in a Teacher Training Course" Teacher Training ed. Susan Holden Hongkrong: MEP Ltd.

_____. (1982). "Foreign Language Syllabus Development some Recent Approaches." Longuage Teaching Surveys.ed Kinsella, Cambridge: Cambridge University Press.

Stern, H.H (1984). Fundamental Concepts of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

_____. (1984). "Review and discussion". General English Syllabus Design, ELT Documents 118. ed, Brumfit. Oxford: Pergamon.

Strevens, P. (1977). New Orientations in the Teaching of English. London: Oxford University Press.

Susan, H. (1984). "Teachers and Learners: The Changing Focus" Teaching and the teacher, ed, Susan Holden. Hongkong: MEP Ltd.

Taba, H. (1962). Curriculum Development Theory and Practice. Marcourt Brau. Jovanourch Inc.

Teshome Wagaw. (1979). "Educational Development in Ethiopia: A source book" AAU (PP 1-466), Unpublished.

Tyler, R. (1949). Basic Principles of Curriculum and Instruction. University of Chicago press.

West, M, (1960). Teaching English in a Difficult Circumstances. Oxford: Longman.

_____.(1978). Longuage Teaching Analysis. London: Longman.

White, R.v. (1988). The ELT Curriculum, Massachusetls: Basil Black well Inc.

Widdowson, H.G. (1978). Teaching Longuage as Communcation Oxford: Oxford University Press.

_____. (1990). Aspects of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Williams, D. (1983) "Developing Criteria for Text book Evaluation", ELT 37, 1-4 : 251-255.

Yalden, J. (1987). Principles of Course Design For Longuage Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት፣ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት:: (1982):: አማርኛ ለአንድ ዓመት የመምህርነት ሥልጠና:: አዲስ አበባ:: ት.መ.ማ.ማ.ድ

_____:: (1987):: "ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ሥልጠና የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ሲለበስ" (የተባዛ)

በትምህርት ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነትና ዜና አገልግሎት ዋና ክፍል:: (1977):: ከትምህርት አለም (የመስከረም ወር ልዩ እትም) ከገጽ 34-35::

_____:: (1979):: ከትምህርት አለም (የነሐሴ ወር ልዩ እትም) ከገጽ 17-18::

በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራን ትምህርት ክፍል:: (1972):: "ለ1ኛ ደረጃ መምህራን አሠለጣጠን የተዘጋጀ ሥርዓተ ትምህርት የመጀመሪያ ረቂቅ" (የተባዛ)::

በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የሥርዓተ ትምህርት መምሪያ:: (1987):: ለአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን (ከ1ኛ-4ኛ) የተዘጋጀ የአማርኛ ትምህርት መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ::

አሥራቴ ገበየሁ:: (1988):: "በ1984 ዓ.ም የታተመው የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ከመማሪያ መጽሐፉ ጋር ያለው ግንኙነት":: ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ የኢትዩጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ የቀረበ::

አብዱሮህማን መሃመድ:: (1985):: "መመህርና ሥራው አጠቃላይ የማስተማር ዘዴ":: መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ የሥነ ትምህርት ክፍል:: (የተባዛ)

አያሌው አስፋው:: (1985):: " ከ1933-1983 ዓ.ም ባሉት አመታት ውስጥ በአገልግሎት የዋሉ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ዝርዝር ዓይነትና የይዘት ግምገማ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍል፣ ለዲግሪ ማሟያ የቀረበ::

ጌታቸው አዱኛ:: (1986):: "ለ10ኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ት/ቤት፣ ለማስትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ::

የኢትዩጵያ ሽግግር መንግሥት:: (1986):: አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ (ኢትፖ 86) አዲስ አበባ:: ት.መ.ማ.ማ.ድ.

አ ባ ሪ ዎ ች

አባሪ 1

በመጀመሪያ ደረጃ የአንደኛ ሳይክል /1ኛ - 4ኛ/ ለሚያስተምሩ መምህራን ሥልጠና የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ዓላማዎች

1- የቋንቋን መሠረታዊ ሃሣቦችን ይረዳሉ፤
2- የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮችን ይገነዘባሉ፤
3- የሥርዐተ-ነጥቦችን አጠቃቀም ያውቃሉ፤
4- የሥነ-ፅሑፍ ችሎታቸውን ያዳብራሉ፤
5- ቋንቋን የማስተማር መማር ዘዴዎችን ተግባራዊ ያደርጋሉ፤
6- ከአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል /1ኛ-4ኛ/ የትምህርት መሣሪያዎች ጋር ይተዋወቃሉ፤
7- የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎችን አዘጋጃጀትና አጠቃቀም ይረዳሉ፤
8- የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትንና አጠቃቀምን ይገነዘባሉ፤

በመጀመሪያ ደረጃ የአንደኛ ሳይክል /1ኛ-4ኛ/ ለሚያስተምሩ መምህራን ሥልጠና የአማርኛ ቋንቋ መርሐ-ትምህርት አጠቃላይ ይዘቶችና የክፍለ-ጊዜ ድልድል

		ክ/ጊዜ
1.	የቋንቋ መሠረተ-ሀሳቦች	3
	1.1 ቋንቋ ምንድነው ?	
	1.2 የቋንቃ አጠቃላይ ባህሪያት	
2.	የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ ጠባዮች	8
	2.1 በድምፅ ደረጃ	
	2.2 በቃላት ደረጃ	
	2.3 በዐ.ነገር ደረጃ	
3.	ሥርዐተ ነጥቦች	3
4.	ሥነ ፅሑፍ	7
	4.1 ሥነ-ቃል	
	4.2 የፅሑፍ ሥነ-ፅሁፍ	
5.	ቋንቋን የማስተማር መማር ዘዴዎች	20
	5.1 የማስተማር መማር ፅንሠ-ሀሣብ	
	5.2 የቋንቋ ትምህርት መነሻ ምክንያት	
	5.3 የቋንቋ ክሂሎቶች	
6.	የመጀመሪያ ደረጃ 1ኛ ሳይክል /1ኛ-4ኛ/ የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት የመምህሩ መምሪያዎችና የተማሪው መፃሕፍት ትውውቅ . . .	4
	6.1 ዓላማ	
	6.2 ይዘት	
	6.3 ያዘገጃጀት ዘዴ	
	6.4 የመማሪያዎቹ ቅንጅታዊ አጠቃቀም	

ክ/ጊዜ

7. የቋንቋ መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም 3

7.1 ማዳመጥን ለማስተማር የሚረዱ

7.2 መናገርን ለማስተማር የሚረዱ

7.3 ማንበብን ለማስተማር የሚረዱ

7.4 ፅህፈትን ለማስተማር የሚረዱ

8. የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም 4

8.1 ዓመታዊ የቋንቋ ትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም፣

8.2 ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አጠቃቀም፣

ጠቅላላ የክ/ጊዜ መጠን፣ 52

ምንጭ:- የሥርዓተ ትምህርት ኢንስቲትዩት በ1987 ዓ.ም ለአንደኛ ደረጃ መምህራን ሥልጠና ያዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት::

አባሪ - 2

ከ1-4ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን መለያ ባህሪ (ፕሮፋይል)

መምህራኑ በሥራ ላይ ከመሰማራታቸው በፊት 10ኛ ክፍልን እንዳጠናቀቁ የ2 ዓመት ሥልጠና ተሰጥቷቸው የትምህርት ደረጃቸው 10+2 መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ (ሠርቲፊኬት) ያገኛሉ፡፡

በዚህ እርከን የሚመደቡት መምህራን፡-

1- መሠረታዊ ዕውቀትን መደበኛና ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ አቀናጅቶ ለማቅረብ መቻል፣

2 መሠያው ከሚጠይቃቸው አስፈላጊ ጉዳዮች ጋር በሚገባ መተዋወቅ፣ ማለትም ለማመር-ማስተማሩ የሚጠቅሙ ሥነ ዘዴዎችንና የትም/መርጃ መሣሪያዎችን መምረጥና ተግባራዊ ማድረግ መቻል፣ እንዲሁም የትምህርቱን አቀራረብና የተማሪዎችን አያያዝ በሚገባ ማጤን፣

3 የተማሪዎችን፣ የት/ቤቱንና የአካባቢውን አቅምም ሆነ ለየት ያለ ባህሪይ ተገንዝቦ ከመማር ማስተማሩ ተግባር ጋር ለማዛመድ መቻል፣

4 የተማሪዎችን ፍላጐትና በትምህርቱ ያሳዩትን መሻሻል በቅርብ በመረዳት ከእድሜ ደረጃቸው ጋር የሚመጣጠኑ የክሂል ዘርፎችን እንዲያዳብሩ ማገዝ፣

5- ለመሠያው ከሚያስፈልገው ሥነ ምግባር ጋር በሚገባ መተዋወቅ፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎችን መውደድ፣ ለማስተማሩ ሥራ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀትና ለሰላምና ለአለም አቀፍ ህግጋት ራስን ጠበቃ አድርጐ ማቅረብ፣

6- በሚመደቡበት የሥራ ቦታ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለማስተማር-መቻል፣ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ምንጭ፡- ሥርዓተ ትምህርት ኢንስቲትዩት፣ (1997፡12)
(ወደ አማርኛ የተተረጐመ)

አባሪ 3

የግንኙነት ቀመርና አተረጓጎም

ሀ) የግንኙነቱ ቀመር

$$r = \frac{N \Sigma xy - (\Sigma x)(\Sigma y)}{\sqrt{N \Sigma x^2 - (\Sigma x)^2 \times N\Sigma y^2 - (\Sigma y)^2}}$$

ለ) የግንኙነቱ ውጤት አተረጓጎም

1.0	Perfect relationship
0.7 - 0.9	high relationshp
0.4 - 0.6	Moderate relationship
0.1 - 0.3	Low relationship
0	No relationship
- 1.0	perfect negative relationship
0.7 - 0.9	high negatvie relationship
- 0.4 - 0.6	moderate negative relationship
- 0.1 - 03	Low negative relationship

(Mehrens and Lehmann : 1991; 220 - 221)

አባሪ - 4

የግንኙነቱ ቀመር አሠራር

$$r = \frac{N \Sigma x y - (\Sigma x)(\Sigma y)}{\sqrt{N\Sigma x^2 - (\Sigma x)^2 \times N\Sigma y^2 - (\Sigma y)^2}}$$

$N = 9$

$\Sigma x = 25$

$\Sigma x^2 = 91$

$(\Sigma x)^2 = 625$

$\Sigma y = 40$

$\Sigma y^2 = 520$

$(\Sigma y)^2 = 1600$

$\Sigma xy = 175$

$$r = \frac{9 \times 175 - 25 \times 40}{\sqrt{9 \times 91 - 625} \times \sqrt{9 \times 520 - 1600}}$$

$$r = \frac{1575 - 1000}{\sqrt{194} \times \sqrt{3080}}$$

$$r = \frac{575}{772.99}$$

$$r = \underline{0.75}$$

አባሪ 5

በደሴና በደብረብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የአማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን የቀረበ መጠይቅ

መግቢያ፣ በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትምህርት ቢሮ ሥር ለአንደኛ ደረጃ መምህርነት የሚያሰለጥኑ ሁለት የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች አሉ።

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማም ለተቋሞቹ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማማላት መቻሉን ለማጥናት የሚያግዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው።

የጥናቱ ትኩረት ለተቋሞቹ የተዘጋጀው የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሳካት የሚያስችል ነውን ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በመሆኑ በመጠይቁ የተካተቱት ጉዳዮች በዚህ ዙሪያ እንዲመሠረቱ ተደርጓል።

የዚህ ጥናት ለውጤት መብቃትም ከእርስዎ ፈቃደኝነትና ቀና ትብብር ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው። በመሆኑም በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብበውና አገናዝበው ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጡ በአክብሮት እየጠየቅሁ፤ ለሚያደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

ማሳሰቢያ፡- በመጠይቁ ላይ ስምዎን መጻፍ አያስፈልግም

ክፍል አንድ - የግል ሁኔታ

እባክዎ ለሁሉም ጥያቄዎች በተዘጋጀው ቦታ ላይ ☑ ምልክት በማድረግ ምርጫዎን ያመልክቱ ረዘም ያለ መልስ ለሚያስፈልገው ደግሞ በክፍት ቦታዎች ላይ ማብራሪያውን ይጻፉ::

1/ የማሠልጠኛ ተቋሙ ስም_____

2/ ፆታ ወንድ ☐ ሴት ☐

3/ እድሜ 21-25 ☐ 26-30 ☐ 31-35 ☐

36-40 ☐ ከ40 በላይ ☐

4/ የትምህርት ደረጃ

የኮሌጅ ዲፕሎማ ☐ የማስትሬት ዲግሪ ☐

የመጀመሪያ ዲግሪ ☐ ሌላ ከሆነ ይጠቀስ_____

5/ የሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት

አቢይ_____ ንኡስ_____

6/ የአፍ መፍቻ ቋንቋ_____

7/ የአገልግሎት ዘመን_____

በመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ውስጥ _____

በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህርነት _____

በሌላ_____

8/ የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞችን የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍ ለማዘጋጀት ወይም ለማሻሻል በተጠራ ወርክሾፕ ተሳትፈዋል ?

ተሳትፌአለሁ ☐ አልተሳተፍኩም ☐

9/ መልስዎ 'ተሳትፌአለሁ' የሚል ከሆነ የወርክሾፑን ይዘት ባጭሩ ያስፍሩ::

_____

_____

_____

ክፍል ሁለት-አጠቃላይ ጉዳዮች

10/ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት በተቋሙ ውስጥ ይገኛል ?

ሀ/ ይገኛል ☐ ለ/ አይገኝም ☐

11/ የሚገኝ ከሆነ እንዴት ያገኙታል ?

ሀ/ ለመምህራን ይሰጣል ☐ ለ/በቤተመጻሕፍት ውስይ ጥቀመጣል ☐

12/ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ለሠልጣኞች የሚደርሰው እንዴት ነው ?

ሀ/ ለያንዳንዳቸው ይሰጣል ☐

ለ/ በቡድን መልክ ይሰጣል ☐

ሐ/ በቤተ መጻሕፍት ውስጥ ይቀመጣል ☐

13/ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመምህሩ መምሪያ አለ ?

ሀ/ አለ ☐ ለ/ የለም ☐

14/ ለ13ኛው ጥያቄ መልስዎ 'የለም' የሚል ከሆነ አለመኖሩ ያስከተለው ሁኔታ ምንድን ነው ?

ሀ/ የመምሪያው አለመኖር በሥራ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል ☐

ለ/ የመምህሩ መምሪያ ባለመኖሩ ያጋጠመ ችግር የለም ☐

ሐ/ የማስተማሪያ መጽሐፉ እንደ መምህሩ መምሪያ ስለሚያገለግል የመምሪያው አስፈላጊነት አይታይም። ☐

መ/ ሌላ ምክንያት ካለ ይጠቀስ_____

15/ መርሀ-ትምህርቱን ለማስተማሩ ሥራ በመመሪያነት ይገለገሉበታል ?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ እገለገልበታለሁ ☐

ለ/ በከፊል እገለገልበታለሁ ☐

ሐ/ አልገለገልበትም ☐

16/ ለ15ኛው ጥያቄ መልስዎ 'ሐ' ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ?

ሀ/ እምብዛም ስለማይረዳኝ ☐

ለ/ ከመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ጋር ግንኙነት ስለሌለው ☐

ሐ/ አስፈላጊነቱ ስላልታየኝ ☐

መ/ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ በቂ ስላልሆነ ☐

17/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ በትምህርት ዘመኑ ይጠናቀቃል ?

ሀ/ ይጠናቀቃል ☐ ለ/ አይጠናቀቅም ☐

18/ መልስዎ 'ለ' ከሆነ ሊጠናቀቅ የማይችለው በምን የተነሳ ነው ?

ሀ/ የይዘቱ ብዛትና የትምህርቱ ወቅት ባለመመጣጠኑ ☐

ለ/ ክፍለጊዜው ለክፍሎቹና ምዕራፎቹ በትክክል ባለመደልደሉ ☐

ሐ/ በትምህርት ክፍለ ጊዜ መባከን የተነሳ ☐

መ/ ሌላ ምክንያት_____

ክፍል ሶስት-መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን በተመለከተ

1/ በመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች የተፈለገውን ሥልጠና ተግባራዊ ለማድረግ ተስማሚ ናቸው።

ሀ/ በጣም እስማማለሁ ☐

ለ/ እስማማለሁ ☐

ሐ/ አልስማማም ☐

መ/ በጣም አልስማማም ☐

2/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማዘጋጀትና ለመጠቀም የሚያስችል ፅንስ ሀሣብ አካትቷል።

ሀ/ በጣም እስማማለሁ ☐

ለ/ እስማማለሁ ☐

ሐ/ አልስማማም ☐

መ/ በጣም አልስማማም ☐

3/ በመጽሐፉ ይዘት ውስጥ በሚገኙት መልመጃዎች ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው የቋንቋ ክሂል ነው ?

ሀ/ ለመናገር ☐

ለ/ ለማንበብ ☐

ሐ/ ለመጻፍ ☐

መ/ ለሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ☐

4/ ለ3ኛው ጥያቄ የሰጡት መልስ 'መ' የሚል ከሆነ የክሂሎች ቅንጅት አጥጋቢ በመሆኑ ይስማማሉ ?

ሀ/ በጣም እስማማለሁ ☐

ለ/ እስማማለሁ ☐

ሐ/ አልስማማም ☐

መ/ በጣም አልስማማም ☐

5/ በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የየምዕራፉ የትምህርት ይዘቶች በይበልጥ አመቺ የሚሆኑት ለየትኛው የማስተማር ዘዴ ነው ? (ከአንድ በላይ መልስ ካለ በሁሉም ላይ ምልክቱን ያድርጉ)

ሀ/ ለገለፃ ዘዴ ☐ ሠ/ ሌላ ካለ ይግለፁ_____

ለ/ ለውይይት ዘዴ ☐

ሐ/ ለግልሥራ ዘዴ ☐

መ/ ለድርጊት ዘዴ ☐

6/ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የማስተማር ዕቅድ አዘገጃጀት መግለጫዎች የተሟሉ ናቸው፡

ሀ/ በጣም እስማማለሁ ☐

ለ/ እስማማለሁ ☐

ሐ/ አልስማማም ☐

መ/ በጣም አልስማማም ☐

7/ በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ-ውስጥ ያሉት የትምህርት ይዘቶች አዳዲስ ግንዛቤን በማስጨበጥ ረገድ ወቅታዊ አይደሉም፡፡

ሀ/ በጣም እስማማለሁ ☐

ለ/ እስማማለሁ ☐

ሐ/ በጣም አልስማማም ☐

መ በጣም አልስማማም ☐

8/ በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘት ውስጥ የተጠቀሰው የማስተማር ዘዴ ዓይነት በየትኛው ሊመደብ ይችላል ?

ሀ/ በመምህር - መራሽ ☐

ለ/ በተማሪ - መራሽ ☐

ሐ/ በሁለቱም ☐

9/ በመጽሐፉ ውስጥ በቀረቡት ይዘቶች አማካይነት የሠልጣኞችን የዕውቀት፣ የክሂልና አመለካከት ባህሪያትን መቅረጽና ማዳበር ይቻላል።

ሀ/ በጣም እስማማለሁ ☐

ለ/ እስማማለሁ ☐

ሐ/ አልስማማም ☐

መ/ በጣም አልስማማም ☐

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምርጫዎን ☐ ምልክት በማድረግ ያመልክቱ

<u>የመልስ ቁልፎች</u>

4- በጣም እስማማለሁ

3- እስማማለሁ

2- አልስማማም

1- በጣም አልስማማም

ተ. ቁ.	ጥያቄዎች	አማራጮች			
		4	3	2	1
10	በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች ሠልጣኞችን የሚስቡ ናቸው፡፡				
11	በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የተለያዩና ብቃት ያላቸው ሆነው አልተዘጋጁም፡፡				
12	በመጽሐፉ ይዘት አማካይነት የተጠቀሰው የማስተማር ዘዴ ሠልጣኞችን በቡድንና በግል እንዲሠሩ የሚያደርግ ነው፡፡				
13	የመማሪያ-መጽሐፉ ሠልጣኞችን ለአንደኛ ደረጃ መምህርነት የሚያዘጋጅ አይደለም፡፡				
14	የመጽሐፉ ይዘቶች በተገቢው ቅደም ተከተል የቀረቡ ናቸው፡፡				
15	በመጽሐፉ ይዘቶች ውስጥ ስለ አንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መጻሕፍት ትውውቅ በበቂ ሁኔታ አልቀረበም፡፡				
16	በመጽሐፉ ይዘት ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ሠልጣኞቹ ትምህርቱን መከታተላቸውን ለመገምገም ያስችላሉ፡				
17	የመጽሐፉ የትምህርት ይዘቶች ለሠልጣኞች ደረጃ የሚመጥኑ አይደሉም፡፡				

ክፍል አራት- <u>የመርሀ-ትምህርቱና መማሪያ መጽፉን ግንኙነት በተመለከተ</u>

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል የሚስማሙበትን ☑ ምልክት በማድረግ ይመልሱ፡፡ በክፍት ቦታዎች ላይ ደግሞ ተገቢውን መልስ ይጻፉ፡፡

18/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ መርሀ-ትምህርቱን በመከተል የተዘጋጀ ነው ?

ሀ/ መሉ በሙሉ ነው ☐

ለ/ በከፊል ነው ☐

ሐ/ አይደሉም ☐

19/ ለ18ኛው ጥያቄ መልስዎ 'ሀ' ወይም 'ለ' ከሆነ የሁለቱ ግንኙነት የተመሠረተው በየትኛው ምክንያት ነው ?

ሀ/ በርዕሰ ቅደም ተከተል መመሳሰል ☐

ለ/ በይዘትና አላማ ስምረት ☐

ሐ የተወሰኑ ይዘቶች በሁለቱም ውስጥ ስለሚገኙ ☐

መ/ ሌላ ከሆነ ይጠቀስ_____

20/ ለ18ኛው ጥያቄ መልስዎ 'አይደለም' የሚል ከሆነ የልዩነቱ መንስኤ ምንድን ነው ?

ሀ/ የመርሀ-ትምህርቱ ይዘት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባለመካተቱ ☐

ለ/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ የቋንቋ ደረጃ አለመመጠኑ ☐

ሐ/ የሁለቱ የት/መሣሪያዎች የትኩረት አቅጣጫ በመለያየቱ ☐

መ/ የመርሀ-ትምህርቱ አላማ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ባለመንፀባረቁ ☐

21/ በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በመርሀ-ትምርቱ ላይ ላልተጠቀሱ አላማዎች የቀረቡ ይዘቶች አሉ ?

ሀ/ አሉ ☐ ለ/ የሉም ☐

22/ ለ21ኛው ጥያቄ መልስዎ 'አሉ' የሚል ከሆነ ርዕሶችን ብቻ ያስፍሩ

_____

_____

23/ የመማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርቱን ዓላማ ከማስፈጸም አንፃር ሲመዘን ሁለቱ የትም/መሣሪያዎች (መርሀ-ትምህርትና መማሪያ መጽሐፉ) ግንኙነት አላቸው?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ አላቸው ☐

ለ/ በከፊል አላቸው ☐

ሐ/ ግንኙነት የላቸውም ☐

24/ መልስዎ 'ሐ' ከሆነ በየትኛው ምክንያት ይመስልዎታል ?

ሀ/ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ የመርሀ-ትምህርት አላማ ባለመከተሉ ☐

ለ/ የመርሀ-ትምህርቱ አላማ በግልጽ ባለመቀመጡ ☐

ሐ/ አላማና ይዘት ባለመጣጣማቸው ☐

መ/ ሌላ ከሆነ ይጠቀስ_____

25/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘቶች የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ግብ ለማስመታት ያስችላሉ ?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ ያስችላሉ ☐

ለ/ በከፊል ያስችላሉ ☐

ሐ/ አያስችሉም ☐

26/ መልስዎ 'ሐ' የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው ?

ሀ/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘት የቋንቋ እውቀትን አያዳብርም ☐

ለ/ ይዘቱ አዳዲስ የማስተማር ዘዴና ስልትን አያስተዋውቅም☐

ሐ/ ይዘቱ ለክሂል መዳበር ትኩረት አይሰጥም ☐

መ/ ይዘቱ ለመምህርነት ሙያ በበቂ ሁኔታ አያዘጋጅም ☐

ሠ/ በሁሉም ምክንያቶች የተነሳ ☐

27/ ስለተቋሙ የአማርኛ ቋንቋ የትምህርት መሣሪያዎች (መርሀ ትምህርትና መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ) ያለዎትን አጠቃላይ አስተያየት ሰፋ አድርገው ቢያሰፍሩ ?

_____

_____

_____

_____

_____

አባሪ 6

በደሴና በደብረብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች በትምህርት ላይ ለሚገኙ ሠልጣኞች የቀረበ መጠይቅ

መግቢያ፡- በአማራው ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የትም/ቢሮ ሥር ለ1ኛ ደረጃ መምህርነት የሚያሠለጥኑ ተቋሞች እንዳሉ ይታወሳል፡፡

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማም ለነዚህም ተቋሞች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሟላት መቻሉን ለማጥናት የሚያግዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡

የጥናቱ ውጤት መሳካትም በማስተማሪያ ዝግጅቱ ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ለመጠቆም ይረዳል፡፡ ለእንደዚህ ዓይነቱ ጥናት ደግሞ የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ሠልጣኞች የሚሠጡት እውነተኛና ትክክለኛ አስተያየት በእጅጉ ጠቃሚ ነው፡፡

ስለዚህ የአንተ/አንቺ/ ፈቃደኝነትና ቀና ትብብር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብበህ/አንብበሽ/ ትክክለኛውን ምላሽ እንድትሠጥ/እንድትሠጪ/ እየጠየቅሁ፣ ለትብብርህ/ለትብብርሽ/ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

ክፍል አንድ - የግል ሁኔታን በተመለከተ

በምርጫ መልክ ለቀረቡት ጥያቄዎች የትክክለኛውን መልስ ፊደል በመክበብ ለሌሎች፤ ደግሞ በክፍት ቦታው ላይ በመፃፍ መልስ/መልሽ/

1/ የማሠልጠኛ ተቋሙ ስም_____

2/ ፆታ ሀ/ ወንድ ለ/ ሴት

3/ ዕድሜ ሀ/ 15-19 ለ/ 20-29 ሐ/ 25-29 መ/ ከ30 በላይ

4/ የአፍ መፍቻ ቋንቋህ /ቋንቋሽ/

ሀ/ አማርኛ

ለ/ ትግርኛ

ሐ/ ኦሮምኛ

መ/ አፋርኛ

ሠ/ ሌላ ከሆነ ይገለጽ_____

5. የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉን የምታገኙት እንዴት ነው ?

ሀ/ ለእያንዳንዳችን ይሠጠናል

ለ/ በቡድን ይሠጠናል

ሐ/ በቤተ መፃሕፍት ውስጥ ይቀመጣል

መ/ ሌላ መንገድ ካለ ይገለጽ_____

ክፍል ሁለት - አጠቃላይ ጉዳዮች

1/ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ይዘቶች ለመምህርነት ሥልጠና ተስማሚ ናቸው ?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ ተስማሚ ናቸው

ለ/ በመጠኑ ተስማሚ ናቸው

ሐ/ ተስማሚ አይደሉም

2/ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት የትምህርት ይዘቶች አዳዲስ ግንዛቤን ከማስጨበጥ አንፃር ወቅታዊ ናቸው ?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ ወቅታዊ ናቸው

ለ/ በመጠኑ ወቅታዊ ናቸው

ሐ ወቅታዊ አይደሉም

3/ የይዘቶቹ መልዕክቶች ግልጽ ናቸው ?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ ግልጽ ናቸው

ለ/ በመጠኑ ግልጽ ናቸው

ሐ/ ግልጽ አይደሉም

4/ ለማስተማሪያነት የተመረጡት ይዘቶች የቋንቋ ደረጃ እንዴት ነው ?

ሀ/ በጣም ከባድ ነው

ለ/ ከባድ ነው

ሐ/ ቀላል ነው

መ/ በጣም ቀላል ነው

5/ በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘት ውስጥ ያሉት መልመጃዎች የተሠጠውን ትምህርት ለመረዳት በቂ ናቸው ?

ሀ/ ሙሉ በሙሉ በቂ ናቸው

ለ/ በመጠኑ በቂ ናቸው

ሐ/ በቂ አይደሉም

6/ መልስህ /መልስሽ/ 'በቂ አይደሉም' ከሆነ ምክንያቱ የትኛው ነው ?

ሀ/ መልመጃዎቹ ግልጽ አይደሉም

ለ/ መልመጃዎቹ በይዘቶቹ ላይ ተመስርተው አልተዘጋጁም

ሐ/ የመልመጃዎቹ አጠያየቅ ስልት ውሱን ነው

መ/ መልመጃዎቹ በቁጥር አናሳ ናቸው

ሠ/ ሌላ መልስ ካለ ይገለጽ_____

7/ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በአብዛኛው ትኩረት የሚሠጠውና ልምምድ የሚካሄድበት በየትኛው ተግባር ነው ?

ሀ/ በመናገር

ለ/ በማንበብ

ሐ/ በመፃፍ

መ/ በሁሉም የቋንቋ ክሂሎች

8/ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚከናወነው በየትኛው መንገድ ነው ?

ሀ፡ መምህሩ የሚነግሩንን በመቀበል ላይ ብቻ ያተኮረ ነው

ለ/ በእኛው ተሳትፎ ላይ ያተኮረ ነው

ሐ/ በእኛና በመምህሩ እንደልብ ሀሣብ በመለዋወጥ ላይ ያተኮረ ነው

መ/ የመምህሩን ገለፃ በማዳመጥና አንዳንድ ጊዜ መልክ በመስጠት ላይ ያተኮረ ነው

9/ በመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተጠቆሙት የማስተማር ዘዴ ለወደፊቱ ተግባርህ/ተግባርሽ/ ምን ያህል ይጠቅምሀል/ይጠቅምሻል/ ?

ሀ/ በከፍተኛ ደረጃ ይጠቅመኛል

ለ/ በዝቅተኛ ደረጃ ይጠቅመኛል

ሐ/ አይጠቅመኝም

10/ በምትማርበት /በምትማሪበት/ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አዘገጃጀትና አጠቃቀም የቀረበው መግለጫ ብቃት አለው ?

ሀ/ በከፍተኛ ደረጃ አለው

ለ/ በዝቅተኛ ደረጃ አለው

ሐ/ ብቃት የለውም

11/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ስለማስተማር ዕቅድ አዘገጃጀት በሚገባ ለመረዳት አስችሎሀል /አስችሎሻል/ ?

ሀ/ በከፍተኛ ደረጃ አስችሎኛል

ለ/ በዝቅተኛ ደረጃ አስችሎኛል

ሐ/ አላስቻለኝም

12/ በመጽሐፉ ውስጥ ስለ አንደኛ ደረጃ /1ኛ-4ኛ/ የአማርኛ ቋንቋ መጻሕፍት አጠቃቀም በቂ ሀሳብ አግኝተሃል/አግኝተሻል/?

ሀ/ በከፍተኛ ደረጃ አግኝቻለሁ

ለ/ በዝቅተኛ ደረጃ አግኝቻለሁ

ሐ/ አላገኘሁም

13/ የተማራችሁበት መጽሐፍ የተዘጋጀበት የቋንቋ አጠቃቀም ይከብዳል ወይስ ይቀላል ?

ሀ/ በጣም ከባድ ነው

ለ/ ከባድ ነው

ሐ/ ቀላል ነው

14/ ከመጽሐፉ ባገኛችሁት ሐሳብ መሠረት በቡድንና በግል የመሥራት ልምድን አዳብራችኋል ?

ሀ/ በከፍተኛ ደረጃ አዳብረናል

ለ/ በዝቅተኛ ደረጃ አዳብረናል

ሐ/ አላዳበርንም

15/ በተቋሙ ውስጥ ባገኛችሁት የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀት የቱን ያህል ትተማመናላችሁ ?

ሀ/ በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ

ለ/ ከፍተኛ በሆነ ደረጃ

ሐ/ ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ

መ/ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ

16/ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይነት ለመምህርነት ሙያ ያላችሁ የዝግጅት ብቃት ምን ያህል ነው ?

ሀ/ በጣም ከፍተኛ

ለ/ ከፍተኛ

ሐ/ ዝቅተኛ

መ/ በጣም ዝቅተኛ

17/ ስለ አማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ያለህን/ያለሽን/ አጠቃላይ አስተያየት ዘርዘር አድርገህ/አድርገሽ/ አስፍር/አስፍሪ/፡፡

_____

_____

_____

_____

_____

_____

በድጋሜ አመሰግናለሁ፡፡

አባሪ 7

ለትምህርት ባለሙያው የቀረበ ቃለ መጠይቅ

የትምህርት ደረጃ_____

አጠ/አገልግሎት _____

በመምህርነት_____

በር/መምህርነት_____

በትም/ቢሮ አባልነት_____

አሁን ያሉበት የሥራ ክፍል_____

በክፍሉ ያለዎት የኃላፊነት ደረጃ_____

መሪ ጥያቄዎች

1/ በክልሉ ውስጥ ላሉት የ1ኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የዝግጅት ሂደትን በተመለከተ፡-

ሀ/ በዝግጅቱ የተሳተፉት ሰዎች ከምን ከምን ክፍል የተውጣጡ ነበሩ?

ለ/ ግለሰቦቹ የተመረጡበት መመዘኛ ምን ነበር ?

ሐ/ የአዘጋጂዎቹን የትም/ደረጃና የሥራ ልምድ ቢገልጹልኝ ?

2/ በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ምን ምን ነበሩ? የችግሮቹን ዓይነትና የተሰጡትን መፍትሔዎች ቢያብራሩልኝ ?

3/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ለሠልጣኞች ተፈላጊውን የባህሪይ ለውጥ ሊያስገኝ እንዲችል ምን ጥረት ተደርጓል ?

4/ በማዕከል ደረጃ በተዘጋጀው መርሀ-ትምህርትና በክልሉ በተዘጋጀው የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ መካከል ስላለው ግንኙነት ቢያብራሩልኝ ?

5/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ስለ ጥንካሬውና ድክመቱ የተገኘ የመረጃ ምላሽ (feedback) ካለ ቢገልጹልኝ ?

6/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘት የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሳካት የሚችል ስለመሆኑ አስተያየት ቢሰጡበት?

7/ አዲሱ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ሠልጣኞችን ለመምህርነት ሙያ በሚገባ የሚያዘጋጅ ነው ?

8/ ተጨማሪ አስተያየት አለዎት ?

አመሰግናለሁ።

አባሪ 8

ለመጽሐፍ አዘጋጁ የቀረበ ቃለመጠይቅ

የትምህርት ደረጃ_____

አጠ/አገልግሎት_____

በመምህርነት_____

በሌላ_____

የሠለጠኑበት የትም/ዓይነት

ዋና ትምህርት_____

ንዑስ ትምህርት _____

መሪ ጥያቄዎች

1/ የመምህራን ማሠልጠኛዎቹን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ለማዘጋጀት እርስዎ እንዴት እንደተመረጡ ቢገልጹልኝ ?

2: ለዚህ ሥራ ከመመረጥዎ በፊት በመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ልምድ ነበረዎት ?

3/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት ዋና አላማ ምን ነበር ?

4/ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ይዘቶች (ጽሑፎች) የተመረጡት እንዴት ነበር ?

5/ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው ምን ጥረት ተደርጓል ?

6/ መጽሐፉ ሠልጣኞችን ለመምህርነት ሙያ ለማዘጋጀት እንዲችል ምን ያህል ታስቦበታል ?

7/ ተጨማሪ አስተያየት አለዎት ?

አመሰግናለሁ

አባሪ 9

የትምህርት ባለሙያው ቃለመጠይቅ መልስ

1-ጥያቄ - በክልሉ ውስጥ ላሉት የ1ኛ ደረጃ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ የዝግጅት ሂደትን በተመለከተ፡-

ሀ) በዝግጅቱ የተሳተፉት ሰዎች ከምን ከምን ክፍል የተውጣጡ ነበሩ ?

ለ) ግለሰቦቹ የተመረጡበት መመዘኛ ምን ነበር ?

ሐ) የአዘጋጅዎቹን የትም/ደረጃና የሥራ ልምድ ቢገለጹልኝ ?

መልስ - በዝግጅቱ የተሳተፉት ከደብረ ብርሃን መምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ከባህር ዳር መምህራን ኮሌጅ ነበር። በቢሮው ውስጥ ያሉ የትም/ባለሙያዎችም ተሳትፈዋል።

- እንዴት ተመረጡ ላልከኝ ያላቸው የትም/ደረጃና የማስተማር ልምድ አንዲሁም የመጽሐፍት ዝግጅት ልምድ ነው። ያስመረጣቸው ለሙያው ያላቸው አመለካከትም ጭምር።

ጥያቄ - ከዚህ በፊት በመጽሐፍት ዝግጅት ሥራ የተሳተፉ ነበሩ ማለት ነው ?

መልስ - አዎ ለምሣሌ ከደሴ መም/ማሠልጠኛ ተቋም የመጣው መምህርና ከደብረ ብርሃን መም/ማሠልጠኛ ተቋም የመጣው በሲለበስና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ተሳትፈዋል። ትግራይ ድረስ ሄደው በዝግጅት ሥራ ተሳትፈዋል። ቢሮ ውስጥ ያሉትም ልምድ ያላቸው ናቸው።

ጥያቄ - እሽ ይቀጥሉ !

መልስ - የትም/ደረጃቸውን በተመለከተ ከሌሎቹ ቢ.ኤ ያለቸው ከሌሎቹ ደግሞ ኤም.ኤ ያላቸው ናቸው። የተወሰኑት በቅድሚያ ረቂቁ አዘጋጅተው ሌሎቹ በጋራ ሆነው አይተውት የማሻሻያ ሀሳብ ሰጥተውበታል።

ከተቋሙ የተውጣጡ አባላትም መጥተው ተነጋግረውበት አሻሽለውት ሥራ ላይ ውሏል።

ጥያቄ - በመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ዝግጅት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ምን ነበሩ? የችግሮቹ ዓይነትና የተሰጡትን መፍትሄዎች ሲያብራሩልኝ ?

መልስ - አንዱ ችግር የጊዜ እጥረት ነው። ሌላው ሰዎችን ከየቦታው አሰባስበን ነው የምንሠራው። ቢሮ ውስጥ በቂ ባለሙያ አልነበረንም። ባለሙያዎች ያገኘነው በኋላ ነው። የሰው ኃይል የገንዘብና የልምድ እጥረት ነበረብን። የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ልምድ አለመኖር ማለቴ ነው። ብዙዎቹ የሜቶዶሎጂ ችግር አለባቸው አዘጋጂዎቹም የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ልምድ ውሱንነት ነበራቸው።

ጥያቄ - ታዲያ ይህን ችግር እንዴት ተወጣችሁት ?

መልስ - "በኮሚሽን ራይተርስ" በመጠቀም ትርፍ ጊዜን መሰዋዕት በማድረግ እርስ በርስ የልምድ ልውውጥ በማድረግ ነው። የተወጣነው። "ኦሬንቴሽን" በመስጠት ስለ ቋንቋ ሁኔታና የሜቶዶሎጂ አጠቃቀም "ቢጋር" በመስጠት ለማስተካከል ሞክረናል። የክልልና የማዕከል ሀይልን አስተባብረናል።

ጥያቄ - ቢጋሩ አሁን በጅዎ ይገኛል ?

መልስ- ለጊዜው እንኳ በእጄ የለም። በኋላ ልንፈልገው እንችላለን።

ጥያቄ - ከማዕከል ለምሣሌ ከሥርዓተ ትምህርት ኢንስቲትዩት ያገኛችሁ ድጋፍ የለም ?

መልስ - በአይ-ሲ-ዲ-አር (ICDR) ሲለበስ ሲያዘጋጅ መምህራንን ስለሚጠራ ሲለበስ ደግሞ ወደ መጽሐፍ የሚለውጥበትን ሁኔታ እግረ መንገዱን ስለሚያሳውቅ ለእኛም ጠቀሜታ አለው። የእርሱ "ኮንትሪቢዩሽን" ዋጋ አለው ማለቴ ነው።

3 - ጥያቄ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ለሠልጣኞች ተፈላጊውን የባህሪይ ለውጥ ሊያስገኝ እንዲችል ምን ጥረት ተደርጓል ?

መልስ - ሥርዓተ-ትምህርት ዝም ብሎ አይጽፍም ከነበረው ተነስቶ ምን ጠንከራ ጐን አለው ከሚለው ይነሳል። "ሲቹየሽን አናሊሲስ" ይታያል። ፀሐፊዎቹም መምህራን ስለነበሩ ምን እጥረት አለ ? እንዴት እናስወግደዋለን ? በማለት ነው የጻፉት። በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ላይ የተቀመጠ ሠልጣኙ ሲለበሱን ሲያጠናቅቅ ምን ይጠበቅበታል ? የሚል "ኦብጀክቲቭ" ስላለ እነዚያ መነሻ ሆነው የተሻለ ልምድ ያላቸውን ሰዎች ለመጠቀም ስለተሞከረ ዝግጅቱ ተገቢውን የባህርይ ለውጥ ያመጣል ተብሎ ይገመታል። የተወሰኑ "ሳይኮሎጂካዊና ፔዳጐጂካዊ" ሁኔታዎች ታይተዋል የነበረውን እጥረት ለማስወገድ ልምድ ባላቸው ሰዎች መጠቀሙ በልዩ ልዩ አውደ ጥናቶች ሥራዎቹ እንዲተቹ ማድረግ። የመጽሐፉን ጥራት ይጨምራል። ይህም ተፈላጊውን የባህርይ ለውጥ ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል።

4-ጥያቄ በማዕከል ደረጃ በተዘጋጀው መርሀ-ትምህርትና በክልሉ በተዘጋጀው የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ መካከል ስላለው ግንኙነት ማብራሪያ መስጠት፡

መልስ- መጽሐፉ ሲዘጋጅ "ስታንዳርዱን" ለማስጠበቅ ሲባል ሲለበሱን ተከትሎ ነው። ልዩነት ቢኖር ቅደም ተከተሉን ማስተካከልና ድግግሞሹን ማስወገድ ነው። በርግጥ ይህን ጥያቄ መመህራኑ ቢመልሱት የተሻለ ነበር ሥራውን ስከታተል እንደምረዳው ግን በአጠቃላይ በሁለቱ መካከል ግንኙነት እንዳለ አውቃለሁ።

5- ጥያቄ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ስለ ጥንካሬውና ድክመቱ የተገኘ የመረጃ ምጣባ (Feedback) ካለ ቢገልጹልኝ ?

መልስ - አንድ ዓመት ካስተማሩበት በኋላ መምህራንን ሰብስበን እናጋግረናል። የማሻሻያ ሀሳብ ሰጥተውበት ነበር። ነገር ግን ወደ ሌላ ስላተኮርን በነርሱ ሀሳብ መሠረት ለማሻሻል የነበረውን ዕቅድ ሥራ ላይ አላዋልነውም።

ከዚያ ወዲህም ልናሻሽለው አልቻልንም። የተለያዩ የትም/ዓይነቶች በአንድ ላይ የሚሰጡበት "ኢንቲግሬሽን" አሠራርም ይኖራል የሚል ሀሳብ አለ።

ጥያቄ - ይህ ኢንቲግሬሽን ያሉት አሠራር ተግባራዊ ቢሆን አሁን ያሉት የማስተማሪያ መጻሕፍት ከጥቅም ውጭ ይሆናሉ ማለት ነው እንዴ ?

መልስ - አይ ! ይህ ሳይሆን የየትምህርት ዓይነቶቹ ፅንሰሀሳቦች ተደርድረው የጋራ የሆኑ ነገሮች ከተለዩ በኋላ እነዚያን ለማንሳት የሚቻልበት ሁኔታ ይቀየሳል ማለት ነው። በርግጥ በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ለውጥ ሊኖር ይችል ይሆናል። ነገር ግን ዝርዝር አሠራሩ ወደፊት በተግባር ሲታይ የሚታወቅ እንጂ ካሁኑ እንዲህ ይሆናል ማለት አይቻልም።

6- ጥያቄ የመማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፉ ይዘት የመርሀ-ትምህርቱን አላማ ለማሳካት የሚችል ስለመሆኑ አስተያየት ቢሰጡበት ?

መልስ - ይህ ጥያቄ ቅድም የባህሪይ ለውጥ ያስገኛል ወይ ብለህ ከጠየቅከኝ ጋር የሚመሳሰል ነው። እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ መመለስ ያስቸግራል። ብዙ መረጃዎችን ማገናዘብ ያስፈልጋል። ዝም ብዬ ብመልስ ግን የራሴ አመለካከት ብቻ ይሆናል። ቢሆንም የማውቃቸውን ጉዳዮች ለመግለጽ እሞክራለሁ።

- እንዲህ ዓይነቱ ነገር ሊታወቅ የሚችለው ተገቢ የሆነ ጥናት በማካሄድ ነው በመስክ እይታ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ የጊዜ እጥረትም አለ። መምህራንን አነጋግሬአለሁ ስላልከኝ ከነርሱ ብዙ ነገር እንደምታገኝ እገምታለሁ። አጠቃላይ ሁኔታው ሲታይ ግን አዘገጃጀቱ ጥሩ ነው። በመስክ ሥራ ላይ የተመሠረተና የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞቹ የተሳተፉበት በመሆኑ "ፖሲቲቭ ኢፌክት" አለው ለማለት እችላለሁ።

7 - ጥያቄ አዲሱ የማስተማሪያ መጽሐፍ ሠልጣኞችን ለመምህርነት ሙያ በሚገባ የሚያዘጋጅ ነው ?

መልስ - ይህ ጥያቄ ከላይኛው ጋር የተያያዘ ነው መልሱን በቀጥታ ለመስጠት በተግባር ማየት ያስፈልጋል። አለበለዚያ መልሱ "እርኒየን" ነው የሚሆነው። የትምህርቱን አላማና አሠልጣኞችን ብቃት ማወዳደር ያስፈልጋል። በአስተያየት ደረጃ ከተነጋገርን ግን ከዚህ በፊት ማስተማሪያው በማዕከል ተዘጋጅቶ ይላክ ነበር አሁን ግን በአካባቢው ደረጃ የተቋም መምህራን የተሳተፉበት በመሆኑ የተሻለ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል። እንዲህ ነው ብሎ መወሰን ግን ያስቸግራል።

8- ጥያቄ ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት ?

መልስ - የኔ ተጨማሪ አስተያየት ምናልባት ለአሁኑ ሥራህ ላይጠቅምህ ይችላል። ግን እንድታስብበት ነው። እኔ ለምሣሌ የማስተርስ ጥናቴን የሠራሁት በካሪኩለም በእንግሊዝኛ ትምህርት ላይ ነው። እዚያ ውስጥ ያየኋቸው ችግሮችና የጠቆምኩዋቸው መፍትሄዎች ነበሩ። ጥናቴን ሥርዓተ ትምህርት ኢንስቲትዩት ቢጠቀምበት ደስ ይለኝ ነበር። እነዚያ ችግሮች አሁንም በእንግሊዝኛ መጻሕፍት ውስጥ አሉ። የእንተም ጥናት ለወደፊቱ ሥራ ስለሚጠቅም ለክልሉ ትምህርት ቢሮና ለሌሎቹም ካልተሰራበት ዩኒቨርስቲ መቀመጡ ብቻ ዋጋ የለውም።

አባሪ 10

የመጽሐፍ አዘጋጁ ቃለመጠይቅ መልስ

1- ጥያቄ የመምህራን ማሠለጠኛዎችን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ለማዘጋጀት እንዴት እንደተመረጡ ቢገልጹልኝ ?

መልስ - በ1987 ዓ.ም አዲሱን የትምህርት ፖሊሲ መነሻ በማድረግ አሮጌዎቹ መጻሕፍት እንዲቀየሩ ተባለ። የክልሉ ትም/ቢሮ በየትምህርት ዓይነቶቹ አዳዲስ መጻሕፍት እንዲዘጋጁ ለተቋሞች ኃላፊነት ሰጥቶ ነበር። ለደብረብርሃን የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ዝግጅት ደረሰው። እኔም በዚያን ጊዜ በተቋሙ ውስጥ አማርኛ ስለማስተማር ከሌሎች ሁለት ባልደረቦቼ ጋር እንድናዘጋጅ ተደረገ። በወቅቱ አማርኛ የምናስተምረው ሶስታችንም አዘጋጀን እንጅ እኔ በግሌ አልተመረጥኩም።

2- ጥያቄ ለዚህ ሥራ ከመመረጥዎ ይቅርታ! ይህን ሥራ ከማከናወንዎ በፊት የመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ልምድ ነበረዎት ?

መልስ - ልምድ ስላልከው ጉዳይ እኔ እንኳን በዚያን ጊዜ ልምድ አልነበረኝም። ከእኔ ጋር መጽሐፉን ያዘጋጁት ሁለት ባልደረቦቼ ግን አላቸው። በመጽሐፍ ዝግጅትና ማሻሻያ ሴሚናሮች ተሳትፈዋል። በክልልም በአገር አቀፍም ደረጃ አንዱ እንዲያውም መርሀ-ትምህርቱን የመምህራን ማሠልጠኛውን የአማርኛውን ማለቴ ነው አዲስ አበባ ሄዶ አዘጋጅቷል።

3- ጥያቄ በየትኛው ደረጃ ለሚዘጋጀው መጽሐፍ ነው ሴሚናር የተሳተፉት ?

መልስ - ለአንደኛ ደረጃ አንዱ እንዲያውም ትግራይ ድረስ ተመርጠ ሄዶ መጽሐፍ አዘጋጅቷል።

4- ጥያቄ የገለፁልኝን የተቋሙን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ ስታዘጋጁ ዋና አላማችሁ ምን ነበር ?

መልስ - የዝግጅቱ አላማ አዲሱን የትምህርት ፖሊሲ መሠረት በማድረግ ላይ ነዋ፡፡ ለመምህርነት ሥልጠና የሚያገለግል አዲስ መጽሐፍ አዘጋጁ ተባልን፡፡ መርሀ-ትምህርቱን መሠረት አድርገን አዘጋጀን፡፡ በዝግጅቱ ወቅት ቋንቋውን ማስተማርና ስለቋንቋው ማስተማር የሚሉትን ጉዳዩች ትኩረት ሰጥተናል፡፡ የቀድሞውን መጽሐፍም መነሻ አድርገናል፡፡ የምናሻሽለውን አሻሽለን አዘጋጀን፡፡

5- ጥያቄ ቋንቋውንና ስለቋንቋው ማስተማር ያሉትን ቢያብራሩልኝ

መልስ - እሺ! ይህን ስል ለምሣሌ አማርኛ ቋንቋችን ነው፡፡ በማለት ሁሉንም የሚያውቁ ይመስላቸዋል፡፡ ግን የሰዋስውን ሁኔታ የቋንቋውን ታሪክ ማወቅ አለባቸው፡፡ ችሎታቸውን እንዳያዳብሩ ደግሞ የቋንቋውን ክሂሎች ማወቅ አለባቸው ይህ ሲባል ደግሞ የማስተማር ዘዴው ይረሳል ማለት አይደለም፡፡ ለዚያ ነው የሚዘጋጁት፡፡ እሽ! ገባኝ አሁን ወደሚቀጥለው ልሸጋገር፡፡

6- ጥያቄ በማስተማሪያ ጽሐፉ ውስጥ ያሉት ጽሑፎች እንዴት እንደተመረጡ ቢገልጹልኝ፡፡

መልስ - ጽሑፎቹ የተመረጡት በመርሀ-ትምህርቱ መነሻነት ተስማሚነታቸው እየታየ ነው፡፡ በቀድሞው መጽሐፍ ውስጥ የነበሩትን እያየን እያሻሻልን በአዲሱ ውስጥ እንዲገቡ አድርገናል፡፡ ከወርክሾፕ ተሳታፊዎች በቀረበው ሀሳብ መሠረት ደግሞ የተሻሻሉም የተጨመሩም ጽሑፎች አሉ፡፡

7 - ጥያቄ ማስተማሪያ መጽሐፉ ከመርሀ-ትምህርቱ ጋር ግንኙነት እንዲኖረው ምን ጥረት ተደርጓል ?

መልስ - አዎ ደጋግሜ እንደነገርኩህ የሁለቱ ግንኙነት ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ሠልጣኙ በቅርበ ፈቺ የማስተማር ዘዴ ራሱ በተለያዩ መንገዶች እየተሳተፉ እንዲማማሩ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ በርግጥ በአገር አቀፍ መርሀ-ትምህርት መሠረት ትምህርቱ የሚሰጠው ለ2 ክ/ጊዜ ብቻ ነው፡፡

በክልሉ ግን ለ3 ክ/ጊዜ እንዲሰጥ በመባሉ ተጨማሪ ይዘቶች ተቀምጠዋል። ቢሆንም ግን ግንኙነቱን የሚያፋልስ አይመስልም።

8- ጥያቄ እንግዲህ እስካሁን ከሰጡኝ ማብራሪያ መጽሐፉ ሠልጣኞችን ለመምህርነት ሙያ በሚገባ ያዘጋጃል ማለት ይቻላል ?

መልስ - እኛ እንግዲህ ያዘጋጃል ብለን ነው የምንገምተው የተቻለንን ያህል ሞክረናል። ምንም እንኳ ጊዜው አጭር ቢሆን ሌሎች የተቋም መምህራን ደግሞ በወርክሾፕ ጊዜ ሐሳቡን አዳብረውታል።

9 - ጥያቄ ለወደፊቱስ መሻሻል ያለበት ይመስልዎታል ?

መልስ - እሱማ ለምን አይሻሻል። በአንድ ወቅት የተሠራ ነገር የተሟላ ነው ማለት አይቻልም። እንደምታውቀው፣ መማሪያ-ማስተማሪያ ነው የሚለው ለመምህሩና ለተማሪው ለየብቻ መዘጋጀት ነበረበት። የጊዜ ማጠር ነው እንጂ የመምህሩ መምሪያም አልተዘጋጀም መጽሐፉም ለእያንዳንዱ ሠልጣኝ አልደረሰም። ከፍተኛ እጥረት አለ። በየወቅቱ እየተገመገመም ሊሻሻል ይገባል።

10 - ጥያቄ ከዚህ በተጨማሪ የሚነግሩኝ አለ ?

መልስ - ከዚህ ሌላ የምነግርህ ነገር ያለ አልመሰለኝም። ደብረ ብርሃን ሄደህ ከእኔ ጋር ያዘጋጁትን ብትጠይቃቸው ግን ጥሩ ይመስለኛል። እኔ የዘጋጀኋቸውን ብዙ ሀሳቦች ሊሰጡህ ይችላሉ።

ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት፣ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎች ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ደመቀ ሙሉጌታ

ፊርማ

አድራሻ፡- የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ቀን 26-9-89

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

በደብረ ብርሃንና በደሴ መምህራን ማሠልጠኛ ተቋሞች ለሚሠለጥኑ መምህራን የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ-ማስተማሪያ መጽሐፍ የመርሀ-ትምህርቱን አላማዎች የሚያሟላ ነው ?

ደመቀ ሙሉጌታ

ግንቦት 1989